
# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

# የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት



## በፌዴራል ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኤጀንሲ የሙያ ደረጃ ምደባና ብቃት ምዘና ስርዓት እና የተቋማት ልማት አቅም ግንባታ አፈፃፀም ውጤታማነትን በተመለተ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት

መጋቢት 2011

አዲስ አበባ

# ማውጫ


ድርሞ /Excutive Summery/ ........ 1

ክፍል አንድ ........ 9

መግቢያ ........ 9

የኤጀንሲው አመሰራረት ........ 9

የኤጀንሲው ራዕይ ........ 10

የኤጀንሲው ተልዕኮ ........ 11

የኤጀንሲው ዓላማ ........ 11

የኤጀንሲው ሥልጣንና ተግባር ........ 11

የኤጀንሲው ድርጅታዊ መዋቅር እና የሰው ሀይል ........ 13

የፋይናንስ ምንጭ ........ 13

የፌ/ቴ/ሙ/ት/ስ ኤጀንሲ የአሰራር ስርዓት መግለጫ ........ 14

system description/ ........ 14

የሙያ ደረጃ ምደባ እና የሙያ ብቃት ምዘና ዳይሬክቶሬት ........ 14

የሠልጣኝና የተቋማት ልማት አቅም ግንባታ ዳይሬክቶሬት ........ 14

የኢንደስትሪ ኤክስቴንሽንና ቴክኖሎጂ ሽግግር ዳይሬክቶሬት የስራ ሂደት መግለጫ ........ 15

የምህንድስና ልህቀት ማዕከል ዳይሬክቶሬት የስራ ፍሰት መግለጫ ........ 16

ኦዲቱ ዓላማ ........ 16

የኦዲቱ ወሰንና ዘዴ ........ 16

ለክዋኔ ኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት አካባቢ ........ 18

የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች ........ 18

የኦዲቱ መመዘኛ መስፈርቶች ........ 18

ክፍል ሁለት ........ 19

የኦዲት ግኝቶች ........ 19

የሙያ ደረጃ ዝግጅት እና ክለሳን በተመለከተ፤ ........ 19

የስልጠና መሳሪያዎች (Teaching and Training learning material /TTLM / and Competency biased learning material /CBLM/ መዘጋጀታቸውን እና ተግባራዊ መደረጋቸውን በተመለከተ: ........ 22

ኤጀንሲው የምዘና መሳሪያዎች ስለማዘጋጀቱ እና ........ 24

አፈፃፀማቸውን ስለመከታተሉ በተመለከተ ........ 24

ኤጀንሲው የሙያ ብቃት ምዘና ስርዓት ስለመዘርጋቱ እና ........ 26
አፈፃፀሙን ስለመከታተሉ በተመለከተ ........ 26
ኤጀንሲው ሀገር አቀፍ የብቃት ምስክር ........ 29
ወረቀት አሰጣጥ ስርዓት መዘርጋቱን በተመለከተ ........ 29
የሙያ ብቃት ምዘና ማዕከላት ተደራሽነትን በተመለከተ ........ 32
መዛኞች ለመዛኝነት ሲመረጡ የመመዘኛ መስፈርቶችን ........ 34
ያሟሉ መሆኑን በተመለከተ ፣ ........ 34
የማሰልጠኛ ተቋማት ተደራሽነት እና ........ 36
እውቅና አሰጣትን በተመለከተ ........ 36
የእውቅና ፈቃድ አሰጣጥ እና ........ 38
ክትትልን በተመለከተ ........ 38
የማሰልጠኛ ተቋማት ዕውቅና በተሰጣቸው የማሰልጠኛ መርሃ ግብሮች መሰረት ማከናወናቸውን በተመለከተ ........ 39
በተቋማት የሚሰጠው ስልጠና በስራ ገበያ ፍላጎት መሰረት ........ 41
መሆኑን በተመለከተ፣ ........ 41
ኤጀንሲው በየትኛውም ደረጃ ለሚገኙ የቴ/ሙ/ት/ስ ........ 42
አመራሮች እና አሰልጣኞች የቅድመ ስራ እና ........ 42
የስራ ላይ ስልጠና መስጠቱን በተመለከተ ........ 42
የድህረ ስልጠና ክትትል ጥናቶችን ........ 44
Impact assessment / በተመለከተ ........ 44
በኤጀንሲው ልዩ ትኩረት እና ድጋፍ ........ 45
የሚሹ ጉዳዮች አፈጻፀምን በተመለከተ ........ 45
የቴ/ሙ/ት/ስ 70 በመቶ የተግባርና 30 በመቶ የንድፈ ........ 47
ሃሳብ ቀመርን ያሟሉ መሆኑን በተመለከተ ........ 47
ቅንጅታዊ አሰራርን በተመለከተ ........ 48
መረጃ አያያዝን በተመለከተ፣ ........ 50
ኤጀንሲው የቴ/ሙት/ስ መረጃ በመገናኛ ዘዴ ........ 52
ለህዝብ ይፋ መደረጉን በተመለከተ፣ ........ 52
**ክፍል ሦስት** ........ 54
**የመደምደሚያ ሃሳቦች** ........ 54
**ክፍል አራት** ........ 56

**የማሻሻያ ሀሳብ** ........ 56
(Recommendation) ........ 56

## ድርሞ /Excutive Summery/


የክዋኔ ኦዲቱ የተከናወነው ለመ/ቤታችን በአዋጅ ቁጥር 982/2008 ዓ.ም በተሰጠው ስልጣን መሰረት ሲሆን የክዋኔ ኦዲቱ አላማ የሙያ ደረጃ ምደባና ብቃት ምዘና እና የተቋማት ልማት አቅም ግንባታ አፈፃፀምን በመገምገም የተከሰቱ የአሰራር ችግሮች ካሉ መንስኤያቸውን በመለየት ችግሮቹን ለማስወገድ ወይም ለመቀነስ የሚያስችል የማሻሻያ ሃሳቦችን ማቅረብ ነው፡፡ ኦዲቱ የሸፈነው የሶስት በጀት ዓመታትን ከ2008 እስከ 2010 በጀት ዓመት ክንውኖችን ነው፡፡

የቴክኒክ እና ሙያ ትምህርት እና ስልጠና ኤጀንሲ የቴክኒክ እና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ዘርፍ ገበያው የሚፈልገውን የስራ ብቃትና ተነሳሽነት ያለው ስራ ፈላጊ ሳይሆን ስራ ፈጣሪ በመሆን የኢኮኖሚውን እድገትና ልማት የሚያፋጥን መልካም ስነ-ምግባር ያለው የሰው ኃይልን ለኢኮኖሚ እድገት ግብዓት የሚሆን ምርጥ ቴክኖሎጂን ማከማቸት እና ማሸጋገርን ዓላማ ያደረገ አገር አቀፍ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና እንዲሰጥ ለማስቻል ነው፡፡ ኤጀንሲው በአዋጅ ቁጥር 954/2008 እና በደንብ ቁጥር 199/2003 መሰረት የተሰጡት ተግባር እና ኃላፊነትን ቀልጣፋ እና ውጤታማ እንዲሆን በሚስችል መልኩ ባለመተግበሩ የሚከተሉት ዋና ዋና ግኝቶች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡-

1. **የሙያ ደረጃ ዝግጅት እና ክለሳን በተመለከተ፤**
   - ኤጀንሲው ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር በገበያ ፍላጎት መሰረት በአይነት፣ በደረጃና በመጠን በማጥናት የስራ ገበያውን ፍላጎት መሰረት ያደረጉ የሙያ ደረጃዎች ያልተዘጋጀላቸው ሙያዎች መኖራቸው ፣
   - በተዘጋጁት ሙያዎችም የጥራት ችግር መኖሩ እና የሙያ ደረጃ ከተዘጋጀላቸው ሙያዎች ውስጥ ስልጠና የማሰጥባቸው ሙያዎች መኖራቸው
   - የተከለሱ ሙያዎች አልፎ አልፎ በወቅቱ የማይላክበት ሁኔታ መኖሩ፣ የሙያ ደረጃዎች ሲከለሱ አዲስ ስለተዘጋጁ የሙያ ደረጃዎች አፈጻጸማቸው ከመቼ ጀምሮ፣ የትኞቹን ሰልጣኞች እንደሚመለከት አልፎ አልፎ በግልጽ የማያሳይበት ሁኔታ መኖሩ
   - ሰልጣኞች ባልተከለሰ የሙያ ደረጃ ሰልጥነው ምዘና በተከለሰው በሚሰጥበት ወቅት ሰልጣኞች ለማለፍ የሚቸገሩ መሆኑን
   - በሌላ በኩል የኦዲት ቡድኑ በናሙና ለመረጣቸው ለክልል የቴ/ሙ/ት/ስ/ቢሮዎች እና ለማሰልጠኛ ተቋማት ጉዳዩ ለሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ላቀረበው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ የፌ/ቴ/ሙ/ት/ስ/ ኤጀንሲ ተግባራዊነቱን አስመልክቶ በሚዘጋጁ የውይይት መድረኮች ላይ ውይይት ከማድረግ ያለፈ በቂ ድጋፍ እና ክትትል ያላደረገ መሆኑን ገልጸዋል ፡፡
2. **ኤጀንሲው ስርዓተ - ትምህርቶች እና የስልጠና መሳሪያዎች** (TTLM/CBLM) **በማሰልጠኛ ተቋሞች መዘጋጀታቸውን እና ተግባራዊ መከታተሉን በተመለከተ**
   - በኦዲቱ ወቅት ለኦዲት ቡድኑ ቀርበው ከተከለሱ ሰነዶች በሙያ ምደባው መሠረት የተዘጋጀ የመማር ማስተማር ማሰልጠኛ መሣሪያ /TTLM/ ተዘጋጅቶ ስራ ላይ

እንዲውል ያልተደረገበት ፤ አሰልጣኞች ስልጠና የሚሰጡበት መመሪያ በተሟላ ደረጃ አለመኖሩን፣ ስርዓተ-ትምህርቶች እና የስልጠና መሳሪያዎች /CBLM TTLM/ ያላዘጋጁ መኖራቸውን፡፡

- እንዲሁም ኤጀንሲው ስርዓተ-ትምህርቶች እና የስልጠና መሳሪያዎች (TTLM/CBLM) መዘጋጀታቸውን እና ተግባራዊ መደረጋቸውን ማረጋገጡን በተመለከተ የኦዲት ቡድኑ በናሙና ለተመረጡ ለክልል የቴ/ሙ/ት/ስ/ቢሮዎች እና የማሰልጠኛ ተቋማት የስራ ኃፊዎች ላቀ ረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ ስርዓተ-ትምህርቶች እና የስልጠና መሳሪያዎች /CBLM / TTLM/ ላይ የጥራት ችግር መኖሩን፤ በማሰልጠኛ ተቋማት ወቅታዊ የሙያ ደረጃን መሰረት ያደረገ TTLM/CBLM ዝግጅት ላይ ወጥ የሆነ አዘገጃጀት አለመኖሩን እንድሁም ኤጀንሲው ለተቋማት ድጋፍና ክትትል ሲያደርግ የቴክኒክ እና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ስርዓተ-ትምህርቶች እና የስልጠና መሳሪያዎች መዘጋጀታቸውን ከማየት ባለፈ ተግባራዊ ስለመደረጋቸው፣ ወቅታዊነት ያላቸው ስለመሆኑ እና ጥራት ያለቸው ስለመሆኑ በጥልቀት የማያረጋግጥ መሆኑን ገልጸዋል፣

3. **ኤጀንሲው በፀደቁና በተከለሱ የሙያ ደረጃዎች ላይ ተመስርቶ የምዘና መሳሪያዎች ዝግጅት ስርጭት የተደረገ ክትትል በተመለከተ፤-**

- የኦዲት ቡድኑ በኦዲቱ ወቅት ከከለሳቸው ሰነዶች ኤጀንሲው በፀደቁና በተከለሱ የሙያ ደረጃዎች ላይ ተመስርቶ የሙያ ብቃት ምዘና መሳሪያ ያላዘጋጀላቸው ሙያዎች መኖራቸው እና በተዘጋጀቱም ምዘና መሳርያዎች ላይ የጥራት መጓደል እና የእጥረት ችግር መኖሩን፡
- እንዲሁም በናሙና ለተመረጡ ጉዳዩ ለሚመለከታቸው የስራ ሃላፊዎች የኦዲት ቡድኑ ላቀረባቸው ቃለ መጠይቆች በሰጡት መልስ በደረጃ V የምዘና መሳርያ የሌላቻው ሙያዎች መኖራቸውን፣ በብቃት ማዕከላት በኩል ያልተከለሱ የምዘና መሳሪያዎችን የመጠቀም ችግር መኖሩን፡ የምዘና መሳሪያዎች የሚዘገዩበት ሁኔታ መኖሩን ፤ የምዘና ማዕከላት ለምዘና መሳሪያዎች ሚስጥራዊነት ተገቢውን ጥበቃ የማይደረጉበት ሁኔታ መኖሩን እና ኤጀንሲው በቂ ድጋፍና ክትትል የማይደረግ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

4. **ኤጀንሲው የሙያ ብቃት ምዘና ስርዓት ስለመዘርጋቱ እና አፈፃፀሙን ስለመከታተሉ በተመለከተ**

- በ2010 በጀት ዓመት በመንግሰት እና በግል ተቋማት መደበኛ ስልጠናን ያጠናቀቁ 377,844 ሲሆኑ የተመዘኑት 155,479 ብቻ መሆናቸውን ፤ አጫጭር ስልጠና ያጠናቅቁ 834,018 ሲሆኑ የተመዘኑት 177,219 መሆናቸውን ፤ በአጫጭር ስልጠና እና በኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን ድጋፍ ስራ ምዘና ያለመጠናቀቅ ችግር መኖሩን፡ በደቡብ ክልል ሀዋሳ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ በአንዳንድ ስልጠናዎች ደረጃ አንድን ሳያጠናቅቁ እና ሳይመዘኑ ወደ ደረጃ ሁለት የሚዘሉበት ሁኔታ መኖሩን፣ በአማራ ክልል ቅድመ ምዘና ግምገማ እና ማጠቃለያ ግምገማ የማይደርግ መሆኑን ፤ ስልጠና በተሰጠበት የብቃት አሀድ ምዘና የማይሰጥበት ሁኔታ መኖሩን ፤ የምዘና ማዕከላት ለምዘና መሳሪያዎች ሚስጥራዊነት ተገቢው ጥበቃ የማይደረግበት ሁኔታ መኖሩን፤ በአፋር ክልል የምዘና ወቅታዊነት ላይ ችግር ያለ በመሆኑ ሰልጣኞች ደረጃ

ሁለትን ሳይመዘኑ ደረጃ ሶስትን ተምረው ደረጃ ሁለትን እና ደረጃ ሶስትን በአንድ ላይ ምዘና እንዲወስዱ የሚደረግበት ሁኔታ መኖሩን

- እንዲሁም በኦዲት ቡድኑ በናሙና በተመረጡ የማሰልጠኛ ተቋማት እና የክልል የቴ/ሙ/ት/ስ/ቢሮዎች ባደረገው የሰነድ ክለሳ እና ለሚመለከታቸው የስራ ሃላፊዎች ቃለ መጠይቅ አቅርቦ ከተሰጡ መልሶች፡- ለሰልጣኞች በወቅቱ ምዘና የማይሰጥበት እና የሚዘገይበት ሁኔታ መኖሩን ፣ ሰልጣኞች በምዘና ሂደት ውስጥ እንዲያልፉ የማይደረግበት ሁኔታ መኖሩን እንዲሁም የቴ/ሙ/ት/ስ ሰልጣኞች በምዘና ሂደት ውስጥ ያለፉ ስለመሆኑ በቂ ክትትል እና ቁጥጥር የማይደረግ መሆኑን የሚመከለታቸው የስራ ኃላፊዎች ገልጸዋል፡፡

5. **ኤጀንሲው ሀገር አቀፍ የብቃት ምስክር ወረቀት አሰጣጥ ስርዓት መዘርጋቱን በተመለከተ**

   - የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት ለሰልጣኞች የሚሰጥ የስልጠና የምስክር ወረቀት በየተቋሙ የሚለያይ መሆኑን
   - በደቡብ ብ/ክ/መ የቴ/ሙ/ት/ስ ቢሮ ብቃታቸውን ላረጋገጡ ባለሙያዎች ደረጃ 4 ለደረሱ ባለሙያዎች ብቻ ኦርጅናል የምስክር ወረቀት እነደሚሰጥና ደረጃ 1/ 2 /3 በጊዚያዊ የምስክር ወረቀት ብቻ እንዲቆዩ የሚደረግ መሆኑን ፣ ብቃታቸውን ላረጋገጡ ተመዛኞች ሰርተፊኬት ያለመስጠት ሁኔታ መኖሩን/በተለይ ደረጃ1 እና 2/ ፣ በአጫጭር ስልጠና አጠናቀው የሚወጡ ሰልጣኞችን የደረጃ አንድ ሰርትፍኬት የሚሰጥበት ሁኔታ መኖሩ፣
   - በኦዲት ቡድኑ በተካሄዱ የመስክ ስራዎች ለሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ከቀረቡ ቃለ መጠይቆች እና ከተከለሱ ማስረጃወች የሚከተሉት የአሰራር ችግሮች ታይተዋል፡-የሙያ ብቃት ምዘናና ሀገር አቀፍ የብቃት ምስክር ወረቀት አሰጣጥ ስርዓትን ዘርግቶ ጊዜያዊ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት በብቃት ማዕከላት ተዘጋጅቶ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ስለመሰጠቱ እና ዋናውን በሶስት ወር ውስጥ አዘጋጅቶ በማዕከላት በኩል ለተመዛኞች የማድረስ ስራ እየተሰራ አለመሆኑን፣ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ለሦስት አመታት ብቻ ስለማገልገሉ እና ከ 3 ዓመት በኋላ የሙያ ደረጃው ከተቀየረ ባለሙያው ምዘናውን እንደገና የማይወስድ መሆኑን፣ ከ 3 ዓመት በኋላ የሙያ ደረጃ ካልተቀየረ የአገልግሎት ክፍያ በማስከፈል በየ ሦስት ዓመቱ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱ የማይታደስ መሆኑን፣ እንዲሁም ኤጀንሲው አፈፀሙን የማይቆጣጠር መሆኑን ታውቋል፡

6. **የሙያ ብቃት ምዘና ማዕከላት ተደራሽነትን በተመለከተ**

   - የሙያ ብቃት ምዘና ማዕከላትን ተደራሽ አለመሆናቸው እና ማዕከላት በክልሎች የተለያየ አወቃቀር ያላቸው መሆኑ
   - የደቡብ ክልል የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ኤጀንሲ አደረጃጀቱ የተገልጋዩችን ፍላጎት በሚመጥን ደረጃ በሰው ሀይል እና በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ያልተደራጀ በመሆኑ በክልሉ ባሉ የምዘና ጣብያዎች አገልግሎት በሚፈለግ ጊዜ በወቅቱ ተገኝቶ አገልግሎት ለመስጠት ያልቻለ መሆኑን፣

- ኤጀንሲው የሙያ ብቃት ምዘና ማዕከላት ተደራሽ እንዲሆኑ ለመደገፍና ለመከታተል የሚያስችል የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት የተሰሩ ስራዎች ቢኖሩም የብቃት ምዘና ማዕከሉ እራሱን ችሎ ገለልተኛ ሆኖ ባለመቋቋሙ አቅሙ ውስን እንዲሆን ማድረጉ፣ የሚቋቋሙት የምዘና ጣቢያዎች ደረጃቸውን የጠበቁ አለመሆናቸውን እና ማሰልጠኛ ተቋማት ምዘና ጣብያ ሆነው ምዘና የሚሰጥ መሆኑን፣ እና በሙያ ብቃት ምዘና ሂደት አሠራር የብቃት ምዘና ማዕከላትን ማብቃት ላይ ያደረገው ድጋፍና ክትትል በቂ አለመሆኑን፣

7. **በኤጀንሲው መዛኞች ለመዛኝነት ሲመረጡ የሚያስፈልጉ መመዘኛ መስፈርቶችን ያሟሉ ስለመሆኑ መከታተሉን በተመለከተ**
   - በአማራ ክልል ቴ/ሙ/ት/ስ ቢሮ ለ9 የቴ/ሙ/ት/ስ ኮሌጆች የተደረገ ክትትል ከተመዛኞች ጋር ተመሳሳይ ደረጃ ያላቸው መዛኞች የሚመደቡበት ሁኔታ መኖሩን
   - በደቡብ ክልል ባልተመዘኑ እና ያለ ደረጃ በመዛኝነት የሚመደብበት ሁኔታ መኖሩን ለምሳሌ በአውቶሞቲቭ በደረጃ 3 የበቃ መዛኝ ደረጃ 4 ላይ መመደቡን ፣ ለኢንዳስትሪ መዛኞች ደረጃ ያልወጣ እና ወቅታዊ ብቃታቸው የሚገመገምበት ስርዓት ያልተዘረጋ መሆኑን ፣
   - እንዲሁም በኦዲት ቡድኑ በናሙና ለተመረጡ የማሰልጠኛ ተቋማት ፣ የክልል የቴ/ሙ/ት/ስ/ቢሮዎች እና የምዘና ማእከላት የስራ ኃላፊዎች ከቀረቡ ቃለ መጠይቆች የሚመለከቱ ሁኔታዎች ተገኝተዋል፦ ምዘና በብዛት በሚኖርበት ወቅት የመዛኝ እጥረት እንደሚከሰት ይህንንም ተከትሎ መስፈርት ሳያሟላ የሚመረጥ መዛኝ የሚመረጥበት ሁኔታ መኖሩን እንዲሁም የፌዴራል የቴ/ሙ/ት/ስ/ኤጄንሲ ለመዛኝነት የሚመረጡ መዛኞች የሚያስፈልጉ የመመዘኛ መስፈርቶችን አሟልተው የተመረጡ ስለመሆኑ ክትትል የማያደርግ መሆኑን የሚመለከታቸው የስራ ሃላፊዎች ገልጸዋል፡፡

8. **የማሰልጠኛ ተቋማት ተደራሽነት እና እውቅና አሰጣትን በተመለከተ**
   - በሀገር አቀፍ ደረጃ በአንድ ወረዳ አንድ ማሰልጠኛ ተቋም እንዲኖር ለማድረግ ቢታቀድም በ2010 በጀት ዓመት 158 አዳዲስ ማሰልጠኛ ተቋማት ለመገንባት የታቀደ ቢሆንም መገንባት የተቻለው 24(15%)ብቻ መሆኑን ፣ በ2010 በጀት ዓመት በአገር አቀፍ ደረጃ 225 እውቅና እንዲያገኙ ታቅዶ 17(8%) ብቻ እውቅና ያገኙ መሆኑን ፣ በ2010 በጀት ዓመት በዓለም አቀፍ ደረጃ 12 እውቅና እንዲገኙ ቢታቀድም እውቅና ያገኘ ማሰልጠኛ ተቋማት አለመኖሩን
   - በናሙና ከታዩ ክልሎች በኦሮሚያ ክልል ውስጥ ከሚገኙ 336 ወረዳዎች ውስጥ 163 ወረዳዎች ላይ ብቻ ተቋማት መክፈት እንደተቻለ መገለጹ ፣ በደቡብ ክልል ከ135 ወረዳዎች 51 ወረዳወች ላይ ብቻ የማሰልጠኛ ተቋማት መክፈት እንደተቻለ መገለጹ፣ በአፋር ክልል እስከ ሁለተኛው የዕድገት እና ትራንሰፎርሜሽን ዕቅድ መጨረሻ 7 የቴ/ሙ/ት/ስ/ ኮሌጆችን ለመገንባት ቢታቀድም ምንም ግንባታ አለመከናወኑ በፌ/ቴ/ሙ/ት/ስ/ኤ የ2010 ዓ.ም. ዕቅድ አፈጻጸም መገለፁ፣

9. **የእውቅና ፈቃድ አሰጣጥ እና ክትትልን በተመለከተ**
   - በኦዲቱ ወቅት ለኦዲት ቡድኑ ቀረበው ከተከለሱ ሰነዶች የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡- በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የቴክኒክ ሙያ ትምህርት ና ስጠና ቢሮ የቴ/ሙ/ት/ስ/ ተቋማት ላይ የተካሄደ ክትትልና ድጋፍ ሪፖርት፣ የካቲት 2010 ዓም አማኑኤል የወጣቶች ስልጠና ማስተባበሪያ ወቅቱን ጠብቆ እውቅና ያለማደስ፣ ኮንሰርን ወርልድ እውቅና ፈቃድ ሳይኖረው ማሰልጠን/ ስልጠና የሚሰጠው ልደታ ማኑፋክቸሪንግ ውስጥ መሆኑ/፣ ሀንድ ካን ኢንተርናሽናል ከቴ/ሙ/ት/ስ የስልጠና ፍቃድ ሳያገኝ የስልጠና ስራ መስራቱ፣
   - እንዲሁም በኦዲት ቡድኑ በናሙና ከተመረጡ ክልል ቢሮዎች፣ ተቋማት ለሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ ለቀረበ ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ የ/ፌ/ቴ/ሙ/ስ/ኤጀንሲ ፈቃድ የወሰዱ ስለመሆኑ በቂ ክትትል እና ቁጥጥር እያደረገ አለመሆኑን ገልጸዋል፡፡

10. **የማሰልጠኛ ተቋማት ዕውቅና በተሰጣቸው የማሰልጠኛ መርሃ ግብሮች መሰረት ማከናወናቸውን በተመለከተ**
   - በኦዲቱ ወቅት ለቡድኑ ቀርበው ከተከለሱ ማስረጃዎች የሚከተሉት ችግሮች ተገኝተዋል፡- በአማራ ክልል ህጋዊ አሰራርን የጣሱ ኮሌጆች መኖራቸው ከተፈቀደላቸው ቁጥር በላይ ሰልጣኝ የሚቀበሉ ኮሌጆች መኖራቸውን፣ ከዘመኑ የመግቢያ ነጥብ በታች ሰልጣኞችን የሚቀበሉ ኮሌጆች መኖራቸውን፣ የሰልጣኝ አሰልጣኝ ጥምርታን መሰረት በማድረግ ብቁና ቋሚ አሰልጣኝ አሟልተው የማይገኙ ኮሌጆች መኖራቸውን እንዲሁም አንዳንድ የግል ኮሌጆች ፈቃድ ሳይጠይቁ ሰልጣኞችን መዝግበው ስልጠና የሚሰጡበት ሁኔታ መኖሩን፣ በሰረቭይንግ 15 ሰልጣኞች ሰልጣኞችን መቀበሉን ለማወቅ ተችሏል፡፡
   - እንዲሁም የኦዲት ቡድኑ በናሙና በተመረጡ ክልል ቢሮዎች፣ ተቋማት ለሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች በፌ/ቴ/ሙ/ት/ስ/ኤጀንሲ ስለሚደረገው ክትትል እና ቁጥጥር በማስረጃ አስደግፈው እንዲያብራሩ ለቀረበ ቃለ መጠይቅ ሲመልሱ በቂ ክትትል እየተደረገ አለመሆኑን ገልጸዋል፣

11. **በተቋማት የሚሰጠው ስልጠና በስራ ገበያ ፍላጎት መሰረት መሆኑን በተመለከተ፣**
   - ኦዲት ቡድኑ በናሙና በተመረጡ 4 ክልሎች እና በ 8 የማሰልጠኛ ተቋማት የሚሰጡ ስልጠናዎች በስራ ገበያ ፍላጎት መሰረት ስለመሆናቸው የሚሳይ የገበያ ፍላጐት ጥናት የተደረገባቸው ማስረጃች አለመኖራቸውን እንዲሁም ኤጀንሲው በተቋማት የሚሰጡ ስልጠናዎች በስራ ገበያ ፍላጎት መሰረት ስለመሆናቸው እና በጥራት ላይ ጠንካራ የክትትል ስራ አለመሰራቱን ለማወቅ ተችሏል፡፡

12. **ኤጀንሲው በየትኛውም ደረጃ ለሚገኙ የቴ/ሙ/ት/ስ አመራሮች እና አሰልጣኞች የቅድመ ስራ እና የስራ ላይ ስልጠና መስጠቱን በተመለከተ፡-**
   - በኦዲቱ ወቅት ለቡድኑ ቀርበው ከተከለሱ ማስረጃዎች ኤጀንሲው የቴ/ሙ/ት/ስ አመራሮች እና አሰልጣኞች የቅድመ ስራ እና የስራ ላይ ስልጠና በዘጠኝ ክልሎች

እና በሁለት ከተማ መስተዳደር የበቁ የቴ/ሙ/ት/ስ/ አሰልጣኞችን የ2010 ዕቅድ አፈፃፀም በኦሮሚያ(24%)፣ አማራ(1.1%)፣አፋር(0) ፣ሶማሌ(44%)፣ ጋምቤላ(0)፣ አዲስ አበባ(2%)፣ በአጠቃላይ አፈፃፀሙን 22% መሆኑ እንዲሁም በአመራሮች የዕቅድ አፈፃፀም አማራ(1.3%)፣ሱማሌ(39)፣ አፋር(0)፣ ቤ/ጉሙዝ(40)፣ ጋምቤላ(0)፣ ድሬ ዳዋ(0) በአጠቃላይ አፈፃፀሙን 38% መሆኑ እንዲሁም የፈሩት የኢንዱስትሪ ውስጥ አሰልጣኞች የማስተማር ስነዘዴ ስልጠና እንዲወስዱ ከማድረግ አንፃር ውስንነት መኖሩ፣

- እንዲሁም በናሙና የተመረጡ ክልል ቢሮዎች፣ ማሰልጠኛ ተቋማት ለሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች የኦዲት ቡድኑ ላቀርበው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ ኤጀንሲው የአቅም ግንባታ ስልጠናው የጥራት ችግር ያለበት በመሆኑ ተመሳሳይ ስልጠና በተደጋጋሚ የመሰጥበት ሁኔታ መኖሩ፣ የመንግስት ተቋማት አሰልጣኞች የቅድመ እና የድህረ ስራ ስልጠና ኮታ በመስጠት ቢያሰለጥኑም ነገር ግን ለግል ተቋማት የስልጠና እድል እንደማይሰጡ እንዲሁም የተሰጡ ስልጠናዎች አፈፃፀም ላይ ቁጥጥር የማያደረርግ መሆኑን ለኦዲት ቡድኑ ቀርበው ከተከለሱ ሰነዶች ለማወቅ ተችሏል፡፡

## 13.የድህረ ስልጠና ክትትል ጥናቶችን /Impact assessment / በተመለከተ

- በኤጀንሲ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ስርዓት ውጤታማነቱን ለማረጋገጥ የድህረ ስልጠና ክትትል ጥናቶችን /Impact assesement/ ፍላጎት በሙያ በዓይነትና በደረጃ በመለየት ያልተካሄደ መሆኑን፡

## 14.ኤጀንሲው ልዩ ትኩረት እና ድጋፍ የሚሹ ጉዳዮች አፈፃፀምን በተመለከተ፡-

- በ2010 ዓ.ም. የፌ/ቴ/ሙ/ ኤጀንሲ ዕቅድ አፈፃፀም የሴቶች ተሳትፎ በመደበኛ ስልጠና አዲስ የመደበኛ የሴት ሰልጣኝ ቅበላ አፈጻጸም በሶማሌ 42% አፋር 35% እና ጋምቤላ 16% መሆኑን፣ የሴቶች ተሳትፎ በመደበኛ ስልጠና ተሳትፎ ላይ በጋምቤላ ስልጠና ያጠናቀቁ ብዛት 1314 ሲሆኑ የተመዘኑ 108 ( 8.2%) እና በአፋር ስልጠና ያጠናቀቁ ብዛት 503 የተመዘኑ እና የበቁ የሌሉ መሆኑን፣
- የአካል ጉዳተኞች የመደበኛና የአጫጭር ስልጠና ተሳትፎ ያጠናቅቁ ፣ የተመዘኑ እና ከተመዘኑት የበቁ አፈፃፀሙ ቤ/ጉምዝ(0)፣ ጋምቤላ(0)፣ በአፋር መደበኛና ባጫጭር ያጠናቅቁ ብዛት (18)፣ሀራሪ በመደበኛና ባጫጭር ያጠናቅቁ ብዛት (45) የተመዘኑ እና ከተመዘኑት የበቁ አፈፃፀሙ 0 መሆኑን፣ የቴ/ሙ/ት/ስልጠና ከአዲስ አመራሮች ውስጥ በስርአቱ ያደጉ አመራሮች ድርሻ የሴቶች ተሳትፎ በዘጠኝ ክልሎችና ሁለት ከተማ መስተዳድሮች አፈፃፀሙ 35% መሆኑን፣
- ሴቶች (የአርብቶ አደሩን ሴት ልጆች) እና ለአካል ጉዳተኞች አስፈላጊውን ግብኣት ከማሟላት አንጻር ውስንነት መኖሩን እና ወርክ ሾፖች እና የስልጠና ቦታዎች ለአካል ጉዳተኞች አመቺ አለመሆናቸውን ፣ ለአካል ጉዳተኞች አስፈላጊውን ግብአቶች ከማሟላት አንጻር /የአይነ ስውራን ብሬል/ እጥረት መኖሩን ለአብነት የምዘና መሳሪያዎች በብሬል የታገዙ እንዳልሆኑ ፣ መስማት ለተሳናቸው ግብአቶች እንዳልተሟሉ እና ስልጠናም እንደማይሰጥ እንዲሁም በዘርፉ የሰለጠነ ባለሙያ

እጥረት መኖሩን እንዲሁም በአካል ጉዳተኞች በኩል በቂ የግንዛቤ ስራ ያልተሰራ መሆኑን፣

- ኤጀንሲው በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ዙሪያ ሴቶች፣ አካል ጉዳተኞች እና ልዩ ድጋፍ ለሚሹ ክልሎች ትኩረት እንዲያገኙ የሚያስችል ስርዓት በመዘርጋት መግቢያ ነጥብ ጀምሮ ተጠቃሚ እና ጉዳተኞች ምቹ ሁኔታ እንዲኖር የተሰራ ስራ ቢኖርም ተግባራዊነቱን ለማረጋገጥ የሚያደርገው ድጋፍና ክትትል በቂ አለመሆኑን፣

15. **የቴ/ሙ/ት/ስ 70 በመቶ የተግባርና 30 በመቶ የንድፈ ሃሳብ ቀመርን ያ ሟሉ መሆኑን በተመለከተ**
   - በኦዲቱ ወቅት ለቡድኑ ቀርበው ከተከለሱ ማስረጃዎች በየተቋማቱ የሚሠጡ የቴ/ሙ/ት/ስልጠናዎች 70 በመቶ የተግባርና 30 በመቶ የንድፈ ሃሳብ ቀመርን የሚሸፍን እንዲሆን የአሰራር ስርአት ቢዘረጋም ተግባራዊ አለመደረጉን ፣
   - የትብብር ስልጠና ትግበራ ከጥራትም ሆነ ከሽፋን አንጻር ከፍተኛ ችግር ያበት መሆኑን ፣ በትብብር ስልጠና ጊዜ የኢንዳስትሪ ውስጥ አሰልጣኝ እጥረት መኖሩን ፣ ሰልጣኞች ለትብብር ስልጠና ወደ ኢንተርፕራይዞች ፣ ኢንዱስትሪዎችን እና ካምፓኒዎች በሚወጡበት ጊዜ የኢንዱስትሪ አሰልጣኝ የማይመደብበት መሆኑ ለኦዲት ቡድኑ በኤጀንሲው እና በመስክ ስራ ወቅት ቀርበው ከተከለከሱ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡
   - በናሙና ለተመረጡ ክልል የቴ/ሙ/ት/ስ/ ቢሮዎች እና የብቃት ምዘና ማዕከላት፣ ለሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች የኦዲት ቡድኑ ላቀረበው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ እንደ ሀገር በቴክኒክ እና ሙያ የሚሰጡ ስልጠናዎች የየአካባቢውን ፀጋ(ሁኔታ) ያላገናዘቡ እና 70 በመቶ የተግባርና 30 በመቶ የንድፈ ሃሳብ ቀመርን የሚሸፍን አለመሆኑን ገልጸዋል፣

16. **ኤጀንሲው ከባለድርሻ አካላት ያለው ቅንጅታዊ አሰራር በተመለከተ፡**
   - በኦዲቱ ወቅት ለኦዲት ቡድኑ ቀርበው ከተከለሱ ማስረጃዎች ክልል ቴ/ሙ/ት/ስ/ቢሮዎች፡ የኢንዱስተሪዎች እና የማሰልጠኛ ተቋማት የጋራ እቅድ የሌላቸው መሆኑን፣ በክልል ደረጃ የዘርፍ መሪ መስሪያ ቤቶች ጋር የኢንዱስትሪውን ባለቤተነት የሚጠይቁ ተግባራትን ለይቶ በማቀድ ወደ ተግባር መግባትና የዘርፍ መስሪያ ቤቶች ሚናቸውን እንዲወጡ ከማድረግ አንፃር ውስንነት መኖሩን ከተደረገ የሰነድ ክለሳ ለማወቅ ተችሏል፡፡
   - እንዲሁም ከሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚ/ር፣ ከባህልና ቱሪዝም ሚ/ር ፣ ከአነስተኛ እና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኤጀንሲ እና ከብረታ ብረት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንተርፕራይዝ ጋራ አብሮ ለመስራት በ2010 ዓ.ም. የጋራ ዕቅድ ቢታቀድም ያልፀደቀ እና ወደ ተግባር ያልተገባበት መሆኑን ገልጸዋል፡፡
   - በኦዲት ቡድኑ በናሙና ለተመረጡ ባለድርሻ አካላት የሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ ለቀረቡ ቃለ መጠይቅ በተሰጠ መልስ ከፌደራል ቴክኒክና ሙያ ትምህርት እና ስልጠና ኤጀንሲ ጋር ያለው ቅንጅታዊ አሰራር

በሚፈለው መጠን ካለመሆኑንም ባሻገር ከ2008 ዓ.ም. ጀምሮ ቅንጅታዊ አሰራር እና የድጋፍና ክትትል ስራ በፌደራሉ የቴ/ሙ/ት/ስ/ኤጀንሲ በኩል የለም በሚባል ደረጃ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

17.**መረጃ አያያዝን በተመለከተ፣**

1. የፌ/ቴ/ሙ/ት/ስ ኤጀንሲ በሀገር አቀፍ ደረጃ መረጃ በማሰባሰብ ፣ በማደራጀት ፣ በመረጃ ቋት(በዳታ ቤዝ) በማጠናከር እና በየጊዜው በማሻሻል የማይዝ መሆኑን፣
2. በቁልፍና አበይት ተግባራት ዕቅድ ሲታቀድ የሚያስፈልጉ መሰረታዊ መረጃዎች ምን ምን እንደሆኑ የሚያሳይ መረጃ አለመደራጀቱን፣ በአብዛኞቹ ተቋማት መረጃን ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር መለዋወጥ ላይ ክፍተቶች መኖራቸው

18.**ኤጀንሲው የቴ/ሙ/ት/ስ መረጃ ለህዝብ ይፋ ማድረጉን በተመለከተ፡-**

- በኦዲቱ ወቅት ለቡድኑ ቀርበው ከተከለሱ ሰነዶች የታዩ ችግሮች፡ ሀገር አቀፍ የሙያ ብቃት ማዕቀፍን ለኢንዱስትሪውና ለተጠቃሚው ህብረተሰብ ለማስገንዘብ የሚሰሩ ስራዎች ጠንካራ አለመሆናቸውን በኦዲት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡
- ሀገራዊ የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት በማሳተም፣ ለብቃት ማዕከላት ማሰራጨት እና ሰርተፊኬት የተሰጣቸውን የባለሙያዎች ሀገራዊ መረጃ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ በመታገዝ ለመያዝ በኤጀንሲው ቢታቀድም ዕቅዱን ለማስፈጸም የሚያስችል ተገቢ አደረጃጀት ኤጀንሲው የሌለው በመሆኑ
- ኤጀንሲው ከክልል አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር እውቅና የተሰጣቸውን መርሃ ግብሮችና የሚሰጡባቸውን ማሰልጠኛ ተቋሞች የተጠቃለለ ዝርዝር መረጃ አደራጅቶ በመያዝ በየወቅቱ በመገናኛ ዘዴ ለህዝብ ይፋ የማይደረግ መሆኑን፣

# ክፍል አንድ

## መግቢያ

### የኤጀንሲው አመሰራረት

1. የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና  አገሪቷ የተያያዘችውን ፈጣን ልማት ዘላቂነት ባለው መልኩ ለማሳደግና አገራዊ ራዕይውን እውን ለማድረግ ብቁ የሰው ሀይል በማቅረብ በኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን እና በቴክኖሎጂ ሽግግር አገልግሎት የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን ተወዳዳሪነት በማሳደግ ረገድ የማይተካ ሚና አለው፡፡
2. የሀገራችን ኢኮኖሚያዊ እድገቱን ቀጣይነት ለማረጋገጥም ሆነ ለእድገቱ የሚመጥን ብቁ የሰው ሀይል ለመፍጠር መሰረት ሰለሆነ የአገራችን የኢኮኖሚ ለውጥና ቀጣይነት የማረጋገጥ ጉዳይ የቴክኖሎጂ እድገት ቀጣይነትን ማረጋገጥ የሚችል ብቁ የሰው ሃይል ማፍራት ላይ መመስረቱ የማይቀር ነው፡፡
3. ለሃገራችን የኢንዱስትሪ ዕድገት ዝቅተኛ መሆን ፣ የሰለጠነ የሰው ሃይል እጥረት ዋና መንስዔ እንደሆነ የኢንዱስትሪ ልማት ስትራቴጂ ሰነዱ ይጠቁማል፡፡ በተጨማሪም ስትራቴጂው  ሃገሪቷ ከሙያም ሆነ ከስነ ምግባር አንጻር ብቃት ያለውና የኢንዱስትሪ ዕድገት ግቦችን በዘላቂነት ሊያሳካ የሚችል የሰው ሃይል የሚፈጥር የትምህርትና ስልጠና ስርዓት እንዳልነበራት አስምሮበታል፡፡ በመሆኑም የሃገሪቷን የሰው ኃይል ጥራት ወደ ዓለም አቀፍ ደረጃ ለማሳደግ፣ የቴክኒክና ሙያ ትምህርት እና ስልጠና ስርዓት ትኩረት ተነፍጓቸው በቆዩ የኢንዱስትሪ ሙያዎች ላይ በማተኮር የታታሪነት ባህልን እና ስራ ፈጠራን ለማዳበር ከፍተኛ ጥረት መደረግ እንዳለበት ይጠቁማል፡፡
4. በመሆኑም የሀገሪቱ የማምረቻ፣ የንግድ እና አገልግሎት ሰጭ ድርጅቶች በቴክኒክና በሙያ ብቃት ያለው የሰለጠነ የሰው ሃይል ቀጥሮ በማሰራት ብቁ ተወዳዳሪ እና ዘላቂነት ያለው ድርጅታዊ አቋም እንዲኖራቸው ማስቻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ የቴክኒክና ሙያ ትምህረትና ስልጠና ስርዓትን ለማደራጀት ሲባል በአዋጅ ቁጥር 391/1996 በትምህርት ሚኒስቴር በትምህርት ዘርፍ ስር ተደራጅቶ የቆየ ሲሆን የቴክኒክና ሙያ ትምህርት እና ስልጠና ላይ ትኩረት በመሰጠቱ  ከ1997 ዓ.ም ጀምሮ እንደ አዲስ ራሱን ችሎ የቴክኒክና ሙያ ትምህረትና ስልጠና ዘርፍ በመሆን ተዋቀረ፡፡

5. የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ዘርፍ ገበያው የሚፈልገውን የስራ ብቃትና ተነሳሽነት ያለው ስራ ፈላጊ ሳይሆን ስራ ፈጣሪ በመሆን የኢኮኖሚውን እድገትና ልማት የሚያፋጥን መልካም ስነ-ምግባር ያለው የሰው ኃይልን ለኢኮኖሚ እድገት ግብዓት የሚሆን ምርጥ ቴክኖሎጂን ማከማቸት እና ማሸጋገርን ዓላማ ያደረገ አገር አቀፍ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ስትራቴጂ በ1999 ዓ.ም ከወጣ እና የቴክኒክና ሙያ ትምህረትና ስልጠና ተቋማት ከተስፋፉና የሰው ኃይሉ ተሳትፎ ከፍ ካለ በኃላ በ2003 ዓ.ም የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኤጀንሲን ለማቋቋም በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 199/2003 ኤጀንሲ የሚል ስያሜ በማግኘት ተቋቋመ ፡፡

6. በመሆኑም በኢኮኖሚ ረገድ ተወዳዳሪ ሆኖ ለመዝለቅ ክህሎት ያለው፣ በዲሲፕሊን የታነፀ፣ ተነሻስነት የተላበሰና ከአዳዲስ አሰራሮች ጋር ተዋህዶ ስራውን የሚያከናውን የሰው ኃይል ማፍራት ያለውን ወሳኝ ድርሻ በመገንዘብ በሁሉም ክልሎች ለሁሉም የልማት ዘርፎች የሚያስፈልገውን በዝቅተኛ እና መካከለኛ ደረጃ የሰለጠነ የሰው ኃይል ማቅረብ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ዘርፍ ተልዕኮ እንዲሆን እና ሀገሪቷ ካላት ፀጋ እና የእድገት መሰረት አንዱ እና ዋነኛው የሰው ሃብት በመሆኑ ይህንን የሰው ኃይል በስፋት በማልማት ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ፈጣን፣ ቀጠይና ተከታታይ እንዲሁም ተደራሽ በማድረግ ረገድ ዘርፉ ማሳካት ያለበት ተልዕኮ በስራ ላይ እየዋለ ባለው የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ስትራቴጂ በግልፅ ተመልክቷል፤፤እንዲሁም የዘርፉን ስትራቴጂ የህግ መሰረት እንዲኖረው ለማድረግ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና አዋጅ ቁጥር 954/2008 ተደንግጓል፡፡

## የኤጀንሲው ራዕይ

7. ለአገሪቷ ኢኮኖሚያዊ ዕድገት አስተዋፅኦ የሚያበረክት ብቁና በሙያው የሚተማመን ዜጋ በማፍራት የህዝቡን የኑሮ ሁኔታ ማሻሻልና ቀጣይነት ባለው ሁኔታ ፈጣን ፍትሃዊ ልማትን በማረጋገጥ ድህነትን ማጥፋት ነው፡፡

## የኤጀንሲው ተልዕኮ

8. በሃገሪቷ ብቁ ተነሳሽነት እና የፈጠራ ክህሎት ያለው የሰለጠነ የሰው ሀይል መፍጠርና ኢንዱስትሪውን ተወዳዳሪ የሚያደርግ ምርጥ ቴክኖሎጂ በማቅረብና በማሸጋገር በሀገሪቷ ምርታማ የሆነ ዜጋ በመፍጠር ድህነትን ማስወገድና ለማህበራዊ ኢኮኖሚያዊ እድገት አስተዋፅኦ ማድረግ ነው፡፡

## የኤጀንሲው ዓላማ

9. ኤጀንሲው የሀገሪቱን የኢኮኖሚዊ እና ማህበራዊ እድገት ዓላማዎች ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና በአግባቡ ተደራጅቶና ጥራቱ ተጠብቆ በዘላቂነት እንዲካሄድ የማድረግ እና ዜጎች ፍትሀዊ በሆነ መንገድ ተገቢውን ሥልጠናዎች እንዲያገኙ እና የሀገሪቱን የልማት ትልምና የሰለጠነ የሰው ኃይል ፍላጎትን መሠረት ያደረጉ መሆናቸውን የመከታተልና የሥራ ፈጣሪነትን ባህል የማጎልበት እንዲሁም የጥቃቅንና አንስተኛ ኢንተርፕራይዞችን አቅም የማጎልበት ዓላማ ይኖሩታል፡፡

## የኤጀንሲው ሥልጣንና ተግባር

10. የፌዴራል ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኤጀንሲ በደንብ ቁጥር 199/2003 ዓ.ም. የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ተሰጥቶታል:-

- የሀገሪቱን የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ስትራቴጂ ለማስፈፀም የሚያስችል እስታንዳርድ እና የህግ ማዕቀፍ ረቂቆች ያዘጋጃል ሲፀድቁም ተግባራዊነታቸውን ይከታተላል፣
- የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና አቅራቢዎች የቴክኖሎጂ አቅም ግንባታ ማእከላት መሆናቸውን እና በቴክኖሎጂ ሽግግሩ ለገበያ ተወዳዳሪ የሆኑ ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች መፈጠራቸውን ያረጋግጣል፣
- ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ባለድርሻዎች ጋር በመተባበር በዘርፉ ሀገር አቀፍ የሙያ ብቃት ማዕቀፍ ያዘጋጃል ተግባራዊነቱንም ይከታተላል፣
- ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የስራ ገበያውን ፍላጎት መሰረት ያደረጉ የሙያ ደረጃዎች ያዘጋጃል ተግባራዊነቱንም ይከታተላል፣
- በጸደቁት የሙያ ደረጃዎች ላይ ተመስርቶ የምዘና መሳሪያዎችን ያዘጋጃል፡፡ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ሥርዓት-ትምህርቶች ከጸደቁት የሙያ

ደረጃዎች በመነሳት መዘጋጀታቸውን እና ተግባራዊ መደረጋቸውን ያረጋግጣል፣

- የሙያ ብቃት ምዘናና ሀገር አቀፍ የብቃት ምስክር ወረቀት አሰጣጥ ስርዓት ይዘረጋል አፈፃጸሙን ይቆጣጠራል፣
- የማሰልጠኛ ተቋማትና የሙያ ምዘና ማዕከላት እውቅና የሚያገኙበትን መመዘኛና መመሪያ ያወጣል አፈጻፀሙንም ይቆጣጠራል
- የትብብር ስልጠና አፈጻፀም መመሪያ ያወጣል ተግባበራዊነቱንም ይከታተላል፣
- የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና የስራ ሀላፊዎችን እና አሰልጣኞችን የብቃት መስፈርት ይወስናል ተግባራዊነቱን ይከታተላል፣
- እንዳስፈላጊነቱ በፌዴራል መንግስት የሚቋቋሙ የቴ/ሙ/ት/ስ መምህራን እና የአሰልጣኞች ማሰልጠኛ ተቋማትን ያስተዳድራል፣
- የቴ/ሙ/ት/ስ ፕሮግራሞች ስኬታማ እንዲሆኑ ለክልሎች ተገቢውን እገዛ ያደርጋል፣
- የግል ባለሀብቶችንና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት የሀገሪቱ የልማት ዕቅድና የስራ ገበያውን ፍላጎት መሰረት እስካደረጉ ድረስ ጥራቱን የጠበቀ የቴ/ሙ/ት/ስ በመስጠት የሚሳተፉበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣ የልማት ድርጅቶች በትብብር ስልጠና እንዲሳተፉ ያበረታታል፣
- የቴ/ሙ/ት/ስ ሴቶች ፣ ልዩ ፍላጎት ያላቸው ወገኖች እና የገጠሩ ማህበረሰብ አባላት ተመጣጣኝ የተሳትፎ እድል ማግኘታቸውን ያረጋግጣል፣
- የውጤት ተኮር የቴ/ሙ/ት/ስ ትግበራ በጥናትና ምርምር እንዲጎለብት ያደርጋል፣
- የቴ/ሙ/ት/ስ ስርዓቱን ውጤታማነት ለማረጋገጥ የድህረ ስልጠና ክትትል ጥናቶችን ያካሂዳል፣
- የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ውል ይዋዋላል፣በስሙ ይከሳል ይከሰሳል፣
- አላማዎቹን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ህጋዊ ተግባሮችን ያከናውናል፣ የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

## የኤጀንሲው ድርጅታዊ መዋቅር እና የሰው ሀይል

11. የፌዴራል ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኤጀንሲ ተጠሪነቱ ለሳይንስ ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር ሆኖ በፌዴራል ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ዘርፍ ሚኒስቴር ዴኤታ በመመራት በስሩ በአንድ ዋና ዳይሬክተር እና በሶስት ም/ዋና ዳይሬክተር ተዋቅሯል:: በዋና ዳይሬክተር ስር ም/ዋና ዳይሬክተሩን ጨምሮ ሁለት ዳይሬክቶሬቶች፣ አንድ ልዩ አማካሪ ፅ/ቤትና፣ ሶስት ክፍሎች ያሉ ሲሆን የተቀሩት አራቱ ዳይሬክቶሮቶች በም/ዋና ዳይሬክተሩ ይመራሉ፡፡ ለኤጀንሲው በጠቅላላው 293 የሰው ሀይል ተፈቅዷል፡ ዋና ዳይሬክተሩን ጨምሮ በኤጀንሲው በጠቅላላ በስራ ላይ ያለው የሰው ሀይል እስከ 08 ሰኔ/2010 ዓ.ም የተፈቀደ የሥራ መደብ ብዛት 293 በሥራ ላይ ያሉ ሰራተኞች ድምር 192 ሰራተኞች ሲሆኑ ከነዚህ ውስጥ 55 (29%) ሴቶችና 137 (71%) ወንዶች ናቸው፡፡ የሰራተኞች ፕሮፋይል በትምህርት ደረጃ ሲታይ በኤም.ኤስ.ሲ/ኤም.ኤ ደረጃ ያሉ 21(11%)፣ የመጀመሪያ ዲግሪ ያላቸው 96(50%)፣ ኮሌጅ ዲፕሎማ/10+3/ 22(11%)፣ እንዲሁም የቀለም ትምህርት ያላቸው ሰራተኞች 53(28%) የሚይዝ መሆኑን ከሰው ሀብት ልማት አገልግሎት ከተሰበሰበ መረጃ ለማውቅ ተችሏል፡፡

## የፋይናንስ ምንጭ

12. የፌዴራል የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኤጀንሲ ሥራውን የሚያከናውነው ከመንግሥት በሚመደብለት መደበኛ እና ካፒታል በጀት ሲሆን በ2008 ፣ በ2009 እና በ2010 በጀት ዓመታት ለሚያከናውናቸው ተግባራት ማስፈጸሚያ እንደ ቅደም ተከተሉ በ2008 ብር 216,925,373.82፤ በ2009 ብር 193,332,540 እና በ2010 ብር 224,070,000 በድምሩ ብር 1,268,655,827.64 ሲሆን ከዚህ ውስጥ በ2008 ዓ.ም ብር 126,801,708.42 /58%/ ፣ በ2009 ዓ.ም ብር 146,789,948.12 (76%) እና በ2010ዓ.ም ብር 199,350,815.29 /89%/ በድምሩ ብር 945,884,943.66 (75%) ጥቅም ላይ አውሏል፡፡

## የፌ/ቴ/ሙ/ት/ስ ኤጀንሲ የአሰራር ስርዓት መግለጫ

/system description/

13. የፌዴራል ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኤጀንሲ ዓላማ አስፈፃሚ በአራት ዳይሮክተሬቶች የተዋቀሩ ሲሆኑ፤ የእነዚህም ዳይሮክቶሬቶች የስራ ፍሰት መግለጫ ከዚህ በታች ተዘርዝረዋል፡፡

## የሙያ ደረጃ ምደባ እና የሙያ ብቃት ምዘና ዳይሬክቶሬት

ይህ ዳይሬክቶሬት ሁለት ቡድኖችን የሚመራ ሲሆን የመጀመሪያው ቡድን ለስራ ፍሰቱ የሙያ ደረጃ ምደባ ስርዓት በመዘርጋት፣ የሙያ ደረጃ ሰነዶችን ለማዘጋጀት ምርጥ ተሞክሮዎችን መነሻ በማድረግና የስራ ገበያውን የባለሙያ ፍላጎት መሰረት ያደረጉ ሙያዎችን በመለየትና ደረጃ በማዘጋጀትና በማጸደቅ የሙያ ደረጃ ሰነዶችን ለተጠቃሚዎች በማድረስ/በማሰራጨት/፤ ለብቃት ምዘና መሳሪያ ዝግጅት መነሻ ሰነድ ለማዘጋጀት እንዲያስችል ለተጠቃሚዎች በአተገባበሩ ላይ የሙያ ምደባና ስርጭት ግምገማ በማካሄድ ድጋፍና ክትትል በማደረግ እና ግብረ መልስ በማሰባሰብ የስልጠና ጥራትን የማስጠበቅ ዋና ዋና ሀላፊነቶች ተሰጥቶታል፤፤

ሁለተኛው ቡድን የሙያ ብቃት ምዘና ስርዓት በመዘርጋት፣ የሙያ ብቃት ምዘና መሳሪያ በማዘጋጀት፣ መዛኞችን በማሰልጠንና ዕውቅና በመስጠት፣ የምዘና ሂደቱን በመከታተልና በመገምገም፣ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት በመስጠት፣ የምዘና መረጃ ባንክ በማደራጀትና በመጠቀም የሙያ ብቃት ምዘና ግምገማ የማካሄድ ዋና ዋና ሀላፊነቶች ተሰጥቶታል፤፤

## የሠልጣኝና የተቋማት ልማት አቅም ግንባታ ዳይሬክቶሬት

በዚህ ዳይሬክቶሬት ስር ሶስት ቡድኖች የተዋቀሩ ሲሆን የስራ ፍሰታቸውም እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

የመጀመሪያው ቡድን የመምህራን ልማት ቡድን ሲሆን ይህ ቡድን የቴ/ሙ/ት/ስ መምህራን ብቃት ማዕቀፍ፣ የቅድመ ስራ ስልጠናና ብቃት ማረጋገጫ እና ተከታታይ የሙያ ማሻሻያ ስርዓቶችን የክልሎችን አቅም የሚገነባና በስርዓቶቹ አተገባበር ላይ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ የመምህራን ልማት ተግባራት ግምገማ ያካሂዳል፡፡

ሁለተኛው የተቋማት አቅም ግንባታ ቡድን የተቋማት አመራር ብቃት፣የተቋማት ውጤታማ ሀብት አጠቃቀምና የጥራት ማኔጅመንት፣ የተቋማት ማስፋፋት እና የተቋማት ማስፋፋት ስርዓቶችን በመዘርጋት በአተገባበሩ ላይ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ምርጥ ተሞክሮዎችን በመዳሰስ በተቋማት ውጤታማ ሀብት አጠቃቀምና የጥራት ማኔጅመንት እና በተቋማት ብቃት አሰራር ስርዓት ላይ አማራጮችን በማቅረብ የተቋማት አቅም ግንባታ ተግባራት ላይ ግምገማ የማካሄድ ሃላፊነት ተሰጥቶታል፤፤

፤ሶስተኛው የሰልጣኝ ልማት ቡድን የስራ ገበያ ፍላጎት ዳሰሳ ስርዓት በመዘርጋትና ሀገራዊ የስራ ገበያ ፍላጎት ጥናት በማከናወን በጥናቱ መሰረት ለክልሎች አቅም በመገንባት ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ለስርዓተ-ትምህርትና የማስተማሪያ/ የማሰልጠኛና መማሪያ መሳሪያዎች/TTLM/CBLM/ ዝግጅት ላይ ስርዓት በመዘርጋት ማኑዋል በማዘጋጀት የክልሎችን አቅም በመገንባት በአተገባበሩ ላይ ግምገማ በማድረግ የማሻሻያ ሃሳብ ይሰጣል፡፡በተጨማሪም የትብብር ኩባንያ ውስጥ መደበኛና መደበኛ ያልሆነ የአሰለጣጠን ስርዓት በመዘርጋትና ስልጠና በመስጠት ተግባራዊነቱ ላይ ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፤፤ ለሰልጣኞች የምክርና የድጋፍ አገልግሎት ስርዓት ዘርግቶ ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፤፤

## የኢንደስትሪ ኤክስቴንሽንና ቴክኖሎጂ ሽግግር ዳይሬክቶሬት የስራ ሂደት መግለጫ

ይህ ዳይሬክቶሬት ከኤጀንሲው ዓላማ አስፈፃሚ ዋና የሥራ ክፍሎች አንዱ ሆኖ የተዋቀረ ሲሆን ዋና ተግባሩም የኢንዱስትሪዎችን የእሴት ሰንሰለት ትንተና ሥርዓት መዘርጋትና ትንተና ማካሄድ ፣ የምርጥ ቴክኖሎጂ ፍላጎትን የመለየትና የቴክኖሎጂ ምርጫ ማከናወን ፣ ምርጥ ቴክኖሎጂ የማቅረብና የቴክኖሎጂ ሽግግር ሥርዓት የመዘርጋት፣ የተሸጋገረን ቴክኖሎጂ ፋይዳ የማጥናት ፣ የጥቃቅንና አነሥተኛ ኢንተርፕራይዞች የሚጠበቅባቸውን ሀገራዊ ፋይዳ ለመጫወት እንዲችሉ አቅማቸውን መገንባት፣ የቴክኖሎጅ ሽግግር ተጠቃሚ የሚሆኑበትንና አስፈላጊውን የአቅም ግንባታና የምክር አገልግሎት የሚያገኙበትን የተቀናጀ የአሠራር ማዕቀፍ መዘርጋትና አፈፃፀሙን ማረጋገጥን በሃላፊነት ይዞ የሚሰራ ነው፡፡

## የምህንድስና ልህቀት ማዕከል ዳይሬክቶሬት የስራ ፍሰት መግለጫ

ይህ ዳይሬክቶሬት በስሩ ሁለት (ቴክኖሎጂ ሽግግር እና የብየዳ ስልጠና) ቡድኖች በመያዝ ተዋቅሯል፡፡ ዳይሬክቶሬቱ የተቋሙን ፖሊሲና ስትራቴጂክ ጉዳዮች ጋር ተያያዥነት ባላቸው ከፍተኛ የአዕምሮ ጥረት በሚጠይቁ የጥናትና የምርምር ስራዎች ወይም ከፍተኛ እውቀትና ችሎታ የሚጠይቁን የኤጀንሲውንና የማህበረሰቡን ችግሮች መፍታት የሚችሉ ጥናቶችን የማካሄድና የተለያዩ ፕሮጀክቶችን ስራ ላይ በማዋል አፈፃፀማቸውን በመገምገም የብየዳ ወርክሾፕ ስራዎችን በማቀድ፣ በማደራጀት፣ አቅጣጫ በመስጠት ይከታተላል እንዲሁም ብየዳ ማሽኖችና መሳሪዎች በተቀመጠላቸው የጥራት ደረጃዎች መሰረት መሆኑን በመከታተል ለወርክሾፑ የሚያስፈልጉ ጥሬ ዕቃዎችና ግብዓቶች በበቂ መጠን መኖራቸውን በማረጋገጥ በወቅቱ መገዛታቸውን ይከታተላል፡፡ እንዲሁም በወርክሾፖች ውስጥ የሴፍቲ ህጎችና ደንቦች መከበራቸውን በመከታተል ችግር ፈቺ የሆኑ ቴክኖሎጂዎችን ከእሴት ሰንሰለት ትንተና በመነሳት የመለየት ስራ በማስተባበር እንዲሰሩ ትዕዛዝ በማስተላለፍና በመምራት በተጨማሪም የተለያዩ ቴክኖሎጂዎችን በመቅዳትና በመምራት ዲዛይንና ዝርዝር ዶክመንቶች እንዲዘጋጁ በማስተባበር ለጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት እንዲሸጋገሩ ማደረግ ይጠበቅበታል፡፡

### ኦዲቱ ዓላማ

14. የክዋኔ ኦዲቱ ዓላማ የሙያ ደረጃ ምደባና ብቃት ምዘና እና የተቋማት ልማት አቅም ግንባታ አፈፃፀምን ኢኮኖሚያዊ፣ቀልጣፋና ዉጤታማ መሆናቸውን በመገምገም በስራው ወቅት የተከሰቱ የአሰራር ችግሮች ካሉ መንስኤያቸውን በመለየት ችግሮቹን ለማስወገድ ወይም ለመቀነስ የሚያስችሉ የማሻሻያ ሃሳቦችን በማቅረብ ተጠያቂነትን ለማስፈን ነው፡፡

### የኦዲቱ ወሰንና ዘዴ

15. ኦዲቱ የሚከናወነው በመንግሥት መ/ቤቶች ላይ የክዋኔ ኦዲትን ለማካሄድ ለመሥሪያ ቤታችን በአዋጅ ቁጥር 982/2008 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ነው፡፡ኦዲቱ የሚሸፍነው ከ2008 በጀት ዓመት እስከ 2010 በጀት አመት ድረስ ባለው ጊዜ የተሰራውን ሥራ ነው፡፡ ኦዲቱ በዋናነት የሚከናወነው በፌዴራል ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኤጀንሲ ሲሆን፤ የተለያዩ አግባብነት ያላቸው

ማስረጃዎችን በመከለስ ፣ ለሚመለከታቸው የኤጀንሲው የሥራ ኃላፊዎች ቃለ-መጠይቅ በማቅረብ፣ በተመረጡ የክልል የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ቢሮዎች/ኤጀንሲዎች የብቃት ምዘና ማዕከላት እንዲሁም በተለያዩ ሴክተሮች ያሉትን በፌዴራል ደረጃ ፈቃድ የተሰጣቸው የግል እና የመንግስት ተቋማት እና ሌሎች ባለድርሻ አካላትን በናሙና በመምረጥ ለተለያዩ የስራ ኃላፊዎች ቃለ-መጠይቅ በማቅረብ እና ማስረጃዎችን በመሰብሰብ እና በመከለስ ነው፡፡

በዚህም መሠረት ከአስራ አንዱ የክልል ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ቢሮዎች/ኤጀንሲዎች እና የብቃት ምዘና ማዕከላት ውስጥ ዘጠኝ (አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የቴ/ሙ/ት/ስ/ቢሮ ፣ የአ.አ ከተማ አስተዳደር የብቃት ማዕከል፣ የኦሮሚያ ክልል የቴ/ሙ/ት/ስ/ቢሮ፣ የኦሮሚያ ክልል የብቃት ማዕከል፣ ደቡብ ክልል የቴ/ሙ/ት/ስ/ቢሮ ፣ ለደቡብ ክልል የብቃት ምዘና ማዕከል፣ ለአፋር ክልል የቴ/ሙ/ት/ስ/ቢሮ፣ ለአማራ ክልል የቴ/ሙ/ት/ስ/ቢሮ ፣ ለአማራ ክልል የብቃት ማዕከል)፣ በተለያዩ ስምንት ሴክተር መ/ቤቶች ማለትም (በከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር፣ ብረታ ብረትና ኢንዳስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ፣ አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ልማት ኤጀንሲ ፣ ግብርና ሚኒስቴር ፣ ባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ፣ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር፣ ለፌደራል የከተሞችና የሥራ ዕድል ፈጠራ እና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ ፣ ቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት) እንዲሁም በስምንት የመንግስት ተቋማት ማለትም (ምስራቅ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ፣ ተግባረ ዕድ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ፣ ልደታ ማኑፋክቸሪንግ ኮሌጅ ፣ አዳማ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ፣ የሻሸመኔ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ፣ ለሀዋሳ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ፣ ለወ/ሮ ስሂን ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ፣ ለሰመራ ጤና ሳይንስ ኮሌጅ በኦዲቱ ተሸፍነዋል፤፤ከዚህ በተጨማሪ ከ ሶስት የግል ተቋማት ለሻሸመኔ አፍሪካ ቤዛ ቴ/ሙ/ ማሰልጠኛ ኮሌጅ፣ ለሀዋሳ አትላስ የቢዝነስና ቴክኖሎጂ ማሰልጠኛ ኮሌጅ ፣ በባህርዳር ለሃይላንድ ኮሌጅ እንዲሁም ለሁለት መንግስታዊ ያልሆኑ ማሰልጠኛ ተቋማት ማለትም ለፕሮጀክት-ኢ ፣ ለኤስ ኦ ኤስ የቴ/ሙ/ት/ማ/ ተቋም ፣ በአጠቃላይ የኦዲት ቡድኑ በሙያ ደረጃ ምደባና ብቃት ምዘና እንዲሁም የአሰልጣኝ ልማት እና የተቋማት አቅም ግንባታ አፈፃፀም ዙሪያ በአካል በመገኘት የተለያዩ ማስረጃዎችን በመከለስ እና በመሰብሰብ፣ እንዲሁም ለሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ቃለ-መጠይቅ በማቅረብ ማስረጃወች በመሰብሰብና በመተንተን ኦዲቱ ተከናውኗል፡፡

## ለክዋኔ ኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት አካባቢ

16. ለክዋኔ ኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት አካባቢ የሙ-ያ ደረጃ ምደባ ፣ ብቃት ምዘና እንዲሁም የአሰልጣኝ ልማት እና የተቋማት አቅም ግንባታ አፈፃፀም ኢኮኖሚያዊ ፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ መሆኑን መገምገም የሚል ነው፡፡

## የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች

17. ከላይ በተለየው የኦዲት አካባቢ ሥር ሦስት የኦዲት ትኩረት አቅጣጫዎች /Audit Issues/ ተለይተዋል፡፡ እነሱም

I. ኤጀንሲው በቴክኒክ እና ሙ-ያ ትምህርትና ሥልጠና ብቁና ጥራቱን የጠበቀ የሰው ኃይል ለማፍራት ኢኮኖሚያዊ ፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ የሙ-ያ ደረጃ ምደባና የሙ-ያ ብቃት ምዘና ስርዓት የዘረጋ እና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን መገምገም፤

II. ኤጀንሲው በሃገር አቀፍ ደረጃ የቴክኒክ እና ሙ-ያ ትምህርት ስልጠና አሰልጣኞችን ፣ ተቋማትን እና ሰልጣኞችን አቅም ለመገንባት ድጋፍ እና ክትትል ለማድረግ የሚያስችል ኢኮኖሚያዊ ፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ የአሰራር ስርአት የዘረጋ እና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን መገምገም፤

III. ኤጀንሲው ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት መስራቱን እና ቀልጣፋና ውጤታማ የሆነ የመረጃ ልውውጥ ስርአት የዘረጋ እና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን መገምገም፤

## የኦዲቱ መመዘኛ መስፈርቶች

18. ለተመረጡ ሶስት የኦዲት ዋና ዋና የትኩረት አቅጣጫዎችን ለመመዘን የሚረዱ 31 የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative criteria) ተዘጋጅተዋል፡፡ በተዘጋጁት የትኩረት አቅጣጫዎች እና የመመዘኛ መስፈርቶች ላይም የኤጀንሲው ኃላፊዎች አስተያየታቸውን እንዲሰጡበት ቀርቦላቸው አስተያየት ሰጥተውበታል፡፡ የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶቹ በአባሪ 1 ተያይዘዋል፡፡ የኦዲት የመመዘኛ መስፈርቶችን ለማዘጋጀት መሰረት ከሆኑት ዋና ዋናዎቹ የኤጀንሲው ማቋቋሚያ አዋጅ ፣ ደንብ ፣ መመሪያዎች፣ የቴ/ሙ/ት/ስ ስትራቴጂክ ዕቅድ እና ዓመታዊ የዕቅድ እና የክንውን ሪፖርቶች (ከ2008-2010ዓ.ም.) እና የተለያዩ አግባብነት ያላቸው ሰነዶች ናቸው፡

# ክፍል ሁለት

## የኦዲት ግኝቶች

**የሙያ ደረጃ ዝግጅት እና ክለሳን በተመለከተ፤**

19. ኤጀንሲው በደንብ ቁጥር 199/2203 አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 4 መሠረት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የስራ ገበያውን ፍላጎት መሰረት ያደረጉ የሙያ ደረጃዎችን ሊያዘጋጅ ፣ ሊከልስ እና በአግባቡ በስራ ላይ መዋላቸውን ሊከታተል ይገባል፡፡

20. ይሁን እንጅ የኦዲት ቡድኑ ጉዳዩን አስመልክቶ ከፌደራል ቴ/ሙ/ት/ስ ኤጀንሲ የስራ ሃላፊወች ፣ በናሙና ተመርጠው ከታዩ የክልል የቴ/ሙ/ት/ስ/ ቢሮዎች እና ከማሰልጠኛ ተቋማት የስራ ሃላፊወች ጋር ባካሄዳቸው ቃለ መጠይቆች እና ቀርበው በተከለሱ ሰነዶች መሰረት ኤጀንሲው የስራ ገበያውን ፍላጎት መሰረት ያደረጉ የሙያ ደረጃዎችን በተሟላ ሁኔታና በወቅቱ ያላዘጋጀ እና ያልከለሰ መሆኑን እንዲሁም ያዘጋጃቸውንና የከለሳቸውን ደረጃወችም ለሴክተር መ/ቤቶች ፣ ለክልል ቢሮዎች እና ለምዘና ማዕከላት እና ለተቋማት መድረሳቸውን እና በአግባቡ ስራ ላይ መዋላቸውን አለመከታተሉን በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡ በኦዲቱ ወቅት ከታዩ ችግሮች ለአብነት እንደሚመከተለው ቀርቧል፦

- ኤጀንሲው በገበያ ተፈላጊ ሆነው የሙያ ደረጃ ያላዘጋጀላቸው ሙያዎች ለአብነትም፦ በወለል ንጣፍ ምርት Terrazzo Tiles production ፣ በልብስ ቁልፍ ማምረት ሥራ ፣ በጠመኔ ፣ በ airfram technician level III እና በወረቀትና ሰበዝ በሚሰሩ ጌጣጌጦች ፣ በሚስማር ፣ በአጥር ሽቦ ማምረት እና በሳሙና ጌጣጌጥ እና ፕላስቲክ) ሙያዎች መኖራቸው ፡፡
- ለኦሮሚያ የቴ/ሙ/ት/ስ/ቢሮ እና የብቃት ማረጋገጫ ኤጀንሲ ፣ ለአፋር እና ደቡብ ክልል የቴ/ሙ/ት/ስ/ቢሮዎች ፣ ለአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር ብቃት ምዘና ማዕከል እና የማሰልጠኛ ተቋማት ፦ ለሻሸመኔ ለአፍሪካ ቤዛ ኮሌጅ ፣ ለሀዋሳ አትላስ የቢዝነስ ቴክኖሌጂ ኮሌጅ እና ለኤስ ኦ ኤስ የቴ/ሙ/ት/ስ/ ኮሌጅ ፣ ለአዳማ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ፣ ለሰመራ ጤና ሳይንስ ኮሌጅ፣ ለወ/ሮ ስኂን ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ እና ለልደታ ማኒፋክቸሪንግ ኮሌጅ የስራ ሃላፊዎች ከቀረበ

ቃለ መጠይቅ የሙ.ያ ደረጃዎች ሲከለሱ ለኮሌጆች ወቅቱን ጠብቆ የማይላክበት ሁኔታ መኖሩን ፣ የሙ.ያ ደረጃ ደብዳቤ ሳይጻፍ በሲዲ ብቻ እንደሚላክና ፎርማሊቲ የሚጎድለው መሆኑን ፣ ሙ.ያ ደረጃዎች ተከልሰው ሲላኩ ስልጠና ከተጀመረ በኋላ የሚደርሱበት ሁኔታ መኖሩ ፣ በተከለሰው የሙ.ያ ደረጃ ወደ ስራ ስለመገባቱ ክትትል እንደማይደረግ ፣ በፌዴራሉ ኤጀንሲ የሙ.ያ ደረጃዎች ከ 3-5 ዓመት ባለው ጊዜ ውስጥ መከለስ ቢኖርባቸውም ከተባለው የግዜ ገደብ ቀድሞ የሚከለስበት ሁኔታ በመኖሩ የስልጠና ጥራት ችግር እንደሚፈጥር እና ተግባራዊነቱን አስመልክቶ በሚዘጋጁ የውይይት መድረኮች ላይ ውይይት ከማድረግ ያለፈ በቂ ድጋፍ እና ክትትል ያላደረገ መሆኑን ገልጸዋል ::

- እንዲሁም ለኦዲት ቡድኑ በፌደራል ቴ/ሙ/ት/ስ ኤጀንሲ ፣ በክልል የቴ/ሙ/ት/ስ/ቢሮዎች እና በማሰልጠኛ ተቋማት ቀርበው ከተከለሱ ሰነዶች በአማራ ክልል ሳይከለሱ ለረጅም ግዜ የቆዩ ሙ.ያወች መኖራቸው ለአብነት፡- በIT (ኢንፎርሜሽ ቴክኖሎጂ), building constraction (ሕንፃ ግንባታ), በ health and manufacturing እና በሜታልና እውቶ ሙ.ያዎች ላይ ክለሳ አለመደረጉን ፣ በሪፍት ቫሊ ዩኒቨርሰቲ ኮሌጅ ፣ በቴክኖ ብሬይን ኮሌጅ ፣ በኪያሜድ ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ከሙ.ያ ደረጃዎች ውስጥ ወቅታዊ የሆኑትን እና ያልሆኑትን ፣ የተከለሱና ያልተከሱትን ገላጭ በሆነ መልኩ በሙ.ያ አይነት ፣ በደረጃ ፣ በዓመተ ምህረት ያልተለዩ መሆኑን ፣ በትግራይ ክልል ብቃት ኤጀንሲ ለፌ/ቴ/ሙ/ት/ስ ኤጀንሲ በተፃፈ ደብዳቤ አዲስ የተዘጋጁ ሙ.ያዎች እና የሙ.ያ ደረጃዎች ተልከው ነገር ግን አፈጻጸማቸው ከመቼ ጀምሮ እነደሆነ እና የትኞቹ ሰልጣኞችን እንደሚመለከት በግልጽ የማይጠቁምበት ሁኔታ መኖሩን ለማወቅ ተችሏል፡፡

21. ስለ ጉዳዩ የፌ/ቴ/ሙ/ት/ስ/ ኤጀንሲ የስራ ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው የነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት መልስ ችግሮቹ መኖራቸውን ተቀብለው ለወደፊቱ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር መድረክ በማዘጋጀት እንደሚፈቱት በመግለፅ የሙ.ያ ደረጃዎች የሚዘጋጁት ከኢንዳስትሪው ጋር በመተባበር መሆኑን ነገር ግን በዘርፉ የመሪ መ/ቤት ባለቤቶች ጥያቄ ባለማቅረባቸው የሙ.ያ ደረጃ ምደባ ሥራ ሊከናወን አለመቻሉን በሌላ በኩል የአብዛኛው ዘርፍ መሪ መ/ቤቶች የሙ.ያ ደረጃ ሲላክላቸው በአግባቡ ፈትሸው የማይልኩ መሆኑን እንዲሁም

ባልተፈቀደ ሙ.ያ ደረጃ ሰልጣኞችን ተቀብሎ የማሰልጠን ስራ በአንዳንድ ተቋማት ላይ እንደሚታይ ግልፅ ቢሆንም የክትትል ስራ የሚሰራ መሆኑን ፡

22. እንዲሁም የሙ.ያ ደረጃ ክለሳን በተመለከተ የቴክኖሎጂ ለውጥን ተከትሎ የሚከናዎን በመሆኑ በሚከለስበት ወቅት ለሚመለከተው አካል እንደሚያሳውቁ እና የተከለሰውን የሙ.ያ ደረጃም የሚልኩ መሆኑን ነገር ግን ወደ ክልሎች ከወረደ በኋላ በቀድሞው ወይም ባልተከለሰው የሙ.ያ ደረጃ የመስራት ችግር መኖሩን ገልፀዋል፡፡ እንዲሁም የሙ.ያ ደረጃ ክለሳም ሆነ እንደ አዲስ ማዘጋጀት በኢንዱስትሪው ፍላጎት መሰረት ብቻ የሚከናወን ሲሆን ከላይ የተገለጹት ሦስቱም ሙ.ያዎች (manufacturing, health and manufacturing እና constraction ከ2009 ዓ.ም. ጀምሮ በኢንዱትሪው ወቅታዊ ፍላጎት መሰረት ተከልሰው በዘርፉ ለማስጸደቅ የተላኩ መሆኑን እና ፀድቀው ሲመጡ ስራ ላይ እንዲውሉ የማድረግ ስራ የሚያከናውኑ መሆኑን፡ ክልሎች የሙ.ያ ደረጃ በረቂቅ ደረጃ ሲዘጋጅ ሰነዶቹን ከዓውደ-ጥናት ተሳትፎ በኋላ በፍላሽ ወስደው ወደ ስልጠና የሚያስገቡበት ሁኔታ በመኖሩ በኤጅንሲው ጥራታቸው ተፈትሾ በዘርፍ የጸደቁት በህጋዊ ደብዳቤ ሲላክላቸው ግራ መጋባት እየተፈጠረባቸው በመሆኑ ክልሎች የተከለሱ የሙ.ያ ደረጃዎችን በደብዳቤ በህጋዊ መልኩ ከፌደራል ኤጀንሲ እስካልተላከላቸው ድረስ ስልጠና መስጠት እንደማይችሉ የአሰራር ስርአት ያስቀመጡ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

23. የፌ/ቴ/ሙ/ት/ስ/ ኤጀንሲ የስራ ኃላፊዎች ኦዲቱ ረቂቅ ሪፖርት ላይ በተሰጠ አስተያየት ሳይከለሱ ለረዥም ጊዜያት የቆዩ የሙ.ያ ደረጃዎች እንዳሉና በአሁኑ ጊዜ ክትትል በማድረግ መረጃውን በማጥራት በየዘርፉ ተከልሰው ያለቁ የሙ.ያ ደረጃዎችን ለሚመለከታቸው የክልል ቴ/ሙ/ት/ስ/ አካላት መላካቸውን፣ ተከልሰው ለሚመለከተው አካል በወቅቱ ያለመላክና ግልጽ የአጠቃቀም ማብራሪያ ችግሩ እንዳለ ገልጸው፣ በአሁኑ ጊዜ ለሁሉም ክልሎች የተከለሱ ሙ.ያ ደረጃዎችን አስመልክቶ ዝርዝር ማብራሪያ እንደተሰጠ፣ በተጨማሪም የሙ.ያ ደረጃን አስመልክቶ የሚደረገው ክትትል ኤጀንሲው ካለው የሰው ሃይል እጥረት የመነጨ በቂ ክትትል እየተደረገ እንዳልሆነ ነገር ግን ባለው ውሱን የሰው ሃይል ክልሎችን ለመደገፍ ጥረት እንደተደረገ እና የክዋኔ ኦዲቱ ሪፖርት ከቀረበ ጊዜ ጀምሮ ክልሎችን በመጥራት በችግሮቹ አፈታት ዙሪያ ስምምነት ተደርጎ ቸክ ሊስት ተዘጋጅቶ ወደ ዕቅድ በመቀየር ለክልሎች በመላክ ችግሮች እየተፈቱ እንደሚገኙ ተገልጸዋል፡፡

24. የፌ/ቴ/ሙ/ት/ስ/ ኤጀንሲ የስራ ኃላፊዎች በኦዲቱ ሪፖርት መውጫ ስብሰባ ላይ በተሰጠ ምላሽ ኦዲት ግኝቱን መቀበላቸው ገልፀው ከኦዲቱ ነባራዊ ሁኔታ ተነስተው ወደ ስራ መግባታቸውን ገልፀዋል፡፡

25. ኤጀንሲው የስራ ገበያውን ፍላጎት መሰረት ያደረጉ የሙያ ደረጃዎችን ከሚለከታቸው አካላት ጋር በመሆን በተሟላ ሁኔታ አለማዘጋጀቱ ፣ የሙያ ደረጃዎች የሚከለሱበትን ሁኔታ እና ግዜ አሰቀምጦ አለመከለሱ ፣ የተዘጋጁትና የተከለሱት የሙያ ደረጃዎችም ለሚመለከታቸው ተቋማት በወቅቱ ስለመድረሳቸውና በአግባቡ ስራ ላይ ስለመዋላቸው በቂ ክትትል አለማድረጉ ማሰልጠኛ ተቋማት የስራ ገበያውን ፍላጎት መሰረት ባደረጉ እና ወቅታዊ በሆኑ የሙያ ደረጃዎች ስልጠና እንዳይሰጡ እና ሰልጣኞችም ውጤታማ እንዳይሆኑ ያደርጋል፡፡

**የስልጠና መሳሪያዎች** (Teaching and Training learning material /TTLM / and Competency biased learning material /CBLM/ **መዘጋጀታቸውን እና ተግባራዊ መደረጋቸውን በተመለከተ**:

26. ኤጀንሲው በደንብ ቁጥር 199/2003 አንቀፅ 6 ንዑስ አንቀጽ 5 መሠረት ፣ ስርዓተ - ትምህርቶች እና የስልጠና መሳሪያዎች (Teaching and Training learning material /TTLM / እና Competency biased learning material /CBLM/ መዘጋጀታቸውን እና ተግባራዊ መደረጋቸውን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

27. ይሁን እንጂ ጉዳዩን አስመልክቶ በኦዲት ቡድኑ በናሙና ተመርጠው በታዩ በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር፣ በአፋር፣ በኦሮሚያ፣ በደቡብ እና በአማራ ክልል የቴ/ሙ/ት/ስ/ ቢሮዎች እንዲሁም ለሰመራ ጤና ሳይንስ ኮሌጅ፣ ለሀዋሳ የአትላስ የቢዝነስ እና ቴክኖሎጂ ማሰልጠኛ ኮሌጅ እና ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ፣ ለሻሸመኔ የአፍሪካ ቤዛ ኮሌጅ ፣ ለወ/ሮ ስ'ኒን ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ፣ ለአዲስ አበባ ተግባረ ዕድ ፣ ለምስራቅ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ፣ ለልደታ ማኑፋክቸሪንግ ኮሌጅ እና ለአዳማ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ የስራ ኃላፊዎች ኤጀንሲው ስርዓተ-ትምህርቶች እና የስልጠና መሳሪያዎች (TTLM/CBLM) መዘጋጀታቸውን እና ተግባራዊ መደረጋቸውን ማረጋገጡን በተመለከተ የኦዲት ቡድኑ ላቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ ኤጀንሲው ለተቋማት ድጋፍና ክትትል ሲያደርግ የቴክኒክ እና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ስርዓተ-ትምህርቶች እና የስልጠና መሳሪያዎች መዘጋጀታቸውን ከማየት ባለፈ ተግባራዊ ስለመደረጋቸው ፣ ወቅታዊነት ያላቸው ስለመሆኑ እና ጥራት ያለቸው ስለመሆኑ በጥልቀት የማያረጋግጥ መሆኑን ገልጸው በመሆኑም በስርዓተ-ትምህርቶች እና የስልጠና መሳሪያዎች /CBLM / TTLM/ ላይ የጥራት ችግር መኖሩን ፣ የማሰልጠኛ መሳሪያዎች ያልተሟሉበት ሁኔታ መኖሩን እና በማሰልጠኛ

ተቋማት ወቅታዊ የሙያ ደረጃን መሰረት ያደረገ TTLM/CBLM ዝግጅት ላይ ወጥ የሆነ አዘገጃጀት አለመኖሩን ገልፀዋል፡፡

28. ከዚህ በተጨማሪ በኦዲቱ ወቅት ለኦዲት ቡድኑ ቀርበው ከተከለሱ ሰነዶች የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡- በደቡብ ክልል በማሰልጠኛ ተቋማት የደረጃ 3 እና 4 ስልጠናው የሚሰጥበት የአሰለጣጠን ስልት /Mode of delivery/ን ያካተተ እና በሙያ ምደባው መሠረት የተዘጋጀ የመማር ማስተማር ማሰልጠኛ መሣሪያ /TTLM/ ተዘጋጅቶ ስራ ላይ እንዲውል አለመደረጉን እንዲሁም አሰልጣኞች ስልጠና የሚሰጡበት መመሪያ በተሟላ ደረጃ አለመኖሩን ለአብነት፤- ለ Teaching guide; Learning Guide and Assessment Packet Session plan; List of competencies; etc ፣ ስርዓተ-ትምህርቶች እና የስልጠና መሳሪያዎች /CBLM እና TTLM/ ያላዘጋጁና የማሰልጠኛ መሳሪያዎች ያላሟሉ ተቋማት መኖራቸውን ለማወቅ ተችሏል፡፡

29. ጉዳዩን አስመልክቶ በኦዲት ቡድኑ ተዘጋጅቶ ለቀረበው የነባራዊ ሁኔታ መግለጫ የሚመለከታቸው የኤጀንሲው የስራ ኃላፊዎች በሰጡት መልስ ለክልሎች ድጋፍ እና ክትትል በማድረግ ችግሮችን ለይቶ የመፍትሄ አቅጣጫወችን በመስጠት ከክልሎች ጋር በቅንጅት ከመስራት ባሻገር ችግሩን ሙሉ በሙሉ ለመፍታት መንግስት የትምህርት እና ስልጠና ፍኖተ-ካርታ በማዘጋጀት ላይ እንደሚገኝ ገልፀዋል፡፡

30. የፌ/ቴ/ሙ/ት/ስ/ ኤጀንሲ የስራ ኃላፊዎች ኦዲቱ ረቂቅ ሪፖርት ላይ በተሰጠ አስተያየት ስርዓተ ትምህርቶችንና የስልጠና መሳሪያዎችን አስመልክቶ የጥራት ክፍተት እንዳለና እንደመፍትሄም በክልል ደረጃ የተሻሉ ባለሙያዎችን ከየኮሌጆቹ በማሰባሰብ ካሪክለምና ቲቲኤልኤም እንዲዘጋጅ ጊዜያዊ መፍትሄ እንደተቀመጠና በአብዛኛዎቹ ክልሎች እየተሰራበት እንደሆነና ዘላቂ መፍትሄ ለመስጠት በተማከለ ደረጃ እንዲዘጋጅ ኤጀንሲው የውሳኔ ሃሳብ እንዳቀረበ ተገልጿል፡፡

31. የፌ/ቴ/ሙ/ት/ስ/ ኤጀንሲ የስራ ኃላፊዎች ኦዲቱ ሪፖርት መውጫ ስብሰባ ላይ በተሰጠ ምላሽ ኦዲት ግኝቱ መቀበላቸው ገልፀው ከኦዲቱ ነባራዊ ሁኔታ ተነስተው ወደ ስራ መግባታቸውን ገልፀዋል፡፡

32. በመሆኑም ኤጀንሲው ስርዓተ - ትምህርቶች እና የስልጠና መሳሪያዎች (Teaching and Training learning material እና /Competency based learning material) መዘጋጀታቸውን እና ተግባራዊ መደረጋቸውን በአግባቡ አለማረጋገጡ እንዲሁም

የተዘጋጁትም የጥራት ችግር ያለባቸው መሆኑ ሰልጣኞች ተገቢውን ክህሎትና ዕውቀት በሚያስጨብጥ መልኩ ስልጠና ለማግኘት እንዳይችሉ እና የክህሎት ክፍትት እንዲኖር ያደርጋል፡፡

**ኤጀንሲው የምዘና መሳሪያዎች ስለማዘጋጀቱ እና**

**አፈፃፀማቸውን ስለመከታተሉ በተመለከተ**

33. በደንብ ቁጥር 199/2003 አንቀፅ 6 ንዑስ አንቀጽ 5 የሙያ ብቃት ምዘና ማዕከላት ዕውቅና አሰጣጥ መመሪያ ገጽ 8 መሰረት ኤጀንሲው በፀደቁና በተከለሱ የሙያ ደረጃዎች ላይ ተመስርቶ የምዘና መሳሪያዎች ሊያዘጋጅ ፣ ሊያሰራጭ እና ለአተገባበሩም አስፈላጊውን ድጋፍና ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡

34. ኤጀንሲው አዋጅ ቁጥር 954/2008ን መሰረት አድረጎ በተዘጋጀው የሙያ ብቃት ምዘና ማዕከላት ዕውቅና አሰጣጥ መመሪያ መሰረት የሴክቴር መ/ቤቶች እና ኢንዳስትሪዎችን በማስተባበር ከሀገራዊ የሙያ ደረጃ ሰነድ በመነሳት የሙያ ብቃት ምዘና መሳርያዎችን በማዘጋጀት ፣ የተዘጋጁትን በማጸደቅ ፤ የፀደቁትንም ለሁሉም ማእከላት እንዲሰራጩ ማድረጉንና የተሰራጩትም ሚስጥራቸው ተጠብቆ ለምዘና ተግባር መዋላቸውን ስለመከታተሉ ኦዲት ሲደረግ፡

35. በኦዲቱ ወቅት ለኦዲት ቡድኑ ቀርበው ከተከለሱ ሰነዶች የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል ኤጀንሲው በፀደቁና በተከለሱ የሙያ ደረጃዎች ላይ ተመስርቶ **የሙያ ብቃት ምዘና መሳሪያ** ያላዘጋጀላቸው ሙያዎች መኖራቸው ለአብነት አዲስ አበባ ምስራቅ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ በመንገድ ስራ በደረጃ አንድ ምዘና ቢዘጋጅም ከደረጃ አንድ በላይ የምዘና መሳርያ የሌለ መሆኑን ፣ ከኤጀንሲው ደብዳቤዎች የተገኙ ለገጸ ምድር ማዕድን ማምረት ስራ /surface mining/ ደረጃ ll , lll, እና lv ፣ ለከርሰ ምድር ማአድን ስራ (underground mining) ደረጃ ll, እና lll. ፣ ለቢዝነስ እና ንግድ አገልግሎት /Business & trade service/ ደረጃ l, እና ll, ፣ ለየቢዝነስ ስራ አመራር አገልግሎት /bussines management service/ ደረጃ lll, ፣ For bussines governance service ደረጃ lv ፣ ለየማስታወቅያ ስራ አመራር /Advertizing management/ ደረጃ v ፣ ለአለም አቀፍ ንግድ /International trade/ ደረጃ lll, እና lv, International bussines ደረጃ v ፣ ለጅምላ ሽያጭ /whole selling/ ደረጃ lll, ፣ ለጅምላ ሽያጭ ተቆጣጣሪ /whole selling supervision/ ደረጃ lv ፣ ለጅምላ ሽያጭ

ስራ አመራር /whole selling management/ ደረጃ v ፣ retailing supervision ደረጃ lv እና retailing management ደረጃ v. የሙያ ብቃት ምዘና መሳሪያ ያልተዘጋጀላቸው መሆኑን እንዲሁም የኤጀንሲው ሙያ ደረጃና ብቃት ምዘና ዳይሬክቶሬት ለ25 ሙያዎች የምዘና መሳርያ ለማዘጋጀት አቅዶ ከታቀደው ውስጥ 4 የአግሮ ፕሮሰሲግ ሙያዎች ብቻ መዘጋጀታቸውን ለማወቅ ተችሏል፤፤

36. በተዘጋጀቱም ምዘና መሳርያዎች ላይ የጥራት መጓደል እና የእጥረት ችግር መኖሩን፡ ለአብነት ፡- በአማራ ክልል ህክምና ላብራቶሪ ደረጃ 3 የዕውቀት ምዘና አንድ ቨርዥን ላይ መልስ የሚሳሳትበት ሁኔታመኖሩ ፣ የንድፈ ሃሳብ ምዘና ላይ የተሟላ ጥያቄ ያለመኖር ፣ ሰርቬይንግ ደረጃ 4 (V-2) ላይ መልስ መስጫ ኖሮ ነገር ግን ጥያቄው የሌለ መሆኑ /ኮምበልቻ ፖሊ ቴክኖሌጂ ኮሌጅ  እና ባህር ዳር ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ  የዕውቀት ምዘናው ላይ ስካን ተደረጎ የገባው ድሮይንግ የማይነበብ መሆኑ፣ በፋርማሲ ቴክኖሎጂ ደረጃ 4 አዛምድ ላይ መልስ ያልተሰራለት መሆኑን እንዲሁም በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ማዕከል በአውቶ መካኒክ እና ኤሌክትሪክ ዘርፍ ለእያንዳንዳቸው 10  የምዘና መሳሪያዎች ቨርዥን ለማዘጋጀት ታቅዶ አፈጻጸሙ 4/ 40% ብቻ መሆኑ፣  በሌላ በኩል የሙያ ደረጃ ላይ ስልጠና እና ምዘና ያለመጣጣም ችግር መኖሩ፡

37. እንዲሁም በኦዲት ቡድኑ በናሙና ለተመረጡ ለአማራ ክልል ቴ/ሙ/ት/ስ/ቢሮ እና የሙያ ደረጃ ምደባና ብቃት ምዘና ማዕከል እና ወ/ሮ ስኂን ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ፣ ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የቴ/ሙ/ት/ስ/ቢሮ  ፣ ለተግባረ ዕድ ፣ ለምስራቅ ፖሊ ቴክኖሎጂ ኮሌጅ እና ለልደታ ማኑፋክቸሪንግ ኮሌጅ ፣ ለደቡብ ክልል የቴ/ሙ/ት/ስ/ቢሮ ፣  ለሻሼመኔ አፍሪካ ቤዛ ኮሌጅ ፣ ለአፋር ክልል የቴ/ሙ/ት/ስ/ቢሮ ጉዳዩ ለሚመለከታቸው የስራ ሃላፊዎች የኦዲት ቡድኑ ላቀረባቸው ቃለ መጠይቆች በሰጡት መልስ በደረጃ V የምዘና መሳርያ የሌላቻው ሙያዎች መኖራቸውን ለአብነት፡-textile, water constraction management ፣ በብቃት ማዕከላት በኩል ያልተከለሰ የምዘና መሳሪያዎችን የመጠቀም ችግር መኖሩን፡ የምዘና መሳሪያዎች የሚዘገዩበት ሁኔታ መኖሩን ፣ የምዘና ማዕከላት ለምዘና መሳሪያዎች ሚስጥራዊነት ተገቢውን ጥበቃ የማይደረጉበት ሁኔታ መኖሩን እና ኤጀንሲው በቂ ድጋፍና ክትትል የማይደረግ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

38. ጉዳዩ የሚመለከታቸው የኤጀንሲው የስራ ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ ተዘጋጅቶ ለቀረበው የነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት መልስ የዘርፍ መሪ መ/ቤቶች ስራውን በባለቤትነት ባለመያዛቸው ለዝግጅት የሚመጡ ባለሙያዎች የአቅም ክፍተት ያለባቸው መሆኑን ገልጸው የምዘና መሳሪያ የጥራት ችግር ቢኖርም ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻለ መሆኑን ፣ ክፍተት ያለበትን የምዘና መሳሪያ ለማስተካከል የሚቻል ቢሆንም ችግሩ የባለሙያዎች የአቅም ውስንነት በመሆኑ በታህሳስ 2011 ዓ.ም ከክልል ባለሙያዎች ጋር በተደረገው ሰልጠና እና ውይይት ለችግሩ መፍትሄ በማግኘት ላይ መግባባት ላይ መድረሳቸውን እና የምዘና መሳርያ እጥረት ችግርን ለመፍታት ከኢንዱስትሪው እና ከብቃት ማዕከላት ጋር በጋራ እየሰሩ እንደሚገኙ ገልፀዋል፡፡

39. ጉዳዩ የሚመለከታቸው የኤጀንሲው የስራ ኃላፊዎች በክዋኔ ኦዲቱ የረቂቅ ሪፖርት እና በመውጫ ስብሰባ ላይ በተሰጡት መልስ በኦዲቱ ነባራዊ ሁኔታ ላይ ተመስርተው ኢንዱስትሪውን በማሳመንና በማንቀሳቀስ የምዘና መሳሪያዎች እንዲከለሱ ማድረግ እንደተቻለና ስራው ተጠናክሮ እንደቀጠለ፣ የምዘና መሳሪያን አስመልክቶ ሪፖርቱ ላይ የተጠቀሱት ችግሮች በኢንዳስትሪዎች የአመለካከት ችግር ፈቃደኛ ባለመሆናቸው ችግሩ እንደተከሰተ፣ በተዘጋጁት የምዘና መሳሪያዎች ላይ የሚስተዋለው የጥራት እና እጥረት ችግር እንዳለና ክትትል በማድረግ ለማረም ጥረት እየተደረገ እንደሆነ ገልፀዋል፡፡

40. በመሆኑም ኤጀንሲው በፀደቁና በተከለሱ የሙያ ደረጃዎች ላይ ተመስርቶ በተሟላ ሁኔታ የምዘና መሳሪያዎች አለማዘጋጀቱ እና ተግባራዊ ስለመደረጋቸው በቂ ክትትል እና ድጋፍ አለማደረጉ ሰልጣኞች የወሰዷቸውን ስልጠናወች ባግባቡ እንዳይመዘኑ የሚያደርግ እና ከእያንዳንዱ ስልጠና የሚጠበቀው ውጤት ስለመሳካቱ ወይም ስላለመሳካቱ ለማረጋገጥ እንዳይቻል ያደርጋል፡፡

## ኤጀንሲው የሙያ ብቃት ምዘና ስርዓት ስለመዘርጋቱ እና አፈፃፀሙን ስለመከታተሉ በተመለከተ

41. በደንብ ቁጥር 199/2003አንቀፅ 6 ንዑስ አንቀጽ6 መሰረት ኤጀንሲው የሙያ ብቃት ምዘና ስርዓት በመዘርጋት የቴ/ሙ/ት ሰልጣኞች በምዘና ሂደት ውስጥ ያለፉ ስለመሆኑ ሊከታተል እና አፈፃፀሙንም ሊቆጣጠር ይገባል፡፡

42. ይሁን እንጂ ጉዳዩን አስመልክቶ የኦዲት ቡድኑ ለኤጀንሲው የስራ ሃላፊወች እንዲሁም በናሙና ተመርጠው ለታዩ የክልል ቴ/ሙ/ት/ስ/ ቢሮዎች ፣ የሙያ ደረጃ ምደባና ብቃት ምዘና ማዕከላት እና ለቴ/ሙ/ት/ስ/ኮሌጆች የስራ ሃላፊወች ላቀረበው ቃለ መጠይቆች እና ከተከለሱ የሰነድ ማስረጃወች ኤጀንሲው የሙያ ብቃት ምዘና ስርዓትን ቢዘረጋም የቴ/ሙ/ት/ስ ሰልጣኞች በምዘና ሂደት ውስጥ ስለማለፋቸው እንዲሁም ኤጀንሲው የምዘና ስርአቱ ውጤታማ እንዲሆን የሚያስችል ተከታታይነት ያለው በቂ ክትትል እና ቁጥጥር ያላደረገ መሆኑን ፡

43. እንዲሁም በ2010 በጀት ዓመት በመንግሰት እና በግል ተቋማት መደበኛ ስልጠናን ያጠናቀቁ 377,844 ሲሆኑ የተመዘኑት 155,479 ብቻ መሆናቸውን ፣ አጫጭር ስልጠና ያጠናቅቁ 834,018 ሲሆኑ የተመዘኑት ግን 177,219 ብቻ መሆናቸውን፣ በአጫጭር ስልጠና እና በኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን ድጋፍ ስራ ምዘና ያለመጠናቀቅ ችግር መኖሩን ፣ የሙያ ደረጃን ለኤክስቴንሽን ድጋፍ የጥራት ማስጠበቂያ መሳርያ አድርጎ በመጠቀም ጥቃቅን እና አነስተኛ ተቋማትን እስከ ደረጃ አራት የማብቃት ስራ በሚፈለገው ልክ አለመሰራቱን እና ጥራትን በምዘና እንዲረጋገጥ ማድረግ ላይ ትኩረት ተሰጥቶ አለመሰራቱን ፣ በሬልዌይ ቴክኖሎጂ የብቃት ማረጋገጫ ምዘና ፓኬጅ እንደ ሀገር አለመኖሩን እንዲሁም በልደታ ማኑፋክቸሪንግ ኮሌጅ GMFA እና በአውቶ መካኒካል ዲፓርትመንት በደረጃ 5 ሙያ ምዘና የማይሰጥ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

44. በሌላ በኩል በኦዲት ወቅት በናሙና ተመርጠው በታዩ ክልሎች ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የስራ ሃላፊወች ጋር በተካሄዱ ቃለ መጠይቆች እና የሰነድ ክለሳዎች የሚከተሉት የአሰራር ችግሮች ተገኝተዋል፤-

- በደቡብ ክልል ሀዋሳ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ በአንዳንድ ስልጠናዎች ደረጃ አንድን ሳያጠናቅቁ እና ሳይመዘኑ ወደ ደረጃ ሁለት የሚሄዱበት ሁኔታ መኖሩን እንዲሁም በጋርመንት እና ሌዘር ቴክኖሎጂ ሰልጣኞችን አሰልጥኖ እያስመረቀ የሚገኝ ቢሆንም የአውቶ ካድ ማሽን ባለመኖሩ በጋርመንት ደረጃ 3 እና 4 ለመመዘን ጥያቄ ያቀረቡ ተመዛኞች እንዲሁም በሌዜር ደረጃ 3 የሰለጠኑ የኮሌጁ ስልጣኞች በከፊል ከአውቶ ካድ ጋር በተያያዘ የምዘና ፕሮግራም ተይዞላቸው ነገርግን ለመመዘን የተመደበ መዛኝ ባለመሟላቱ ሊመዘኑ አለመቻላቸውን፤

- በአማራ ክልል ቅድመ ምዘና ግምገማ እና ማጠቃለያ ግምገማ የማይደርግ መሆኑን ፣ ስልጠና በተሰጠበት የብቃት አሀድ ምዘና የማይሰጥበት ሁኔታ መኖሩን፣
- በአፋር ክልል የምዘና ወቅታዊነት ላይ ችግር ያለ በመሆኑ ሰልጣኞች ደረጃ ሁለትን ሳይመዘኑ ደረጃ ሶስትን ተምረው ደረጃ ሁለትን እና ደረጃ ሶስትን በአንድ ላይ ምዘና እንዲወስዱ የሚደረግበት ሁኔታ መኖሩን እንዲሁም ምዘና ሳይወስዱ ወደ ስራ የሚገቡበት ሁኔታ መኖሩን የኦዲት ቡድኑ ባካሄዳቸው የሰነድ ክለሳወች ለማወቅ ችሏል፣

45. በኦዲት ቡድኑ በናሙና በተመረጡ የማሰልጠኛ ተቋማት በተካሄዱ የመስክ ስራዎች ባካሄዳቸው የሰነድ ክለሳወች እና ለሚመለከታቸው የስራ ሃላፊዎች ላቀረባቸው ቃለ መጠይቆች ከተሰጡ መልሶች የሚከተሉት የአሰራር ችግሮች ተገኝተዋል፦ በአዲስ አበባ ምስራቅ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ እና በሀዋሳ አትላስ የቢዝነስና ቴክኖሎጂ ኮሌጅ ለሰልጣኞች በወቅቱ ምዘና የማየሰጥበት እና የሚዘገይበት ሁኔታ መኖሩን ፣ በኤስ ኦ ኤስ የቴ/ሙ/ት/ስ ተቋም በ Installation Constraction Works( ) ላይ በምዘና ማዕከል እጥረት ምክንያት ለሰልጣኞች ምዘና በወቅቱ የማይሰጥ መሆኑን እንዲሁም የቴ/ሙ/ት/ስ ሰልጣኞች በምዘና ሂደት ውስጥ ያለፉ ስለመሆኑ በቂ ክትትል እና ቁጥጥር የማይደረግ መሆኑን፣ ለማወቅ ተችሏል፡፡

46. ጉዳዩን አስመልክቶ የሚመለከታቸው የኤጀንሲው የስራ ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ እና ለቀርበላቸው የነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት መልስ የኦዲት ግኝቱ ትክክል መሆኑን ተቀብለው የቴ/ሙ/ት/ስልጠና አዋጅ እና ስትራቴጅው እንደሚገልጸው የምዘና ማዕከላት መሆን ያለባቸው ኢንዱስትሪዎች እንጅ ማሰልጠኛ ተቋማት በላመሆናቸው ኢንዱስትሪዎችን በማሳመን ሁሉም የምዘና ማዕከሎቻችው ኢንዱስትሪዎች እንዲሆኑ ጥረት እያደረጉ መሆኑን እንዲሁም የምዘና ጥራት ችግር መኖሩን በዝርዝር በኤጀንሲውም የተገመገመ በመሆኑ ችግሮቹን ለመቅረፍ ከክልሎች ጋር በመተባበርና ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም እና አዳዲስ የአሰራር ማንዋሎችን በማዘጋጀት ለማሻሻል ትኩረት ሰጥተው እንደሚሰሩ

47. እንዲሁም የክትትል እና ድጋፍ ስራዎችን አስመልክቶ የኤጀንሲውን የቴክኒክ ቡድን አባላትን በማሳተፍ የመስክ ምልከታ ማካሄዳቸውን እና ችግሩን ተገንዝበው ችግሮቹን ለመፍታት የምዘና አፈፃፀም ዝርዝር መመሪያ አዘጋጅተው ለክልሎች

በማውርድ ስራ ላይ የሚገኙ መሆኑን እና በአፈፃፀሙ ዙርያ ከክልል ክልል ልዩነት እንዳለና ችግሮቹ አሁንም ያልተፈቱ በመሆኑ በታህሳስ 2011 ዓ.ም በዝርዝር የገመገሙ መሆኑን ገልፀው፤ በታዳጊ ክልሎች ካላቸው ነባራዊ ሁኔታ አንፃር ተመዝኖ የበቃ የሰው ሃይል / የመዛኝ / እጥረት በመኖሩ በቀጣይ የተለያዩ ድጋፎችን በማድረግ እና አጓራባች ክልሎችም እንዲደግፉ ለማድረግ ጥረት እየተደረገ መሆኑን ገልፀዋል፤፤

48. የፌ/ቴ/ሙ/ት/ስ/ ኤጀንሲ የስራ ኃላፊዎች ኦዲቱ ሪፖርት መውጫ ስብሰባ ላይ በተሰጠ ምላሽ ኦዲት ግኝቱ መቀበላቸው ገልፀው ከኦዲቱ ነባራዊ ሁኔታ ተነስተው ወደ ስራ መግባታቸውን ገልፀዋል፡፡
49. በመሆኑም ኤጀንሲው የሙያ ብቃት ምዘና ስርዓትን በመዘርጋት ሰልጣኞች በምዘና ሂደት ውስጥ ያለፉ ስለመሆኑ በተሟላ ሁኔታ አለመከታተሉ እና አለመቆጣጠሩ በምዘና ሂደት ያለፉ ብቁ እና በስራ አለም ውጤታማ የሚሆኑ ባለሙዎችን ለማግኘት አስቸጋሪ እንዲሆን ያደርጋል፡፡

## ኤጀንሲው ሀገር አቀፍ የብቃት ምስክር

## ወረቀት አሰጣጥ ስርዓት መዘርጋቱን በተመለከተ

50. በደንብ ቁጥር 199/2003 ዓንቀፅ 6 መሠረት ኤጀንሲው ለሙያ ብቃት ምዘና ሀገር አቀፍ የብቃት ምስክር ወረቀት አሰጣጥ ስርዓት በመዘርጋት አፈፃፀሙን ሊቆጣጠር ይገባል፡፡
51. ይሁን እንጂ ጉዳዩን አስመልክቶ በኦዲቱ ወቅት ለኦዲት ቡድኑ በኤጀንሲው ቀርበው ከተከለሱ ማስረጃዎች የሚከተሉት ችግሮች ታይተዋል፤-
    - በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የቴ/ሙ/ት/ስ/ቢሮ የግልና መያድ ማሰልጠኛ ተቋማት ላይ በተካሄደ የክትትል ስራ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት ለሰልጣኞች የሚሰጥ የስልጠና የምስክር ወረቀት በየተቋሙ የሚለያይ መሆኑን:
    - የተቋማት አቅም ግንባታ ዋና የሥራ ሂደት በግልና መንግስታዊ ያልሆኑ ማሰልጠኛ ተቋማት ላይ በተካሄደ የማጥራት ስራ (ኢንስፔክሽን) በተዘጋጀ ሪፖርት በኮሌጅ ደረጃ የታዩ ችግሮች የብሄራዊ ምዘና ውጤት በማህደራቸው ውስጥ ያልገባላቸው ሰልጣኞች መኖራቸውን፣ ስልጠናቸውን ያጠናቀቁ ሰልጣኞች ሰርተፍኬት ላይ የሚመለከተው አካል አለመፈረም ፣ ብቃታቸውን

ለማያረጋግጡ ሰልጣኞች የተቋም የብቃት ማረጋገጫ ሰርቲፊኬት የሚሰጥ መሆኑን መገለፁ፤

- በደቡብ ብ/ክ/መ የቴ/ሙ/ት/ስ ቢሮ ብቃታቸውን ላረጋገጡ ባለሙያዎች ደረጃ 4 ለደረሱ ባለሙያዎች ብቻ ኦርጅናል የምስክር ወረቀት እነደሚሰጥና ደረጃ 1/ 2 /3 በጊዚያዊ የምስክር ወረቀት ብቻ እንዲቆዩ የሚደረግ መሆኑን ፣ ብቃታቸውን ላረጋገጡ ተመዛኞች ሰርተፊኬት ያለመስጠት ሁኔታ መኖሩን /በተለይ ደረጃ 1 እና 2/ ፣ በአጫጭር ስልጠና አጠናቀው የሚወጡ ሰልጣኞችን የደረጃ አንድ ሰርትፍኬት የሚሰጥበት ሁኔታ መኖሩ ፣

52. እንዲሁም በኦዲት ቡድኑ በናሙና በተመረጡ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር፣ በኦሮሚያ ፣ አፋር ፣ አማራ እና ደቡብ ክልል የቴ/ሙ/ት/ስ/ቢሮዎች እና በሰመራ ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ፣ በወ/ሮ ስኂን ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ፣ በሀዋሳ አትላስ ቢዝነስና ቴክኖሎጂ ኮሌጅ እና ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ፣ በሻሼ መኔ አፍሪካ ቤዛ የቴ/ሙ/ት/ስ/ኮሌጅ እና ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ፣ በምስራቅ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ እና በልደታ ማኑፋክቸሪንግ ኮሌጅ በተካሄዱ የመስክ ስራዎች ለሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ከቀረቡ ቃለ መጠይቆች እና ከተከለሱ ሰነዶች የሚከተሉት የአሰራር ችግሮች ታይተዋል፡-

- በሀዋሳ አትላስ የቢዝነስና ቴክኖሎጅ ማሰልጠኛ ኮሌጅ እና በሻሸመኔ አፍሪካ ቤዛ ኮሌጅ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት አሰጣጥ የሚዘገይበት ሁኔታ መኖሩን፣
- በሙያ ብቃት ምዘና ማዕከላት ዕውቅና አሰጣጥ መመሪያ ገፅ 6 መሠረት የሙያ ብቃት ምዘናና ሀገር አቀፍ የብቃት ምስክር ወረቀት አሰጣጥ ስርዓትን ዘርግቶ ጊዜያዊ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት በብቃት ማህከላት ተዘጋጅቶ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ስለመሰጠቱ እና ዋናውን በሶስት ወር ውስጥ አዘጋጅቶ በማዕከላት በኩል ለተመዛኞች የማድረስ ስራ እየተስራ አለመሆኑን፣
- የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ለሦስት አመታት ብቻ ስለማገልገሉ እና ከ 3 ዓመት በኂላ የሙያ ደረጃው ሲቀየር ባለሙያው ምዘናውን እንደገና የማይወስድበት ሁኔታ መኖሩን ፣ ከ 3 ዓመት በኂላ የሙያ ደረጃ ካልተቀየረ የአገልግሎት ክፍያ በማስከፈል የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ምስክር

ወረቀቱ የማይታደስበት ሁኔታ መኖሩን በሌላ በኩል ኤጀንሲው ጠንካራ የክትትል እና ቁጥጥር ስራ እየሰራ አለመሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

53. ጉዳዩ የሚመለከታቸው የኤጀንሲው የስራ ኃላፊዎች ለነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት መልስ በመረጃ ዙሪያ የተገለፀው የኦዲት ግኝቱ ትክክል መሆኑን ገልፀው አዋጁን ተከትሎ በተዘጋጀው የምዘናና ዕውቅና አሰጣጥ ማስተግበሪያ መመሪያ ላይ ስለ ጊዜያዊ እና ኦርጂናል የምስክር ወረቀት አሰጣጥ ስርዓት እና እድሳት ሁኔታ በግልጽ መቀመጡን እና ፣ ክልሎች መመሪያውን በትክክል አንብበው ስራ ላይ እንዲያውሉ ክትትልና ድጋፍ እያደረጉ መሆኑን ገልፀዋል፤ በክልሎች መካከል የሚታየውን የአፈፃፀም ልዩነት ለማጥበብ ትኩረት ሰጥቶ ለመስራት በ2011 ዓም ታህሳስ ወር በተደረገው ግምገማና መግባባት ሁሉም ደረጃዎች ላይ ኦርጂናል የምስክር ወረቀት እንዲሰጥ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ መሰረት እንዲታደስ መግባባት ተደርሶ በቀጣይ ተግባራዊ ለማድረግ ከክልል ብቃት ማዕከላት ጋር በመሆን የምዘና ማስተግበሪያ መመሪያው ላይ በተቀመጠው ስታንዳርድ መሰረት በተቀመጠው ጊዜ መሰረት እንዲሰጡ ጥብቅ ክትትልና ድጋፍ የሚያደርጉ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

54. የኤጀንሲው የስራ ሃላፊወች ይህንን ይበሉ እንጂ ኤጀንሲው ለሙያ ብቃት ምዘና ሀገር አቀፍ የብቃት ምስክር ወረቀት አሰጣጥ ስርዓትን በመዘርጋት አፈፃፀሙን ሊቆጣጠር የሚገባ ሆኖ ሳለ ይህንን ሳይፈፅም በ2011ዓ.ም ልፈፅም አቅጃለሁ ማለቱ በኦዲቱ ቡድኑ ተገቢነት ያለው መልስ ሆኖ አልተገኘም፡፡

55. የኤጀንሲው የስራ ሃላፊወች በክዋኔ ኦዲቱ የረቂቅ ሪፖርት እና መውጫ ስብሰባ ላይ በተሰጠ መልስ የኦዲት ግኝቱ ትክክል እንደሆነ በመግለፅ ከኦዲቱ ነባራዊ ሁኔታ በመነሳት በአሁኑ ጊዜ ከደረጃ 1 ጀምሮ ዋና የምስክር ወረቀት እንዲሰጥና የምስክር ወረቀት እድሳት በሁሉም መጀመር እንዳለበት አቅጣጫ በማስቀመጥ ወደ ስራ እንደተገባ፣ የመረጃ ስርዓቱን ለማዘመን የዳታቤዝና የመረጃ ቋት ዳይሬክቶሬት ጸድቆ በሂደት ላይ እንደሆነ ተገልጿል፡፡

56. በመሆኑም ኤጀንሲው ለሙያ ብቃት ምዘና ሀገር አቀፍ የብቃት ምስክር ወረቀት አሰጣጥ ስርዓትን ቢዘረጋም አፈፃፀሙን በተሟላ ሁኔታ ባለመቆጣጠሩ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቶች ለሀሰተኛ መረጃነት ሊጋለጡ ፣ ሰልጣኞች በወቅቱ

ወደ ስራ አለም እንዳይቀላቀሉ እንዲሁም ብልሹ የአሰራር ክፍተት እንዲፈጠር ያደርጋል፡፡

## የሙያ ብቃት ምዘና ማዕከላት ተደራሽነትን በተመለከተ

57. ኤጀንሲው የሙያ ብቃት ምዘና ማዕከላትን በማብቃት ተደራሽነት ለመከታተል እና ለመደገፍ የሚያስችል የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋና አፈጻጸሙን ሊከታተል ይገባል፣

58. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ጉዳዩን አስመልክቶ ለኦዲት ቡድኑ ቀርበው ከተከለሱ ሰነዶች የሚመለከቱ ሁኔታዎች ተገኝተዋል ፦ኤጀንሲው የኢንዱስትሪ የሙያ ብቃት መዛኝ ማፍራት ላይ ከግማሽ በታች እና መሉ ለሙሉ ላልፈጸሙ ክልሎች ተገቢውን ድጋፍ ያላደረገ መሆኑን ፣ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል የብቃት ምዘና ማዕከል የሌለ መሆኑን ፣ በአፋር ክልል ከ 2008-2010 ዓ.ም. በ 5 ወረዳዎች ላይ የብቃት ምዘና አገልግሎትን ተደራሽ ለማድረግ ታቅዶ ያልተከናወነ መሆኑን ፣ የደቡብ ክልል የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ኤጀንሲ አደረጃጀቱ የተገልጋዩችን ፍላጎት በሚመጥን ደረጃ በሰው ሀይል እና በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ያልተደራጀ በመሆኑ በክልሉ ባሉ  የምዘና ጣብያዎች አገልግሎት በሚፈለግ ጊዜ በወቅቱ ተገኝቶ አገልግሎት ለመስጠት ያልቻለ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

59. በኦዲቱ ወቅት በኦዲት ቡድኑ በናሙና ለተመረጡ የማሰልጠኛ ተቋማት ፣ የክልል የቴ/ሙ/ት/ስ/ቢሮዎች እና የምዘና ማእከላት ከቀረቡ ቃለ መጠይቆች የሚመለከቱት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፦

- የፌዴራል የቴ/ሙ/ት/ስ/ኤጀንሲ የሙያ ብቃት ምዘና ማዕከላትን ተደራሽነት ለመከታተልና ለመደገፍ የሚያስችል የአሰራር ስርዓት ቢዘረጋም ስለ አፈጻጸሙ የሚያደርገው ድጋፍና ክትትል በቂ አለመሆኑን ፣
- የደቡብ ክልል የብቃት ማረጋገጫ ኤጀንሲ መዋቅሩ ክልል ላይ ብቻ ሲሆን ቅርንጫፍ ጽ/ቤ/ቤቶች በወቅቱ እንዲከፈቱ ባለማደረጉ የብቃት ማረጋገጫ ማዕከሎችም ሆኑ የምዘና ጣቢያዎች ተደራሽ እንዳይሆኑ ማድረጉ እና የትኩረት ዘርፍ መ/ቤ ቶች ለምዘና ስራው የሚፈለገውን ያህል ትኩረት አለመስጠታቸው እና ይህንን የግንዛቤ ክፍተት የሚሞላ የህዝብ ግንኙነት ስራ የሚሰራ መዋቅር አለመኖሩ በመሆኑም ምዘና በማሰልጠኛ ኮሌጆች የሚሰጥ መሆኑን ፣

- የምዘና አገልግሎት በየሳምንቱ ከክልል ማዕከል ወደ የምዘና ጣብያዎች እየተሄደ የሚሰጥ ሲሆን የተሸከርካሪ እጥረት በመኖሩ ምክንያት አንዳንድ የምዘና ፕሮግራሞች በተያዘላቸው ጊዜ የማይካሄዱበት ሁኔታ መኖሩን በተጨማሪም የሚቋቋሙት የምዘና ጣቢያዎች ደረጃቸውን የጠበቁ አለመሆናቸውን፡
- በአፋር ክልል የምዘና ማዕከላት ተደራሽ አለመሆናቸው በክልሉ የኢንዳስትሪዎች እጥረት በመኖሩ ከመመሪያ ውጭ ምዘና በኮሌጆች የሚሰጥ መሆኑን የሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ለኦዲት ቡድኑ ገልጸዋል፡፡

60. ጉዳዩ የሚመለከታቸው የኤጀንሲው የስራ ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ ተዘጋጅቶ ለቀረበው የነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት መልስ
    - የሙያ ብቃት ምዘና ማረጋገጫ ማዕከላት ወጥ የሆነ አደረጃጀት እንዲኖር ክትትል የሚያደረጉ መሆኑን ፣ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል የብቃት ምዘና ማዕከል ኤጀንሲ ያለ ቢሆንም እጥረት በመኖሩ በክልሉ የአደረጃጀት እና አቅም ውስንነት ላይ በቀጣይ ከክልሉ ጋር በመነጋገር ለመፍታት ጥረት የሚያደርጉ መሆኑን ፣
    - በአዋጅ ቁጥር 954/2008 መሰረት ለቴ/ሙ/ት/ስልጠና የምዘና ማዕከላት መሆን የሚችሉት ኢንዱስትሪዎች መሆናቸውን ያስቀመጠ ሲሆን ባለው ችግር ምክንያት ተቋማትን እየተጠቀሙ ያሉ የብቃት ማዕከላት መኖራቸው የተገመገመ በመሆኑ ወደፊት ለኢንዱስትሪዎች ግንዛቤ በመፍጠር ሙሉ በሙሉ ወደ ኢንዱስትሪው መሸጋገር እንዲቻል ክትትልና ድጋፍ እንደሚያደርጉ፣
    - በደቡብ ክልል የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ኤጀንሲ የተደራሽነት ችግር ያለ በመሆኑ በቀጣይ ከክልሉ መንግስት ጋር በመነጋገር ችግሩ እንዲፈታ በአመራር ደረጃ የሚቻለውን ሁሉ ክትትልና ድጋፍ እያደረጉ መሆኑን፡
    - የአደረጃጀት እና አቅም ዉስንነት ያለባቸውን ክልሎች በቀጣይ ከክልሎች ጋር በመነጋገር ለመፍታት ጥረት እንደሚያደርጉ እና ምዘናውን ተደራሽ ለማድረግ ክትትልና ድጋፍ እየተደረገ እንደሆነና ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ገልፀዋል፡፡

61. የኤጀንሲው የስራ ሃላፊወች ይህንን ይበሉ እንጂ ኤጀንሲው የሙያ ብቃት ምዘና ማዕከላትን ተደራሽነትን ለመከታተል እና ለመደገፍ የሚያስችል የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት አፈፃፀሙን ስለመከታተሉና ስለመደገፉ ባካሄደው ድጋፍ ምን አይነት ተጨባጭ ችግሮችን እንደፈታ የሚያሳይ የሰነድ ማስረጃ ለኦዲት ቡድኑ ያላቀረበ

በመሆኑ የኤጀንሲው የስራ ሃላፊወች የሰጡት መልስ በኦዲቱ ተቀባይነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፤፤

62. የፌ/ቴ/ሙ/ት/ስ/ ኤጀንሲ የስራ ኃላፊዎች ኦዲቱ ሪፖርት መውጫ ስብሰባ ላይ በተሰጠ ምላሽ ኦዲት ግኝቱ መቀበላቸው ገልፀው ከኦዲቱ ነባራዊ ሁኔታ ተነስተው ወደ ስራ መግባታቸውን ገልፀዋል፡፡

63. በመሆኑም ኤጀንሲው የሙያ ብቃት ምዘና ማዕከላትን ተደራሽነት ለመከታተል እና ለመደገፍ የሚያስችል ውጤታማ የአሰራር ስርዓት ያልዘረጋና አፈጻጸሙን ያልተከታተለ በመሆኑ እንዲሁም የሙያ ብቃት ምዘና ማዕከላት ተደራሽ አለመሆናቸው ሰልጣኞች ወቅታዊ ምዘና እንዳያገኙ ከማድረጉም በተጨማሪ የትኩረት ዘርፍ መ/ቤቶች ለምዘና ስራው የሚፈለገውን ያህል ትኩረት ሰጥተው ወደ ስራ ባለመግባታቸው ለምዘና ስራው ደረጃቸውን ባልጠበቁ ማሰልጠኛ ኮሌጆች እንዲሰጥ በመደረጉ ሰልጣኞች ተገቢውን ምዘና እንዳይወሰዱ በማድረግ በሀገር ደረጃ ወጥ የሆነ አሰራር እንዳይኖር ተፅእኖ እንዲፈጠር አድርጓል፡፡

## መዛኞች ለመዛኝነት ሲመረጡ የመመዘኛ መስፈርቶችን ያሟሉ መሆኑን በተመለከተ ፣

64. ኤጀንሲው በሙያ ብቃት ምዘና ማዕከላት ዕውቅና አሰጣጥ መመሪያ መሠረት መዛኞች ለመዛኝነት ሲመረጡ የሚያስፈልጉ መመዘኛ መስፈርቶችን ያሟሉ ስለመሆኑ ሊከታተል ይገባል፡፡

65. በአዋጅ ቁጥር 954/2008 መሰረት የተዘጋጀው የሙያ ብቃት ምዘና ማዕከላት ዕውቅና አሰጣጥ መመሪያ ላይ መዛኝ ለመዛኝነት ሲመረጥ የሚያስፈልጉ መመዘኛ መስፈርቶችን / በሙያው ላይ በስራ የሚገኝ/የምትገኝ ፣ ምዘና በሚሰጥበት ሙያ ቢያንስ ሶስት ዓመት የሰራ/የሰራች ፣ ከደረጃ አምስት በስተቀር ምዘና ከሚሰጥበት የሙያ ደረጃ ቢያንስ በአንድ ደረጃ ከፍ ብሎ የተመዘነ/የተመዘነች ፣ የሙያ ምዘና ስነዘዴ የሰለጠነበት/የሰለጠነችበትን ማስረጃ የሚያቀርቡ ፣ የመዛኝነት ሙያ ፍቃድ ያለው/ያላት እና መልካም የሙያ ስነ ምግባር ያለው/ያላት መሆን እንዳለባቸው ያስቀምጣል፡፡

66. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ለኦዲት ቡድኑ በኤጀንሲው እና በናሙና ከተመረጡ የክልል የቴ/ሙ/ት/ስ/ቢሮዎች እና የምዘና ማእከላት ቀረበው ከተከለሱ ማስረጃዎች የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፦ በኤጀንሲው የሙያ ደረጃ ምደባና ምዘና

ዳ/ሬት በተመረጡ ፖሊ. ቴክኒክ ኮሌጆች ላይ በተደረገ ቴክኒካል ድጋፍ ሪፖርት ላይ መዛኞች ለመዛኝነት ሲመረጡ የሚያስፈልጉ የመመዘኛ መስፈርቶችን ያላሟሉ እና ያልተመዘኑ መዛኞች መዛኝ ሆኖው የሚመደቡበት ሁኔታ መኖሩን ፣ በቂ የኢንዱስትሪ መዛኝ ባለመኖሩ በዘርፉ እውቅና የሌላቸው እና ያለሙያቸው መዛኝ ሆነው ሰልጣኞችን እንዲመዝኑ የሚደረግበት ሁኔታ መኖሩ፤

67. በአማራ ክልል ከተመዛኞች ጋር ተመሳሳይ ደረጃ ያላቸው መዛኞች የሚመደቡበት ሁኔታ መኖሩን ለአብነት ፣ ኮምቦልቻ ፖሊ. ቴክኒክ ኮሌጅ ፣ ከሚሴ ቴ/ሙ/ኮሌጅ ፣ ለጊ ሀይቅ ቴ/ሙ/ኮሌጅ ፣ ከላላ ቴ/ሙ/ኮሌጅ ፣ መካነ ሰላም ቴ/ሙ/ኮሌጅ ፣ ትሮፒካል ኮሌጅ ፣ አልካን ኮሌጅ፣ ወ/ሮ ስኂን ፖሊ. ቴክኒክ ኮሌጅ እና ደሴ ጤና ሳይንስ ኮሌጅ፡ በደቡብ ክልል ባልተመዘኑ እና ያለ ደረጃ በመዛኝነት የሚመደብበት ሁኔታ መኖሩን ለምሳሌ በአውቶሞቲቭ በደረጃ 3 የበቃ መዛኝ ደረጃ 4 ላይ መመደቡን ፣ ለኢንዳስትሪ መዛኞች ደረጃ ያልወጣ እና ወቅታዊ ብቃታቸው የሚገመገምበት ስርዓት ያልተዘረጋ መሆኑን ፣

68. እንዲሁም በኦዲት ቡድኑ በናሙና ለተመረጡ የማሰልጠኛ ተቋማት ፣ የክልል የቴ/ሙ/ት/ስ/ቢሮዎች እና የምዘና ማእከላት የስራ ኃላፊዎች ከቀረቡ ቃለ መጠይቆች የሚመለከቱ ሁኔታዎች ተገኝተዋል፦

69. በአማራ ክልል ብቃት ማዕከል ፌዴራል የቴ/ሙ/ት/ስ/ኤጀንሲ የመዛኞችን መስፈርት አዘጋጅቶ የሚልክ ቢሆንም ነገር ግን በመስፈርቱ መሰረት ስለመከናወኑ ክትትል የማያደረግ መሆኑን መገለፁ፣

70. በደቡብ ክልል ሀዋሳ ፖሊ. ቴክኒክ ኮሌጅ ምዘና በብዛት በሚኖርበት ወቅት የመዛኝ እጥረት እንደሚከሰት ይህንንም ተከትሎ መስፈርት ሳያሟላ የሚመረጥ መዛኝ የሚመረጥበት ሁኔታ መኖሩን እንዲሁም የፌዴራል የቴ/ሙ/ት/ስ/ኤጀንሲ ለመዛኝነት የሚመረጡ መዛኞች የሚያስፈልጉ የመመዘኛ መስፈርቶችን አሟልተው የተመረጡ ስለመሆኑ ክትትል የማያደርግ መሆኑን የሚመለከታቸው የስራ ሃላፊዎች ገልጸዋል፡፡

71. ጉዳዩ የሚመለከታቸው የኤጀንሲው የስራ ኃላፊዎች ለነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት መልስ ያለውን የመዛኝ እጥረት እና የጥራት ችግር እንዲሁም በመዛኝ ፍትሀዊ አመዳደብ ዙሪያ የተነሱ ችግሮችን ክልሎች የመዛኝና የምዘና ማዕከል ዝርዝር መረጃ በማጠናከርና በየጊዜው ወቅታዊ እያደረጉ እንዲልኩ ከታህሳስ 22 እስከ 24/2011 ከክልሎች ጋር በተደረገ ስብሰባ ላይ ስምምነት ላይ መድረሳቸውን

እና መረጃው ከተሰበሰበ በኋላ ስለ ትክክለኛነቱ በተለያዩ የክትትልና ድጋፍ ዘዴዎች የመስክ ምልከታን ጨምሮ የሚታይ መሆኑን እና በመዛኝ ብቃትና ከተመዛኙ ጋር ያለውን  አጠቃላይ መስፈርት አዋጁን ተከትሎ በወጣው የምዘና እና እውቅና አሰጣጥ መመሪያው ላይ የተቀመጠ ስለሆነ ክልሎች መመሪያው በሚያዘው መሰረት እንዲተገብሩ ክትትልና ድጋፍ እያደረጉ እንደሚገኙ ገልፀዋል፡፡

72. የኤጀንሲው የስራ ኃላፊዎች ይህን ይበሉ እንጂ ኦዲቱ እስከ ተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ጉዳዩን አስመልክቶ የተሰራውን ስራ የሚሳይ ደጋፊ ማስረጃ ለኦዲት ቡድኑ ያላቀረቡ በመሆኑ በኤጀንሲው የስራ ሃላፊወች የተሰጠውን መልስ ለመቀበል የኦዲት ቡድኑ ይቸገራል፡፤

73. የኤጀንሲው የስራ ኃላፊዎች በክዋኔ ኦዲቱ የረቂቅ ሪፖርት ላይ በሰጡት አስተያየት የኦዲት ግኝቱ ትክክል እንደሆነና ኤጀንሲው ችግሩን ለመፍታት የመዛኝ መስፈርት በመመሪያ አስደግፎ ወደ ክልሎች ያወረዱ ሲሆን አተገባበሩን አስመልክቶ ከክልሎች ጋር በመገምገም እንዲያስተካክሉና የመዛኞች የመረጃ ቋት እንዲኖራቸው በማድረግ ችግር ያለባቸው መዛኞች ላይ ተገቢውን የዕርምት እርምጃ እንዲወስዱ እንደተደረገና ተጠናክሮ እንደሚቀጥል እና የመዛኞች እጥረት ጥራት ላይ ችግር ስለሚፈጥር ችግሩን ለመቅረፍ አቅጣጫ በማስቀመጥ ወደ ስራ እንደተገባ ተገልጿል፡፡

74. የፌ/ቴ/ሙ/ት/ስ/ ኤጀንሲ የስራ ኃላፊዎች ኦዲቱ ሪፖርት መውጫ ስብሰባ ላይ በተሰጠ ምላሽ ኦዲት ግኝቱ መቀበላቸው ገልፀው ከኦዲቱ ነባራዊ ሁኔታ ተነስተው ወደ ስራ መግባታቸውን ገልፀዋል፡፡

75. በመሆኑም ኤጀንሲው መዛኞች ለመዛኝነት ሲመረጡ መመዘኛ መስፈርቶችን ያሟሉ ስለመሆኑ ባለመከታተሉ በሃገሪቱ የተለያዩ ቦታወች ባሉ ተቋማት የሰለጠኑ ሰልጣኞች አልፎ አልፎ ደረጃቸውን ባላሟሉ ምዛኞች በመመዘናቸው ደረጃቸውን የማያሟሉ ሰልጣኞች እውቅና እንዲያገኙ ሊያደርግና በዘርፉ እንዲገኝ የታሰበው ውጤታማነት እንዳይገኝ ሊያደርግ ይችላል፤

## የማሰልጠኛ ተቋማት  ተደራሽነት እና

## እውቅና አሰጣትን በተመለከተ

76. በኤጀንሲው የቴክኒክ እና ሙያ ትምህርት እና ስልጠና ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 199/2003 አንቀፅ 6 ንኡስ አንቀፅ 7 እና ትራንፎርሜሽን ዕቅድ (2008-2012) ነሀሴ 2007 ዓ.ም. የታተመ ገፅ 28 በተቀመጠው መሠረት የማሰልጠኛ ተቋማት ተደራሽ እንዲሆኑ እና እውቅና የሚያገኙበትን መመዘኛ መመርያ ሊያወጣ እና አፈጻጸሙን ሊቆጣጠር ይገባል፡፡

77. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ለኦዲት ቡድኑ ቀረበው ከተከለሱ ማስረጃዎች የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡- በሀገር አቀፍ ደረጃ በአንድ ወረዳ አንድ ማሰልጠኛ ተቋም እንዲኖር ለማድረግ ቢታቀድም በ2010 በጀት ዓመት 158 አዳዲስ ማሰልጠኛ ተቋማት ለመገንባት የታቀደ ቢሆንም መገንባት የተቻለው 24(15%)ብቻ መሆኑን ፣ በ2010 በጀት ዓመት በአገር አቀፍ ደረጃ 225 እውቅና እንዲያገኙ ታቅዶ 17(8%) ብቻ እውቅና ያገኙ መሆኑን ፣ በ2010 በጀት ዓመት በዓለም አቀፍ ደረጃ 12 እውቅና እንዲገኙ ቢታቀድም እውቅና ያገኘ ማሰልጠኛ ተቋማት አለመኖሩን

78. እንዲሁም በናሙና ከታዩ ክልሎች በኦሮሚያ ክልል ውስጥ ከሚገኙ 336 ወረዳዎች ውስጥ 163 ወረዳዎች ላይ ብቻ ተቋማት መክፈት እንደተቻለ መገለጹ ፣ በደቡብ ክልል ከ135 ወረዳዎች 51 ወረዳወች ላይ ብቻ የማሰልጠኛ ተቋማትመክፈት እንደተቻለ መገለጹ፣ በአፋር ክልል እስከ ሁለተኛው የዕድገት እና ትራንሰፎርሜሽን ዕቅድ መጨረሻ 7 የቴ/ሙ/ት/ስ/ ኮሌጆችን ለመገንባት ቢታቀድም ምንም ግንባታ አለመከናወኑ በፌ/ቴ/ሙ/ት/ስ/ኤ የ2010 ዓ.ም. ዕቅድ አፈጻጸም መገለፁ፣

79. ጉዳዩ የሚመለከታቸው የኤጀንሲው የስራ ኃላፊዎች በኦዲት ማጠቃለያ በቀረበ መጠይቅ በሰጡት መልስ የማሰልጠኛ ተቋማት እውቅና የሚያገኙበትን መስፈርት ተዘጋጅቶ የግንባታ ስታንዳርድ በማዘጋጀት ተቋሙ ምን ምን ማሽነሪዎች ያስፈልጉታል የሚለውን ስራ መስራቱን እና ሪሶርስ ሞቢላይዝ የማድረግ ስራ በኤጀንሲው የተከናወኑ ቢሆንም የማሰልጠኛ ተቋማት በሃገር አቀፍ ደረጃ ተደራሽ እንዳልሆኑ ገልጸዋል፡

80. እንዲሁም ጉዳዩ የሚመለከታቸው የኤጀንሲው የስራ ኃላፊዎች በኦዲት ማጠቃለያ በቀረበ መጠይቅ በሰጡት ምላሽ የተደራሽነት ጉዳይ እንደ ሚኒስቴር መስሪያ ቤትም ሆነ እንደ ፌዴራል መንግስት ትኩረት ተሰጥቶት እየተሰራ እንዳልሆነና ስራው ከፍተኛ የገንዘብ ወጪ ስለሚፈልግ ትኩረት እንደሚሻ እንዲሁም ጠንካራ የማሰልጠኛ ተቋማቶችን ወደ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የመውሰድ ሁኔታ እንዳለ እና የተደራሽነት ቁጥሩን እንደቀነሰው ገልጸዋል፡፡

81. ለነባራዊ ሁኔታ በሰጡት መልስ ተቋማትን የመገንባት ኃላፊነት ሙሉ በሙሉ የክልሎች ኃላፊነት መሆኑን ክልሎች ደግሞ የበጀት አቅማቸው ሊፈቅድ ባለመቻሉ በታቀደው ልክ ሊፈጸም አለመቻሉን፣ ህብረተሰቡን እና አጋር አካላትን በማስተባበር

ተደራሽ ለማደረግ ጥረት መደረጉን፣ ክልልሎች ከውስን በጀታቸዉ ለኮሌጅ ግንባታ በጀት እየመደቡ ለመገንባት መሞከራቸውን፣ የኮሌጅ ግንባታ በክልሎች የበጀት አቅም ሊከናወን እንደማይችል በማጥናት የፌደራል መንግስት እንዲ ደግፍ ፕሮጀክት ሰርተው ማቅረባቸውን በታዳጊ ክልሎችም ሆነ በሌሎች ክልሎች የኮሌጅ ግንባታ ከፍተኛ በጀት ስለሚጠይቅ አፈጻጸሙ አንጻራዊ ልዩነት ከክልል ክልል ያለ ቢመስልም እንደ ሀገር ከ50 በመቶ በታች መሆኑን እንዲሁም በፍኖተ ካርታ ጥናት ችግሩ ጎልቶ የወጣ በመሆኑ መንግስት ውሳኔ ይሰጥበታል ተብሎ እንደሚጠበቅ ገልፀዋል፡

82. በሃገር አቀፍ ደረጃ የማሰልጠኛ ተቋማትን ተደራሽ ለማድረግ እና እውቅና እንዲያገኙ በታቀደው ልክ አለመከናወኑ በሃገር ደረጃ ለሚያስፈልገው የበቃ የቴክኒክና ሙያ ሰልጣኝ እጥረት እንዲኖር እና ከሰልጣኝ ብዛት አንፃር በስልጣና ጥራቱ ላይ ጫና እንዲፈጠር ያደርጋል፡፡

## የእውቅና ፈቃድ አሰጣጥ እና ክትትልን በተመለከተ

83. ኤጀንሲው በአዋጅ ቁጥር 954/2008 አንቀፅ 29 ንዑስ አንቀጽ2 ገፅ 25 መሠረት በፌዴራል ደረጃ በመንግስት ፣ በግልና በውጪ ሀገር ዜጎች በተቋቋሙ እና በሌላ ሀገር ህግ በተቋቋሙ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ስር ለሚተዳደሩ ማሰልጠኛ ተቋሞች እንዲሁም ተቋማቸውን ለማስፋፋት ለሚፈልጉ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ማሰልጠኛ ተቋሞች የእውቅና ፈቃድ ሊሰጥ እና ሊከታተል ይገባል፡፡

84. በኦዲቱ ወቅት ለኦዲት ቡድኑ ቀረበው ከተከለሱ ሰነዶች የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፦ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የቴክኒክ ሙያ ትምህርት ና ስልጠና ቢሮ የተቋማት ጥራት ማረጋገጥና አቅም ግንባታ ዋና ስራ ሂደት መያድ በጎ አድራጎት ድርጅቶች በተቋቋሙ የቴ/ሙ/ት/ስ/ ተቋማት ላይ የተካሄደ ክትትልና ድጋፍ ሪፖርት፣ የካቲት 2010 ዓም አማኑኤል የወጣቶች ስልጠና ማስተባበሪያ ወቅቱን ጠብቆ እውቅና ያለማደስ፣ ኮንሰርን ወርልድ እውቅና ፈቃድ ሳይኖረው ማሰልጠን/ ስልጠና የሚሰጠው ልደታ ማኑፋክቸሪንግ ውስጥ መሆኑ/፣ ሀንድ ካን ኢንተርናሽናል ከቴ/ሙ/ት/ስ የስልጠና ፍቃድ ሳያገኝ የስልጠና ስራ መስራቱ፣

አንዳንድ የማሰልጠኛ ተቋማት ከበጐ አድራጐት ኤጀንሲ እና የክፍለ ከተማ ቴክኒክና ሙ.ያ ጽ/ቤት ፍቃድ ማግኘት መቻላቸው እና የኤጀንሲው ፍቃድ ሳኖራቸው ስልጠና የሚሰጡ መሆኑን፣ ለአብነት አፖርቹኒቲ ኢንዱስትራላይዜሽን ሴንተር ኢትዮጵያ፣ ወጣቶች ሴቶች ማሰልጠኛ ተቋምና ኪዳነምህረት የተማሪዎች ራስ አገዝ ማህበር የሙ.ያ ተቋም፣

85. እንዲሁም በኦዲት ቡድኑ በናሙና ከተመረጡ ክልሎች ለደቡብ፣ ለኦሮሚያ፣ ለአማራ እና ለአፋር ክልል የቴ/ሙ/ት/ስ ቢሮ ለሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ ለቀረበ ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ የ/ፌ/ቴ/ሙ/ስ/ኤጀንሲ በፌዴራል ደረጃ በመንግስት ፣ በግል እና በውጪ ዜጎች ለሚቋቋሙ እና በሌላ ሀገር ህግ በተቋቋሙ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ስር የሚተዳደሩ ማሰልጠኛ ተቋሞች በህጉ መሰረት ፈቃድ የወሰዱ ስለመሆኑ በቂ ክትትል እና ቁጥጥር እያደረገ አለመሆኑን ገልጸዋል፡፡

86. የኤጀንሲው የስራ ኃላፊዎች ለነባራዊ ሁኔታ በሰጡት መልስ በፌደራል ደረጃ ፈቃድ ለመስጠት እና ለማድስ እንዲሁም ክትትልና ድጋፍ ለማድረግ የሰው ኃይል እጥረት ያለባቸው መሆኑን ችግሩን ለማቃለል የመሰረታዊ ስራ ሂደት ለውጥ /ቢፒአር/ ተሰርቶ በሲቭል ሰርቪስ በኩል የጸቀደ በመሆኑ ችግሩ በቅርብ ቀን የሚፈታ መሆኑ ገልፀዋል፡፡

87. የፌ/ቴ/ሙ/ት/ስ/ ኤጀንሲ የስራ ኃላፊዎች ኦዲቱ ሪፖርት መውጫ ስብሰባ ላይ በተሰጠ ምላሽ ኦዲት ግኝቱ መቀበላቸው ገልፀው ከኦዲቱ ነባራዊ ሁኔታ ተነስተው ወደ ስራ በመግባት ጠንካራ ክትትል እያደረጉ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

88. ሆኖም ኤጀንሲው በፌዴራል ደረጃ በመንግስት ፣ በግል እና በውጪ ዜጎች ለሚቋቋሙ እና በሌላ ሀገር ህግ በተቋቋሙ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ስር የሚተዳደሩ ማሰልጠኛ ተቋሞች ላይ የተጠናከረ የክትትል እና ቁጥጥር ስራ ባለማከናወኑ ከህግ አግባብ ውጪ የማሰልጠኛ ተቋሞችን ማቋቋም እና ማስፋፋት እንዲችሉ ክፍተት ፈጥሯል፡፡

## የማሰልጠኛ ተቋማት ዕውቅና በተሰጣቸው የማሰልጠኛ መርሃ ግብሮች መሰረት ማከናወናቸውን በተመለከተ

89. ኤጀንሲው የቴክኒክ እና ሙ.ያ ትምህርት እና ስልጠና ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 199/2003 አንቀፅ 6 ንኡስ አንቀፅ 7 እና ዕውቅና አሰጣጥ መመሪያ ገፅ 23 እና 5

መሠረት የማሰልጠኛ ተቋማት የስልጠና መርሃ ግብሮችን ዕውቅና ፍቃድ በተሰጠበት መመዘኛ መሰረት ስራወችን የማያከናውኑ ተቋማትን የዕውቅና ፈቃዳቸውን መሰረዙን/መታገዱን እንዲሁም የዕውቅና ፍቃዳቸውን የማያሳድሱ ተቋማትን ሊከታተል እና ሊቆጣጠር ይገባል፡፡

90. በኦዲቱ ወቅት ለቡድኑ ቀርበው ከተከለሱ ማስረጃዎች የሚከተሉት ችግሮች ተገኝተዋል፦ በአማራ ክልል ህጋዊ አሰራርን የጣሱ ኮሌጆች መኖራቸው ከተፈቀደላቸው ቁጥር በላይ ሰልጣኝ የሚቀበሉ ኮሌጆች መኖራቸውን፣ ከዘመኑ የመግቢያ ነጥብ በታች ሰልጣኞችን የሚቀበሉ ኮሌጆች መኖራቸውን፣ የሰልጣኝ አሰልጣኝ ጥምርታን መሰረት በማድረግ ብቁና ቋሚ አሰልጣኝ አሟልተው የማይገኙ ኮሌጆች መኖራቸውን እንዲሁም አንዳንድ የግል ኮሌጆች ፈቃድ ሳይጠይቁ ሰልጣኞችን መዝግበው ስልጠና የሚሰጡበት ሁኔታ መኖሩን ፣ ለአብነት፦ አምባሳደር ኮሌጅ አውቅና ባልተሰጠው በfood production supervision ደረጃ 4 ሰልጣኝ መቀበሉን ፣ ጋምቢ ኮሌጅ የኮምፕሪሄንሲቭ ነርስ ፈቃድ ሳይሰጠው ሰልጣኝ መቀበሉን

91. እንዲሁም በፋርማሲ ሙያ እና በከስተመር ኮንታክት በሙያ ደረጃ 2 እና 4 የሰልጣኞች ብዛት ከተፈቀደው በላይ መሆኑን፣ ባህር ዳር ሃይላድ ኮሌጅ በአካውንቲንግ ሙያ በደረጃ 2 እና 4 የሰልጣኞች ብዛት ከተፈቀደው በላይ መሆኑ እና በደረጃ 3 ፈቃድ ሳይሰጠው ሰልጣኝ መቀበሉን እንዲሁም በአካውንቲንግ ሙያ ከዘመኑ መግቢያ ነጥብ በታች 23 ሰልጣኞችን የተቀበለ መሆኑን ፣ በአልካን ኮሌጅ በሜዲካል ላብራቶሪ እና በአካውንቲንግ ደረጃ 4 ከፍቃድ በላይ ሰልጣኝ የተቀበለ እና በአካውንቲንግ ከዘመኑ መግቢያ ነጥብ በታች 28 ፣ በፋርማሲ 8 ሰልጣኞች ፣ በሚድዋይፍሪ 3 ሰልጣኞች ፣ በኮምፕሪቨንሲቭ ነርሲንግ 3 ሰልጣኞች ፣ በሜዲካልላበራቶሪ 5 ሰልጠኞች ፣ በሰረቨይንግ 15 ሰልጣኞች ሰልጣኞችን መቀበሉን ለማወቅ ተችሏል፡፡

92. እንዲሁም የኦዲት ቡድኑ በናሙና በተመረጡ ለአዲስ አበባ ከተማ፣ ለኦሮሚያ ፣ ለአፋር ፣ ለአማራ እና ለደቡብ ክልል የቴ/ሙ/ት/ስ/ቢሮ እንዲሁም ለበሰመራ ጤና ሳይንስ ኮሌጅ፣ ለወ/ሮ ስኂን ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ፣ ለሀዋሳ አትላስ ቢዝነስና ቴክኖሎጂ ኮሌጅ፣ ለሻሼመኔ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ፣ ለተግባረ ዕድ ቴክኒክ ኮሌጅ ፣ ለምስራቅ ፖሊቴክኒክ ኮሌጅ፣ ለልደታ ማኑፋክቸሪን ኮሌጅ ፣ ለሃዋሳ ፖሊ ቴክኒክ

ኮሌጅ፣ ለባህር ዳር ሃይላንደ ኮሌጅ ፣ ለሰመራ ጤና ሳይንስ ኮሌጅ) ለሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች በፌ/ቴ/ሙ/ት/ስ/ኤጀንሲ ስለሚደረገው ክትትል እና ቁጥጥር በማስረጃ አስደግፈው እንዲያብራሩ ለቀረበ ቃለ መጠይቅ ሲመልሱ በቂ ክትትል እየተደረገ አለመሆኑን ገልጸዋል፣

93. ጉዳዩ የሚመለከታቸው የኤጀንሲው የስራ ኃላፊዎች ለነባራዊ ሁኔታ በሰጡት መልስ ለግል ኮሌጆች ፈቃድ የሚሰጡ ፣ ህግን ተላልፈው ሲገኙ እርምጃ የሚወስዱት ክልሎች ቢሆኑም ኤጀንሲው ችግሮችን ለይቶ የእርምት እርምጃ እንድወስዱ የማሳሰብ ስራ የሚሰራ መሆኑን በኦድቱ የተገኙ ችግሮችን ኤጀንሲውም ሱፐርቪዥን ሲያካሂድ ያገኛቸው ክፍተቶች መሆናቸውን እና ከክልሎች ጋር በሚካሄድ የምክክር መድረግክ ላይ ቀርበው የማስተካከያ እርምጃ እንድወስዱ አቅጣጫ መቀመጡን እንዲሁም የግል ኮሌጅ ማህበራትን በመሰብሰብና በማወያየት ከዚህ አይነት ጥፋት አባሎቻቸው እንዲታረሙ እንዲያደርጉ ከስምምነት ላይ መደረሱን ገልጸዋል፡፡

94. ይሁን እንጂ የማሰልጠኛ ተቋማት የስልጠና መርሃደግብሮችን ዕውቅና በተሰጠበት መመዘኛ መሰረት ስለማከናወናቸው በእቅድ ይዞ በተሟላ ሁኔታ ክትትል አለማድረጉ እና ከመመሪያ ውጪ በሚሰሩት ላይ አሰተማሪ እርምጃ አለመውሰዱ ማስልጠኛ ተቋማት ከመመሪያ ውጪ እንዲሰሩ እና የስልጠና ጥራትን ማስጠበቅ እንዳይቻል ያደርጋል፡፡

## በተቋማት የሚሰጠው ስልጠና በስራ ገበያ ፍላጎት መሰረት መሆኑን በተመለከተ፣

95. ኤጀንሲው በቴ/ሙ/ት/ስ ስትራቴጂ መሠረት ለቴ/ሙ/ት/ስልጠና የስራ ገበያ ክትትል የሚደረግበት ስርዓት ሊዘረጋ እና በተቋማት የሚሰጠው ስልጠና በስራ ገበያ ፍላጎት መሰረት መሆኑንና ጥራት ያለው መሆኑን ሊከታተል ይገባል፡፡

96. ኦዲት ቡድኑ በናሙና በተመረጡ 4 ክልሎች እና በ 8 የማሰልጠኛ ተቋማት የሚሰጡ ስልጠናዎች በስራ ገበያ ፍላጎት መሰረት ስለመሆናቸው የሚሳይ የገበያ ፍላጐት ጥናት የተደረገባቸው ማስረጃች አለመኖራቸውን እንዲሁም ኤጀንሲው በተቋማት የሚሰጡ ስልጠናዎች በስራ ገበያ ፍላጎት መሰረት ስለመሆናቸው በቂ ክትትል የማይደረግ መሆኑን ለማወቅ ችሏል፡፡

97. ጉዳዩ የሚመለከታቸው የኤጀንሲው የስራ ኃላፊዎች ለነባራዊ ሁኔታ በሰጡት መልስ ችግሩ መኖሩን በተለያየ መንገድ ኤጀንሲው ማረጋገጥ መቻሉን እና የክልሎችን አቅም በመገንባትና የግል ኮሌጆችን አቅም በማሳደግ እንድሁም ህግና ስርአትን በማስከበር የሚፈታ መሆኑን የገባያ ጥናት በክልሎችና በተቋማት በጥራት የማካሄድ ክፍትት መኖሩን በቀጣይ የማሻሻያ እርምጃ እንደሚወሰድ ገልፀዋል፡፡

98. የፌ/ቴ/ሙ/ት/ስ/ ኤጀንሲ የስራ ኃላፊዎች ኦዲቱ ሪፖርት መውጫ ስብሰባ ላይ በተሰጠ ምላሽ ኦዲት ግኝቱ መቀበላቸው ገልፀዋል፡፡

99. በመሆኑም በተቋማት የሚሰጠው ስልጠና በስራ ገበያ ፍላጎት መሰረት አለመሆኑ ገበያው የሚፈልገውን በሙያው የበቃ ባለሙያ ለማቅረብ እንዳይቻል ያደርጋል፡፡

## ኤጀንሲው በየትኛውም ደረጃ ለሚገኙ የቴ/ሙ/ት/ስ

## አመራሮች እና አሰልጣኞች የቅድመ ስራ እና

## የስራ ላይ ስልጠና መስጠቱን በተመለከተ

100. ኤጀንሲው በየትኛውም ደረጃ ለሚገኙ የቴ/ሙ/ት/ስ አመራሮች እና አሰልጣኞች የቅድመ ስራ እና የስራ ላይ ስልጠና ሊሰጥ እንዲሁም ቀጣይ የስልጠና አፈፃፀም ሊቆጣጠር ይገባል፡፡

101. በኦዲቱ ወቅት ለቡድኑ ቀርበው ከተከለሱ ማስረጃዎች ኤጀንሲው የቴ/ሙ/ት/ስ አመራሮች እና አሰልጣኞች የቅድመ ስራ እና የስራ ላይ ስልጠና በዘጠኝ ክልሎች እና በሁለት ከተማ መስተዳደር የቴ/ሙ/ት/ስ/ አሰልጣኞችን የ2010 ዕቅድ አፈፃፀም በኦሮሚያ(24%)፣ አማራ(1.1%)፣አፋር(0) ፣ሶማሌ(44%)፣ ጋምቤላ(0)፣ አዲስ አበባ(2%)፣ በአጠቃላይ አፈፃፀሙን 22% መሆኑ እንዲሁም በአመራሮች የዕቅድ አፈፃፀም አማራ(1.3%)፣ሱማሌ(39)፣አፋር(0)፣ ቤ/ጉሙዝ(40)፣ ጋምቤላ(0)፣ ድሬ ዳዋ(0) በአጠቃላይ አፈፃፀሙን 38% መሆኑ እንዲሁም የፈሩት የኢንዱስትሪ ውስጥ አሰልጣኞች የማስተማር ስነዘዴ ስልጠና እንዲወስዱ ከማድረግ አንፃር ውስንነት መኖሩ፣

102. እንዲሁም የአቅም ግንባታ ስልጠናው የጥራት ችግር ለበት በመሆኑ ተመሳሳይ ስልጠና በተደጋጋሚ የመሰጥበት ሁኔታ መኖሩ፣ የመንግስት ተቋማት አሰልጣኞች የቅድመ እና የድህረ ስራ ስልጠና ኮታ በመስጠት ቢያሰለጥኑም ነገር ግን ለግል ተቋማት የስልጠና እድል እንደማይሰጡ እንዲሁም የተሰጡ ስልጠናዎች አፈፃፀም

ላይ ቁጥጥር የማያደረርግ መሆኑን ለኦዲት ቡድኑ ቀርበው ከተከለሱ ሰነዶች ለማወቅ ተችሏል፡፡

103. በኦዲት ቡድኑ በናሙና ለተመረጡ ለአዲስ አበባ ፣ ለአማራ፣ ለአፋር እና ለደቡብ የ/ቴ/ሙ/ስ/ቢሮዎች እና ማሰልጠኛ ተቋማት ለወ/ሮ ስኂን ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ፣ ለሻሸመኔ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ፣ ለአዳማ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ፣ ለሀዋሳ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ እና ለሀዋሳ አትላስ የቢዝነስና ቴክኖሎጂ ማሰልጠኛ ኮሌጅ ፣ ለባህር ዳር ሃይላንድ ኮሌጅ ፣ ፣ በአፋር ክልል፣ ለሰመራ ጤና ሳይንስ ኮሌጅ እና ለአዲስ አበባ ፣ ለአማራ፣ ለትግራይ፣ ለአፋር እና ለደቡብ የ/ቴ/ሙ/ስ/ቢሮዎች ለሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች የኦዲት ቡድኑ ላቀርበው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ ኤጀንሲው በየትኛውም ደረጃ ለሚገኙ የቴ/ሙ/ት/ስ አመራሮች እና አሰልጣኞች የብቃት ክፍተት ሊሞላ የሚችል የአቅም ግንባታ የቅድመ ስራ እና የስራ ላይ ስልጠና በእቅድ ይዞ በበቂ ሁኔታ ያልሰጠ መሆኑን እንዲሁም የአቅም ግንባታ ስራው ሁሉንም የስልጠና ዘርፎች ያላካተተ መሆኑን ገልጸዋል፣

104. ጉዳዩ የሚመለከታቸው የኤጀንሲው የስራ ኃላፊዎች ለነባራዊ ሁኔታ በሰጡት መልስ የአመራሮችን አቅም ለመገንባት በየአመቱ የአጫጭር ስልጠና ፕሮግራም በማዘጋጀት የአመራሮችን አቅም ለማጎልበት ጥረት ያደረጉ መሆኑን ነገር ግን የሰው ሀይል ግንባታ በአንድ ጀንበር ተከናውኖ የማይጠናቀቅ በመሆኑ በቀጣይም ታቅዶ የሚሰራ መሆኑን ፣ የኢንዱስትሪ አሰልጣኝ በማፍራትም የተጀማመሩ ስራዎች ቢኖሩም በተፈለገዉ መንገድ ያልተሳካ መሆኑን ፣ ለግል ኮሌጆች የአቅም ግንባታ ስራው ሳይሰራ የቆየ ቢሆንም በዚህ አመት ግን የማሳተፍ ስራ መጀመሩን ፣ የአሰልጣኞች የማሰልጠን ጥራት ችግርን በጥናት ለመመለስ እንቅስቃሴ ላይ እንደሚገኙ ገልፀዋል ፡፡

105. የፌ/ቴ/ሙ/ት/ስ/ ኤጀንሲ የስራ ኃላፊዎች ኦዲቱ ሪፖርት መውጫ ስብሰባ ላይ በተሰጠ ምላሽ የኦዲት ግኝቱን መቀበላቸውን ገልፀዋል፡፡

106. ኤጀንሲው የቅድመ ስራ እና የስራ ላይ ስልጠና እንዲሁም የስልጠና አፈፃፀም አለመቆጣጠሩ በቴ/ሙ/ት/ስ/ ስርዓት እውቀት ያለው ብቁ አሰልጣኝ ለማፍራት እንዳይቻል እና ፈጻሚው ላይ የአቅም ክፍተት እንዲኖር አድርጓል፡፡

## የድህረ ስልጠና ክትትል ጥናቶችን

## /Impact assessment / በተመለከተ

107. ኤጀንሲው በደንብ ቁጥር 199/2003 አንቀፅ 6 ንዑስ አንቀጽ 15 መሠረት የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ስርዓት ውጤታማነቱን ለማረጋገጥ የድህረ ስልጠና ክትትል ጥናቶችን /Impact assessment / ሊያካሂድ ይገባል፡፡

108. በኦዲቱ ወቅት ለቡድኑ ቀርበው ከተከለሱ በኦዲት ቡድኑ በናሙናነት በተመረጡ የማሰልጠኛ ተቋማት፣ የክልል የቴ/ሙ/ት/ስ/ቢሮዎች እንዲሁም ባለድርሻ አካላት በተካሄዱ የመስክ ስራ ወቅት ከቀረበ ቃለ-መጠይቅ ፣ ለቤቶች ልማትና ኮንስትራክሽን ሚ/ር፣ በብረታ ብረትና ኢንዱስትሪ ልማት እንተርፕራይዝ ዘርፍ ፣ በአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ልማት ዘርፍ፣ በሰመራ ጤና ሳይንስ ኮሌጅ፣ ፕሮጅክት ኢ፣ በኤስ ኦ ኤስ የማሰልጠኛ ኮሌጅ ፣ ለሀዋሳ ፖሊ ቴ/ኮ፣ በወ/ሮ ስኂን ፖሊ ቴ/ኮ፣ በባህርዳር ሃይላንድ ኮሌ፣ በሀዋሳ የአትላስ የቢዝነስና ቴክኖሎጂ ማሰልጠኛ ኮሌጅ፣ በሻሸመኔ አፍሪካ ቤዛ ኮሌጅ የድህረ ስልጠና ጥናት ያላጠኑ መሆኑ እና በፌ/ቴ/ሙ/ት/ት/ስ ኤጀንሲ ጥናት እንዲደርግ ድጋፍና ክትትል አለመደረጉን እንዲሁም የድህረ ምረቃ ጥናት ለማድረግ በዕቅድ አለመያዙን እና ወቅታዊ የሆነ የድህረ ምረቃ ጥናት አለመደረጉን ገልጸዋል፡፡

109. የኤጀንሲው የስራ ኃላፊዎች ለነባራዊ ሁኔታ በሰጡት መልስ ከጅአይ ዜድ ጋር በመተባበር የድህረ ስልጠና ክትትል ጥናቶችን አስመልክቶ ስልጠና የሰጡ መሆኑን እና በዚህ ዓመት ጥናቱን ለመጀመር የቅድመ ዝግጅት ስራ መጀመሩን ገልፀዋል፡፡

110. የፌ/ቴ/ሙ/ት/ስ/ ኤጀንሲ የስራ ኃላፊዎች ኦዲቱ ሪፖርት መውጫ ስብሰባ ላይ በተሰጠ ምላሽ የኦዲት ግኝቱን መቀበላቸውን ገልፀዋል።

111. በመሆኑም ኤጀንሲው የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ስርዓት ውጤታማነቱን ለማረጋገጥ የድህረ ስልጠና ክትትል ጥናቶችን /Impact assessment / ባለማካሄዱ በዘርፉ የሚካሄዱ ስልጠናወች ያላቸውን ጠንካራና ደካማ ጎን በመለየት ችግሮቹ የሚፈቱበትን አቅጣቻወች ለማመላከትና የሚሰጡት ስልጠናወችን ውጤታማነትን ለማረጋገጥ እንዳይቻል ያደርጋል፤

## በኤጀንሲው ልዩ ትኩረት እና ድጋፍ

## የሚሹ ጉዳዮች አፈጻፀምን በተመለከተ

112. ኤጀንሲው ደንብ ቁጥር 199/2003 አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀፅ 13 መሰረት በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ዙሪያ ሴቶች ፣ አካል ጉዳተኞች እና ልዩ ድጋፍ ለሚሹ ክልሎች ትኩረት እንዲያገኙ የሚያስችል ስርዓት ሊዘረጋ እና ተግባራዊነቱን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

113. በኦዲቱ ወቅት ለቡድኑ ቀርበው ከተከለሱ ማስረጃዎች ኤጀንሲው በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ዙሪያ ሴቶች ፣ አካል ጉዳተኞች እና ልዩ ድጋፍ ለሚሹ ክልሎች ትኩረት እንዲያገኙ የሚያስችል የአሰራር ስርአት የዘረጋ ቢሆንም ተግባራዊነቱን ለማረጋገጥ የሚያደርገው ድጋፍ እና ክትትል በቂ አለመሆኑን እንዲሁም በ2010 ዓ.ም. የፌ/ቴ/ሙ/ስልተና ኤጀንሲ ዕቅድ አፈፃፀም አዲስ የመደበኛ የሴት ሰልጣኝ ቅበላ አፈጻጸም በሶማሌ 42% ፣ በአፋር 35% እና በጋምቤላ 16% መሆኑን ፣ የሴቶች ተሳትፎ በመደበኛ ስልጠና ላይ በጋምቤላ ስልጠና ያጠናቀቁ ብዛት 1314 ሲሆኑ የተመዘኑት 108 ( 8.2%) እና በአፋር ስልጠና ያጠናቀቁ ብዛት 503 የተመዘኑ አለመሆኑን ፣

114. እንዲሁም የአካል ጉዳተኞች የመደበኛና የአጫጭር ስልጠና ተሳትፎ ያጠናቅቁ ፣ የተመዘኑ እና ከተመዘኑት የበቁ አፈፃፀሙ ቤንሻንጉል ጉምዝ(0) እና ጋምቤላ(0) መሆኑን እነዲሁም የቤ/ጉ/ቴ/ሙ/ኢ/ል/ቢሮ የ2009 ዓ.ም የስራ አፈጻጸም ሪፖርት ለ120 አካል ጉዳተኛ ሰልጣኞች ቅበላ ለማድረግ ታቅዶ አፈጻጸሙ 50(41.6%) መሆኑ፣ በኦሮሚያ ክልል ከተመረጡ የግልና የመንግስት ተቋማት በአድማስ ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ እና ሪፍት ቫሊ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጆች ለአካል ጉዳተኖች ምቹ ሁኔታ አለመፈጠሩን /የመማሪያ ክፍሎች ፣ ሾፖች ፣ ቤተመጽሃፍት ፣ አይቲ ክፍል ፣ ማጸዳጃ ቤቶች እና ቢሮዎች ለዊልቸር ተጠቃሚ አመች አለመሆናቸውን እንዲሁም የመስማትና ማየት ውስንነት ላለባቸው ከበር ጀምሮ ኮሪደሮች ላይ ምልክቶች አለመኖራቸውን ለማወቅ ተችሏል፡፡

115. በሌላ በኩል በኦዲት ቡድኑ በናሙና ለተመረጡ ለደቡብ ፣ ለኦሮሚያ እና ለአፋር ክልል የቴ/ሙ/ት/ስ ቢሮዎች እና ለቤቶች ልማት እና ኮንስትራክሽን ሚ/ር ፣ ለሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ በአካል ጉዳተኞች በኩል በቂ የግንዛቤ ስራ ያልተሰራ መሆኑን ፣

በአፋር ክልል የክልሉን ሴቶች (የአርብቶ አደሩን ሴት ልጆች) እና ለአካል ጉዳተኞች አስፈላጊውን ግብአት ከማሟላት አንጻር ውስንነት መኖሩን እና ወርክ ሾፖች እና የስልጠና ቦታዎች ለአካል ጉዳተኞች አመቺ አለመሆናቸውን ፣ የሀዋሳ አትላስ የቢዝነስና ቴክኖሎጂ ማሰልጠኛ ተቋም ፣ የወ/ሮ ስኂን ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ፣ የሻሸመኔ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ እና የባህርዳር ሃይላንድ ኮሌጅ ለአካል ጉዳተኞች አስፈላጊውን ግብአቶች ከማሟላት አንጻር /የአይነ ስውራን ብሬል/ እጥረት መኖሩን ለአብነት የምዘና መሳሪያዎች በብሬል የታገዙ እንዳልሆኑ ፣ መስማት ለተሳናቸው ግብአቶች እንዳልተሟሉ እና ስልጠናም እንደማይሰጥ እንዲሁም በዘርፉ የሰለጠነ ባለሙያ እጥረት መኖሩን ነገረግን የፌዴራሉም ሆነ የክልሉ የቴ/ሙ/ት/ስ/ኤጀንሲ ድጋፍ እና ክትትል አለማድረጋቸውን ገልጸዋል፡፡

116. ጉዳዩ የሚመለከታቸው የኤጀንሲው የስራ ኃላፊዎች ለነባራዊ ሁኔታ በሰጡት መልስ በአጠቃላይ የሴቶችን ተሳትፎ ለመጨመር ሲባል እንደ ሀገር በሚዘጋጀው የቴ/ሙ/ት/ስልጠና ተቋማት የመግቢያ ነጥብ ሲሰራ የማበረታቻ ስራ መሰራቱን በተመሳሳይ ለታዳጊ ክልሎች ደግሞ በተለየ መልኩ ታሳቢ ተደርጎ መሰራቱ ሴቶችንና አካል ጉዳተኞችን ከቴክኒክና ሙያ ስልጠና ዘርፍ ተጠቃሚ ለማድረግ ጥረት መደረጉን እና በሰልጠናው ዘርፍ የሴቶች ተሳትፎ እያደገ ቢመጣም በታዳጊ ክልሎች በተፈለገው ደረጃ ውጤታማ መሆን ባለመቻሉ እና የሚደረገውም ድጋፍ ዝቅተኛ በመሆኑ በቀጣይ የችግሩን ምንጭ አጥንተው የመፍትሄ እርምጃ እንደሚወስዱ እንዲሁም የግል ኮሌጆችም ሆኑ የመንግስት ኮሌጆች ለአካል ጉዳተኞች ምቹ ሁኔታ በመፍጠር በኩል ችግር እንዳለባቸው በሱፐርቪዥን ማረጋገጣቸውን እና የእርምት እርምጃ እንድወሰድ ለክልሎች ማሳሰቢያ መሰጠቱን ገልጸዋል፡፡

117. የፌ/ቴ/ሙ/ት/ስ/ ኤጀንሲ የስራ ኃላፊዎች ኦዲቱ ሪፖርት መውጫ ስብሰባ ላይ በተሰጠ ምላሽ የኦዲት ግኝቱን መቀበላቸውን ገልፀዋል፡፡

118. በመሆኑም በተዘረጋው የአሰራር ስርዓት መሰረት በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ዙሪያ ሴቶች እና አካል ጉዳተኞች በሚፈለገው መጠን ተጠቃሚ እንዳይሆኑ አድርጓል፡፡

የቴ/ሙ/ት/ስ 70 በመቶ የተግባርና 30 በመቶ የንድፈ

ሃሳብ ቀመርን ያሟሉ መሆኑን በተመለከተ

119. ኤጀንሲው አዋጅ ቁጥር 954/2008 አንቀፅ 26 ንዑስ አንቀጽ1) ገፅ23 መሠረት በየተቋማቱ የሚሠጡ የቴ/ሙ/ት/ስልጠና 70 በመቶ የተግባርና 30 በመቶ የንድፈ ሃሳብ ቀመርን የሚሸፍን ስለመሆኑ ሊከታተል እና ሊቆጣጠር ይገባል፡፡

120. በኦዲቱ ወቅት ለቡድኑ ቀርበው ከተከለሱ ማስረጃዎች በየተቋማቱ የሚሠጡ የቴ/ሙ/ት/ስልጠናዎች 70 በመቶ የተግባርና 30 በመቶ የንድፈ ሃሳብ ቀመርን የሚሸፍን እንዲሆን የአሰራር ስርአት ቢዘረጋም ተግባራዊ አለመደረጉን ፣ በሙያ ደረጃ ምደባና ብቃት ምዘና እና በአጠቃላይ በውጤት ተኮር የቴ/ሙ/ት/ ስርዓት የኢንዱስትሪውን ባለቤትነት የማረጋገጥ ስራን በባለቤተነት የሚይዝ አደረጃጀት ተፈጥሮ የኢንዱስትሪ ባለቤትነት ከማረጋገጥ አንጻር ሰፊ ክፍተቶች ያሉ መሆኑን በክልሎች አብዛኞቹ የማሰልጠኛ ተቋማት የትብብር ስልጠና መውጫ ተቋማት የሌሉበት እና ያልተለዩበት ሁኔታ መኖሩን ፣ የትብብር ስልጠና ትግበራ ከጥራትም ሆነ ከሽፋን አንጻር ከፍተኛ ችግር ያበት መሆኑን ፣ በትብብር ስልጠና ጊዜ የኢንዳስትሪ ውስጥ አሰልጣኝ እጥረት መኖሩን ፣ ሰልጣኞች ለትብብር ስልጠና ወደ ኢንተርፕራይዞች ፣ ኢንዱስትሪዎችን እና ካምፓኒዎች በሚወጡበት ጊዜ የኢንዱስትሪ  አሰልጣኝ የማይመደብበት ፣ ባልተዘጋጀ አሰልጣኝ የሚሰጥበት ሁኔታ በመኖሩ፣  ሰልጣኞች ማወቅ ያለባቸውን የብቃት አሃድ በአግባቡ ሳይሰለጥኑ የሚቀሩበት ሁኔታ መኖሩን እንዲሁም የትብብር ስልጠና /Cooperative Training/ አተገባበር በየተቋሙ የተለያየ መሆኑ፣ ብዙዎቹ ኮሌጆች በየብቃት አሃዱ መሰልጠናቸውን ለማረጋገጥ በሚያስችል መልኩ አለመሆኑን ፣ የትብብር ስልጠናዎች በተዘጋጀው ስታንዳርድ መሰረት የማይተገበሩበት ሁኔታ መኖሩን ለኦዲት ቡድኑ በኤጀንሲው እና በመስክ ስራ ወቅት ቀርበው ከተከለከሱ ማስረጃዎች  ለማወቅ ተችሏል፡፡

121. በናሙና ለተመረጡ ለኦሮሚያ፣ ለደቡብ፣ ለአማራ፣ ለአፋር  ክልሎች እና ለአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር የቴ/ሙ/ት/ስ/ ቢሮዎች እና የብቃት ምዘና ማዕከላት፣ ለአነስተኛ እና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ልማት ኤጀንሲ ፣ ለብረታ ብረት ኢንዳስትሪ ልማት ኢንተርፕራይዝ ፣ ተግባረ ዕድ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ፣ ለምስራቅ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ፣ ለአዳማ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ፣ ለባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ፣ ለሰመራ ጤና

ሳይንስ ኮሌጅ ፣ ለወ/ሮ ስኒን ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ፣ ለባህር ዳር ሃይላንድ ኮሌጅ ፣ ፣ ለሀዋሳ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ እና ለሻሽመኔ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ለሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች የኦዲት ቡድኑ ላቀረበው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ እንደ ሀገር በቴክኒክ እና ሙያ የሚሰጡ ስልጠናዎች የየአካባቢውን ፀጋ(ሁኔታ) ያላገናዘቡ እና 70 በመቶ የተግባርና 30 በመቶ የንድፈ ሃሳብ ቀመርን የሚሸፍን አለመሆኑን ፣ ምክንያቱን ሲገልጹ ፖሊሲው የሃገሪቱን ተጨባጭ ሁኔታ ያላገናዘበ በመሆኑ እና ለተግባር ስልጠና የሚሆን በቂ የስልጠና ኢንዱስትሪዎች የሌሉበት ሁኔታ መኖሩን እና ፖሊሲው በአግባቡ ሥራ ላይ እየዋለ አለመሆኑን ገልጸዋል፣

122. ጉዳዩ የሚመለከታቸው የኤጀንሲው የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ የቴ/ሙ/ት/ስ 70 በመቶ የተግባር እና 30 በመቶ የንድፈ ሃሳብ ቀመር የሚከተል መሆኑ ይታወቃል ነገር ግን በሁሉም ሙያዋች ላይ መርኃ-ግብሩ የተለያየ እንደሚሆን መታዋቅ ይኖርበታል የግድ ሁሉም የሙያ አይነቶች 70/30 ይከተላሉ ማለት እንደማይቻል ነገር ግን የጥራቱ ጉዳይ አሳሳቢ እንደሆነ በፍኖተ ካርታ ጥናትም ታይቶ የመፍትሄ እርምጃም መወሰድ እንዳለበት አቅጣጫ ማስቀመጡን፡፡ የትብብር ስልጠና አፈጻጸም ዝቅተኛ መሆኑ አንድ ነገር ሆኖ ዋናው ጉዳይ ግን ጥራቱ ችግር ያለበት በመሆኑ የማስተካከያ እርምጃ ለመውሰድ ጥናት በማጥናት ላይ እንደሚገኙ ፣ በአጠቃላይ የተገኘውን ግኝት የሚቀበሉት መሆኑን እና በቀጣይ አሰልጣኞችና አመራሮች እንድሁም ኢንዱስትሪዎች ተግባርና ኃላፊነታቸውን አውቀው መስራት እንዲችሉ የሚያግዝ መመሪያ ተዘጋጅቶ ለውሳኔ ሰጭ አካል መቅረቡን ገልፀዋል፡፡

123. የፌ/ቴ/ሙ/ት/ስ/ ኤጀንሲ የስራ ኃላፊዎች ኦዲቱ ሪፖርት መውጫ ስብሰባ ላይ በተሰጠ ምላሽ ኦዲት ግኝቱ መቀበላቸው ገልፀው 70/30 እንደየሙያው ዓይነት እንደሚወሰን ገልፀዋል።

124. በመሆኑም ሰልጣኞች ተግባር ተኮር ስልጠና እንዳያገኙ የሚያደርግ በመሆኑ ጥራት ያለው ብቁ ባለሙያ እንዳይፈራ ተጽእኖ አድርጓል፡፡

### ቅንጅታዊ አሰራርን በተመለከተ

125. ኤጀንሲው ከባለድርሻ አካላት (ከቴ/ሙ/ት/ስ ቢሮዎች )፣ ከሙያ ምዘና ብቃት ማዕከላት ፣ ተቋማትን በበላይነት ከሚመሩ ሴክተር መ/ቤቶች እና አሰልጣኞች ጋር በቅንጅት ሊሰራ ይገባል፡፡

126. በኦዲቱ ወቅት ለኦዲት ቡድኑ ቀርበው ከተከለሱ ማስረጃዎች ኤጀንሲው ከቴ/ሙ/ት/ስ ቢሮዎች ፣ ከሙያ ምዘና ብቃት ማዕከላት ፣ ከማሰልጠኛ ተቋማት ፣ ከሴክተር መ/ቤቶች እና በትብብር የተግባር ስልጠና ከሚሰጥባቸው ኢንዱስትሪዎች ጋር ያለው ቅንጅታዊ አሰራር ሲታይ በደቡብ ፣በአፋር እና በአማራ ክልል የኢንዱስተሪዎች እና የማሰልጠኛ ተቋማት የጋራ እቅድ የሌላቸው መሆኑን ፣ በክልል ደረጃ የዘርፍ መሪ መስሪያ ቤቶች ጋር የኢንዱስትሪውን ባለቤተነት የሚጠይቁ ተግባራትን ለይቶ በማቀድ ወደ ተግባር መግባትና የዘርፍ መስሪያ ቤቶች ሚናቸውን እንዲወጡ ከማድረግ አንፃር ውስንነት መኖሩን ከተደረገ የሰነድ ክለሳ ለማወቅ ተችሏል፡፡

127. በኦዲት ቡድኑ በናሙና ለተመረጡ የማሰልጠኛተቋማት፣ለክልል የቴ/ሙ/ት/ስ/ቢሮዎች እና ለሌሎች ባለድርሻ አካላት በመስክ ስራ ወቅት ለኤስ ኦ ኤስ የግል የቴ/ሙ/ት/ስ/ተቋም ፣ ሀዋሳ አትላስ ኮሌጅ ፣ አዳማ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ፣ ሻሸመኔ አፍሪካ ቤዛ የቴ/ሙ/ት/ስ/ ኮሌጅ ፣ ባህር ዳር ሃይላንድ ኮሌጅ ፣ ሻሸመኔ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ እና ለሰመራ ጤና ሳይንስ ኮሌጅ የሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ ለቀረቡ ቃለ መጠይቅ በተሰጠ መልስ ከፌደራል ቴክኒክና ሙያ ትምህርት እና ስልጠና ኤጀንሲ ጋር ያለው ቅንጅታዊ አሰራር በሚፈለው መጠን ካለመሆኑንም ባሻገር ከ2008 ዓ.ም. ጀምሮ ቅንጅታዊ አሰራር እና የድጋፍና ክትትል ስራ በፌደራሉ የቴ/ሙ/ት/ስ/ኤጄንሲ በኩል የለም በሚባል ደረጃ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

128. እንዲሁም የደቡብ ፣ አማራ እና አፋር ክልል የቴ/ሙ/ት/ስ/ቢሮ የስራ ኃላፊዎች የፌ/ቴ/ሙ/ት/ስ/ኤጀንሲ ከተሰጠው ስልጣን አንጻር ህጎች እና መመሪያዎችን በወቅቱ ያለማድረስ እና የቴ/ሙት/ስልጠና መረጃዎች በወቅቱ ካለመድረሱ የተነሳ አሰራሩ የተዘበራረቀ የሚሆንበት ሁኔታ በመኖሩ በፌዴራሉ የቴ/ሙ/ት/ስ/ኤጀንሲ እና በክልሎች የቴ/ሙ/ት/ስልጠና ቢሮዎች ጋር ተናቦ ያለምስራት ችግር መኖሩን እንዲሁም /ከሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚ/ር፣ ከባህልና ቱሪዝም ሚ/ር ፣ ከአነስተኛ እና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኤጀንሲ እና ከብረታ ብረት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንተርፕራይዝ ጋራ አብሮ ለመስራት በ2010 ዓ.ም. የጋራ ዕቅድ ቢታቀድም ያልፀደቀ እና ወደ ተግባር ያልተገባበት መሆኑን ገልጸዋል፡፡

129. የኤጀንሲው የስራ ኃላፊዎች በሰጡት መልስ ክልሎች ከፌደራል ጋር በየሩብ ዓመቱ በመገናኘት ተናቦ ለመስራት እና ተቀናጅቶ ለመስራት ትኩረት መሰጠቱን እና

ከዘርፍ መ/ቤቶች ጋር ግኑኙነታቸው እየተሻሻለ መምጣቱን ገልፀዋል ይሁን እንጂ ኦዲቱ እስከ ተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ የተሰሩ ስራዎችን የሚያሳይ ማስረጃ ለኦዲት ቡድኑ አልቀረበም ፡፡

130. በመሆኑም ኤጀንሲው ከክልል ቴ/ሙ/ት/ስ ቢሮዎች ፣ ከሙያ ምዘና ብቃት ማዕከላት ፣ ተቋማትን በበላይነት ከሚመሩ ሴክተር መ/ቤቶች፤ ከስልጠና ተቋማት እና ከአሰልጣኞች ጋር በተጠናከረ ሁኔታ በቅንጅት ባለመስራቱ በቴ/ሙ/ት/ስ/ ዘርፍ በሚሰሩ ስራወች የባለድርሻ አካላት በተናጥል እና በጋራ የሚሰሯቸውን ስራዎች በአግባቡ በመለየት ቀልጣፋና ተጠያቂነት ያለው አሰራር እንዳይሰፍን እና በአሰራር የሚያጋጥሙ ችግሮች አፋጣኝ መልስ እዳያገኙና የስልጠና ሂደቱም ውጤታማ እንዳይሆን ተጽእኖ ያደርጋል፡፡

## መረጃ አያያዝን በተመለከተ፣

131. ኤጀንሲው በሀገር አቀፍ ደረጃ ያሉ የቴክኒክና ሙያ ትምህርት እና ስልጠና የማሰልጠኛ ተቋሞችን የሚመለከቱ አስፈላጊ መረጃዎችን በመሰብሰብ በማደራጀትና፤ በመተንተን ሁሉም ባለድርሻ አካላት እንዲጠቀሙበት የሚያስችል ዘመናዊ የመረጃ ዳታ ቤዝ ሊያዘጋጅና ስራ ላይ ሊያውል በየጊዜውም እንዲሻሻል ሊያደርግ ይገባል፤፤

132. ይሁን እንጂ የፌ/ቴ/ሙ/ት/ስ ኤጀንሲ በሀገር አቀፍ ደረጃ ያሉ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና የማሰልጠኛ ተቋሞች ያሉበትን ደረጃ የሚያሳይ፣ የሰልጣኞቻቸውን ቁጥር፣ የሰልጣኞቻቸውን የሙያ ብቃት ምዘና ውጤት(የሙያ ምዘናን ወስደው ብቁ የሆኑ) እና ከስራ ጋር የተሳሰሩትን(ወደ ስራ የተሰማሩ ምሩቃን) ሰልጣኞችን መጠን መረጃ በማሰባሰብ፣ በማደራጀት፣ በመረጃ ቋት(በዳታ ቤዝ) በማጠናከር እና በየጊዜው በማሻሻል የማይዝ መሆኑን፣ ከዚህ በተጨማሪ በኦዲቱ ወቅት ለኦዲት ቡድኑ ቀርበው ከተከለሱ ሰነዶች የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል ፡-

133. በቁልፍና አበይት ተግባራት ዕቅድ ሲታቀድ የሚያስፈልጉ መሰረታዊ መረጃዎችን ምን ምን እንደሆኑ የሚያሳይ መረጃ አለመደራጀቱን፣ በአብዛኞቹ ተቋማት መረጃን ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር መረጃን መለዋወጥ ላይ ክፍተቶች መኖራቸው ለማወቅ ተችሏል፡፡

134. እንዲሁም በአ/አ/ከ/መ/ቴ/ሙ/ት/ስ/ቢሮ በግልና መንግስታዊ ያልሆኑ ኮሌጆችና ተቋማት ላይ ለተካሄደ የማጥራት ስራ (ኢንስፔክሽን) የተዘጋጀ ሪፖርት፣

መንግስታዊ ባልሆኑ በጎ አድራጎት ድርጅቶች በተቋቋሙ የቴ/ሙ/ትስ/ተ ላይ የተካሄደ ክትትልና ድጋፍ ሪፖርት የታዩ ችግሮች፡ ፣ መረጃዎች በአግባቡ አደራጅቶ የማስቀመጥ ችግር መኖሩ /አደራጅቶ አለማስቀመጣቸው/፣ የተደራጀ የመረጃ አያያዝ፣ አላላክ፣ አጠቃቀም፣ የመረጃ አያያዝ በቴክኖሎጂ የታገዘ አለመሆን፣ የትብብር ስልጠና ሠነድ እና የስራ ትስስር አብዛኞቹ ተቋማቶች ላይ በመረጃ የተደገፉ አለመሆናቸው፣ የአንዳንድ ሰልጣኞች ማህደር ውስጥ አስፈላጊው መረጃ አለመያያዙ፣ የሰልጣኞችን ፕሮፋይል በአግባቡ የማይዙና የተደራጀ ሬጅስትራር የሌላቸው ተቋማት መኖራቸው፣ የተቋምና ብሄራዊ ምዘና ዉጤት በሠልጣኞች ማህደር ተሟልቶ አለመያያዙ፣

135. በተጨማሪም በኦዲት ቡድኑ በናሙናነት በተመረጡ የማሰልጠኛ ተቋማት፣ የክልል የቴ/ሙ/ት/ስ/ቢሮዎች እና ባለድርሻ አካላት በተካሄዱ የመስክ ስራ ከቀረበ መጠይቆች በደቡብ፣ ኦሮሚያ፣ በአፋር ክልል የቴ/ሙ/ት/ስ/ቢሮ፣ የወ/ሮ ስኂን ፖ/ቴ/ኮ፣ በሻሸመኔ አፍሪካ ቤዛ የግል ኮሌጅ በክልልም ሆነ በፌዴራል ደረጃ ዳታ ቤዝ የሌለ መሆኑን በሀገር ደረጃ በሲስተም የተደገፈ የመረጃ ቋት አለመኖሩ መገለፁ፣ በአማራ ክልል በክልል ደረጃ ዳታቤዙ እንዳለ ነገር ግን ከሌላው ክልል ጋር የተሳሰረ እንዳልሆነ፣ በደቡብ ክልል የሙያ ብቃት ምዘና ኤጀንሲ 2008 ዓ.ም አካባቢ ኤጀንሲው ዳታ ቤዝ አስተዋውቆ እንደነበር ነገር ግን ተግባር ላይ ያልዋለ መሆኑ መገለፁ፣

136. ጉዳዩ የሚመለከታቸው የኤጀንሲው የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ በኦዲቱ የታየበት ሁኔታ ትክክል መሆኑን ገልፀው ዳታ ቤዝ ከፍተኛ ሀብት የሚጠይቅ በመሆኑ እስካሁን ሳይሟላ መቆየቱ አሁን ግን ስራ መጀመራቸውን ገልፀዋል፡፡

137. የፌ/ቴ/ሙ/ት/ስ/ ኤጀንሲ የስራ ኃላፊዎች ኦዲቱ ሪፖርት መውጫ ስብሰባ ላይ በተሰጠ ምላሽ የኦዲት ግኝቱን መቀበላቸውን ገልፀዋል፡፡

138. ይሁን እንጂ ኤጀንሲው በሀገር አቀፍ ደረጃ ያሉ የቴክኒክና ሙያ ትምህርት እና ስልጠና የማሰልጠኛ ተቋሞችን የሚመለከቱ አስፈላጊ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ለማደራጀትና፣ ለመተንተን ሁሉም ባለድርሻ አካላት እንዲጠቀሙበት የሚያስችል ዘመናዊ የመረጃ ዳታ ቤዝ አለማዘጋጀቱ ለሃሰተኛ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀትን ለመከላከል፣ መረጃ ለጥናትና ምርምር ሲፈለግ በቀላሉ ማቅረብ እንዲቻልና በየደረጃው ካሉ ባለድርሻ አካላት ጋር መረጃን በቀላሉ ለመለዋወጥ፣ አላግባብ የጊዜንና የገንዘብ ብክነትን ለመከላከል እና በዕቅድ ለመስራት እና ያሉበት ደረጃ ለማወቅ እንዳያስችል አድርጓል፡፡

## ኤጀንሲው የቴ/ሙ/ት/ስ መረጃ በመገናኛ ዘዴ

### ለህዝብ ይፋ መደረጉን በተመለከተ፣

139. ኤጀንሲው በአዋጅ ቁጥር 954/2008 አንቀፅ 30 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት ከክልል አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር እውቅና የተሰጣቸውን መርሃ ግብሮችና የሚሰጡባቸውን ማሰልጠኛ ተቋሞች የተጠቃለለ ዝርዝር መረጃ አደራጅቶ በመያዝ በየወቅቱ በመገናኛ ዘዴ ለህዝብ ይፋ ሊያደርግ ይገባል፡፡

140. በኦዲቱ ወቅት ለቡድኑ ቀርበው ከተከለሱ ሰነዶች የታዩ ችግሮች፡ ሀገር አቀፍ የሙያ ብቃት ማዕቀፍን ለኢንዱስትሪውና ለተጠቃሚው ህብረተሰብ ለማስገንዘብ የሚሰሩ ስራዎች ጠንካራ አለመሆናቸውን በኦዲት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

141. ሀገራዊ የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት በማሳተም፣ ለብቃት ማዕከላት ማሰራጨት እና ሰርተፊኬት የተሰጣቸውን የባለሙያዎች ሀገራዊ መረጃ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ በመታገዝ ለመያዝ በኤጀንሲው ቢታቀድም ዕቅዱን ለማስፈጸም የሚያስችል ተገቢ አደረጃጀት ኤጀንሲው የሌለው በመሆኑ ተግባራዊ አለመደረጉን ከኤጀንሲው መሰረታዊ የስራ ሂደት /BPR/ ጥናት ለማወቅ ተችሏል፡፡

142. እንዲሁም የኦዲት ቡድኑ በናሙና ለተመረጡ ለክልል የቴ/ሙ/ት/ስ በሮ ሃላፊወችና የቴ/ሙ/ት/ስ ማሰልጠኛ ተቋማት የስራ ሃላፊወች ጋር ባካሄዳቸው ቃለ መጠይቆች በሰጡት መልስ የፌ/ቴ/ሙ/ስ ኤጀንሲ የመቁረጫ ነጥብ / 2ኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ካጠናቀቁ ቡኋላ ያስመዘገቡት ውጤት ወደ ቴ/ሙ/ት/ስልጠና ሲገቡ በየትኛው የስልጠና ደረጃ መሰልጠን እንደሚችሉ የሚገልፅ የስልጠና ደረጃ ትመና/ ይፋ ከማድረግ ባለፈ እውቅና የተሰጣቸውን መርሃ ግብሮች እና የሚሰጥባቸውን ማሰልጠኛ ተቋሞች የተጠቃለለ ዝርዝር መረጃ አደራጅቶ በመያዝ በየወቅቱ በመገናኛ ዘዴ ለህዝብ ይፋ የማድረግ ስራ በተሟላ ሁኔታ በፌዴራሉም ሆነ በክልሎቹ የማይሰራ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

143. ጉዳዩ የሚመለከታቸው የኤጀንሲው የስራ ኃላፊዎች ለነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት መልስ የኦዲት ግኝቱ ትክክል በመሆኑ የመረጃ አያያዛቸውን ለማዘመን ከአጋር አካላት ጋር ስራ የተጀመረ በመሆኑ በቀጣይ ፕሮጀክቱ ሲጠናቀቅ ችግሩ የሚቃለል መሆኑን ገልፀዋል፡፡

144. የፌ/ቴ/ሙ/ት/ስ/ ኤጀንሲ የስራ ኃላፊዎች ኦዲቱ ሪፖርት መውጫ ስብሰባ ላይ በተሰጠ ምላሽ የኦዲት ግኝቱን መቀበላቸውን ገልፀዋል፡፡

145. በመሆኑም ኤጀንሲው በሀገር አቀፍ ደረጃ ያሉ የቴክኒክና ሙያ ትምህርት እና ስልጠና የማሰልጠኛ ተቋሞችን የሚመለከቱ አስፈላጊ መረጃወችን በመሰብሰብ በማደራጀትና ፤ በመተንተን ሁሉም ባለድርሻ አካላት ሊጠቁምበት የሚያስችል ዘመመናዊ የመረጃ ዳታ ቤዝ ባለማዘጋጀቱና ስራ ላይ ባለማዋሉ ባለድርሻ አካላት ወቅታዊና አሰፈላጊ መረጃወቾን በማግኘት በዘርፉ የሚካሄዱትን ስልጠናዎች ውጤታማ እንዲሆኑ የሚያስችል አስተዋፅኦ እንዳያደርጉ ያደርጋል፡፡

# ክፍል ሦስት
## የመደምደሚያ ሃሳቦች

የቴክኒክና ሙ.ያ ትምህርትና ስልጠናን ውጤታማ ለማድረግ በኤጀንሲው የተደረጉ ጥረቶች መኖራቸውን እንረዳለን የክዋኔ ኦዲቱ ዓላማ የ/ቴ/ሙ/ት ስልጠና ኢኮኖሚያዊ ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ መሆኑን መገምገም ነው፡፡ ከዚህ ዓላማ አንፃር የሚከተሉት ዋና ዋና ግድፈቶች ተገኝቷል፡፡

- ❖ ኤጀንሲው የስራ ገበያውን ፍላጎት መሰረት ያደረጉ የሙ.ያ ደረጃዎችን በተሟላ ሁኔታ እና በወቅቱ ያላዘጋጀ እና ያልከለሰ መሆኑን እንዲሁም ያዘጋጃቸውንና የከለሳቸውን ደረጃወችም ለሴክተር መ/ቤቶች ፣ ለክልል ቢሮዎች እና ለምዘና ማዕከላት እና ለተቋማት መድረሳቸውን እና በአግባቡ ስራ ላይ መዋላቸውን በተሟላ ሁኔታ ያልተከታተለ መሆኑ፤
- ❖ በማሰልጠኛ ተቋማት ወቅታዊ የሙ.ያ ደረጃን መሰረት ያደረገ TTLM/CBLM ዝግጅት ላይ ወጥ የሆነ አዘገጃጀት የሌለ መሆኑ እንዲሁም ኤጀንሲው ለተቋማት ድጋፍና ክትትል ሲያደርግ የቴክኒክ እና ሙ.ያ ትምህርትና ስልጠና ስርዓተ-ትምህርቶች እና የስልጠና መሳሪያዎች መዘጋጀታቸውን ከማየት ባለፈ ተግባራዊ ስለመደረጋቸው ፣ ወቅታዊነት ያላቸው ስለመሆኑ እና ጥራት ያለቸው ስለመሆኑ በጥልቀት የማያረጋግጥ መሆኑ፡
- ❖ ኤጀንሲው የሴክቴር መ/ቤቶች እና ኢንዳስትሪዎችን በማስተባበር በፀደቁና በተከለሱ የሙ.ያ ደረጃዎች ላይ ተመስርቶ የምዘና መሳሪያዎችን በተሟላ ሁኔታ ያላዘጋጀ መሆኑ በተዘጋጁም ላይ ጥራት መጓደል ችግር እና የምዘና መሳርያ እጥረት መኖሩ እንዲሁም የክትትል ስርዓቱ ደካማ መሆኑ፣
- ❖ ኤጀንሲው የሙ.ያ ብቃት ምዘና ስርዓትን ቢዘረጋም የቴ/ሙ/ት/ስ ሰልጣኞች በምዘና ሂደት ውስጥ ስለማለፋቸው እንዲሁም የምዘና ስርአቱ ውጤታማ እንዲሆን የሚያስችል ተከታታይነት ያለው በቂ ክትትል እና ቁጥጥር ያላደረገ መሆኑ ፡
- ❖ ኤጀንሲው ሀገር አቀፍ የብቃት ምስክር ወረቀት በብቃት ማዕከላት ተዘጋጅቶ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ስለመሰጠቱ እና ዋናውን በሶስት ወር ውስጥ አዘጋጅቶ በማዕከላት በኩል ለተመዛኞች የማድረስ ስራ በተሟላ ሁኔታ እየተሰራ አለመሆኑ፣ እንዲሁም በኤጀንሲው የሚደረገው ድጋፍና ክትትል ደካማ መሆኑ፡
- ❖ ኤጀንሲው የሙ.ያ ብቃት ምዘና ማዕከላትን ተደራሽነት ለመከታተል እና ለመደገፍ የሚያስችል ውጤታማ የአሰራር ስርዓት ያልዘረጋና አፈጻጸሙን ያልተከታተለ መሆኑ እንዲሁም የሙ.ያ ብቃት ምዘና ማዕከላት ተደራሽ አለመሆናቸው፡
- ❖ ኤጀንሲው መዛኞች ለመዛኝነት ሲመረጡ የሚያስፈልጉ መመዘኛ መስፈርቶችን አሟልተው የተመረጡ ስለመሆኑ በቂ ክትትል እና ቁጥጥር ያላደረገ መሆኑ፡
- ❖ በሃገር አቀፍ ደረጃ የማሰልጠኛ ተቋማትን ተደራሽ ለማድረግ እና እውቅና እንዲያገኙ ለማድረግ በታቀደው ልክ ያልተከናወነ መሆኑ፡

❖ ኤጀንሲው በፌዴራል ደረጃ በመንግስት ፣ በግል እና በውጪ ዜጎች ለሚቋቋሙ እና በሌላ ሀገር ህግ የተቋቋሙ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ስር የሚተዳደሩ ማሰልጠኛ ተቋሞች በህጉ መሰረት ፈቃድ የወሰዱ ስለመሆኑ በቂ ክትትል እና ቁጥጥር አላደረገም፡

❖ ኤጀንሲው የማሰልጠኛ ተቋማት የስልጠና መርሃ ግብሮችን ዕውቅና ፍቃድ በተሰጠበት መመዘኛ መሰረት ስለማከናወናቸው በቂ ክትትል እና ቁጥጥር ላደረገ መሆኑ፡

❖ ኤጀንሲው በማሰልጠኛ ተቋማት የሚሰጡ ስልጠናዎች በስራ ገበያ ፍላጎት መሰረት ስለመሆናቸው በቂ ክትትል ያላደረገ መሆኑ፡

❖ ኤጀንሲው በየትኛውም ደረጃ ለሚገኙ የቴ/ሙ/ት/ስ አመራሮች እና አሰልጣኞች የብቃት ክፍተት ሊሞላ የሚችል የአቅም ግንባታ የቅድመ ስራ እና የስራ ላይ ስልጠና በእቅድ ይዞ በበቂ ሁኔታ ያልሰጠ መሆኑ፡

❖ ኤጀንሲው የማሰልጠኛ ተቋማት የድህረ ስልጠና ጥናት እንዲደርጉ ድጋፍና ክትትል ያላደረገ እና የድህረ ምረቃ ጥናት ለማድረግ በዕቅድ አለመያዙን እና ወቅታዊ የሆነ የድህረ ምረቃ ጥናት ያላደረገ መሆኑ፡

❖ ኤጀንሲው በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ዙሪያ ሴቶች ፣ አካል ጉዳተኞች እና ልዩ ድጋፍ ለሚሹ ክልሎች ትኩረት እንዲያገኙ የሚያስችል የአሰራር ስርአት የዘረጋ ቢሆንም ተግባራዊነቱን ላይ ክፍተት ያለ መሆኑ እንዲሁም የሚያደርገው ድጋፍ እና ክትትል በቂ አለመሆኑ፡

❖ ኤጀንሲው በየተቋማቱ የሚሠጡ የቴ/ሙ/ት/ስልጠናዎች 70 በመቶ የተግባርና 30 በመቶ የንድፈ ሃሳብ ቀመርን የሚሸፍን እንዲሆን የአሰራር ስርአት ቢዘረጋም ነገር ግን በየተቋማቱ የሚሰጡ ስልጠናዎች 70 በመቶ የተግባርና 30 በመቶ የንድፈ ሃሳብ ቀመርን የሚሸፍኑ አለመሆናቸው፡

❖ ኤጀንሲው ከባለድርሻ አካላት ፡ ከሙያ ምዘና ብቃት ማዕከላት ፣ ተቋማትን በበላይነት ከሚመሩ ሴክተር መ/ቤቶች እና አሰልጣኞች ጋር ያለው ቅንጅታዊ አሰራር ጠንካራ አለመሆኑ፡

❖ ኤጀንሲው ከክልል አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር እውቅና የተሰጣቸውን መርሃ ግብሮችና የሚሰጡባቸውን ማሰልጠኛ ተቋሞች የተጠቃለለ ዝርዝር መረጃ አደራጅቶ በመያዝ በየወቅቱ በመገናኛ ዘዴ ለህዝብ ይፋ የማያደረግ መሆኑ፡

ስለሆነም በኦዲቱ ወቅት የተገኙትን ድክመቶች እና ችግሮች ለማስወገድ ወይንም ለማቃለል አስተዋፅኦ ያደርጋሉ ብለን ያመንባቸውን የማሻሻያ ሃሳቦች በሚቀጥለው የሪፖርት ክፍል አቅርበናል፡፡

# ክፍል አራት

## የማሻሻያ ሀሳብ
## (Recommendation)

- ኤጀንሲው የቴ/ሙ/ሰልጣኞች ተግባር ተኮር ስልጠና እንዲያገኙ ለማስቻል የኢንዳስትሪውን ተሳትፎ በማረጋገጥ በጋራ ጥራት ያለው የገበያ ፍላጎት ጥናት በማጥናት ገበያው በሚፈልጋቸው የስልጠና መስኮች ደረጃውን የጠበቀ የሙ.ያ ደረጃ ሊያዘጋጅ እና ከሚመለከታቸው የዘርፉ ባለሙያዎችና ኢንድስትሪዎች ጋር በመቀናጀት ከዘመኑ የቴክኖሎጂ መቀያየር ጋር ለመራመድ እንዲችል ስርዓቱ በሚፈቅደው ጊዜ ውስጥ ያልተከለሱ የሙ.ያ ደረጃዎችን ሊከልስና ሰልጣኞች ወቅታዊ ስልጠና እንዲያገኙ ለማስቻል የተከለሰው የሙ.ያ ደረጃ ስልጠና ከመጀመሩ አስቀድሞ ለሚመለከተው አካል (ለሴክተር መ/ቤቶች ፣ ለክልል ቢሮዎች እና ለምዘና ማዕከላት እና ለማሰልጠኛ ተቋማት) ስለመድረሱ ሊከታተል ይገባል፡፡
- ኤጀንሲው ስርዓተ - ትምህርቶች እና የስልጠና መሳሪያዎች (Teaching and Training learning material /TTLM / እና Competency biased learning material /CBLM/ መዘጋጀታቸውን ሊያረጋግጥ እንዲሁም የማሰልጠኛ ተቋማት ዕውቅና በወሰዱባቸው የስልጠና መስኮች ወቅታዊ የሙ.ያ ደረጃን መሰረት ያደረጉ በቂ ጥራትና ወጥነት ያለው የመማር ማስተማር ስርዓተ-ትምህርቶችና የማሰልጠኛ መሳሪያዎች ስለማዘጋጀታቸው እና ተግባራዊ ስለመሆናቸው እንደሁም ለተጠቃሚው (ሰልጣኝ እና አሰልጣኝ) ተደራሽ በሚሆኑበት ሁኔታ ስለመቀመጣቸው ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡
- ኤጀንሲው የሴክቴር መ/ቤቶች እና ኢንዳስትሪዎችን በማስተባበር የሙ.ያ ደረጃ ሲያዘጋጅ አግባብ ባለው ብቁ ባለሙ.ያ ጥራቱን የጠበቀ የምዘና መሳሪያዎችን አዘጋጅቶ ሊያሰራጭ የተሰራጩትም ሚስጥራቸው ጠብቆ ለምዘና ተግባር መዋላቸውን በተጨማሪም በክልሎች የሚዘጋጁ ተጨማሪ የምዘና ቨርዥኖችን በወቅቱ አጸድቆ ሊልክና የምዘና ማዕከላት ወቅታዊ የምዘና መሳሪያዎችን ስለመጠቀማቸው በቂ ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ኤጀንሲው የሙ.ያ ብቃት ምዘና ኢንዳስትሪዎች ላይ ስለመካሄዱ ፣ በየሙ.ያ ዘርፉ በቂ መዛኝ ስለመኖሩ ፣ የምዘና መሳሪያ ያልተዘጋጀላቸውን የሙ.ያ ደረጃዎች

በመለየት እንዲዘጋጁ በማድረግ ፣ በመዛኞችና ሱፐርቫይዘሮች በምዘና ወቅት ሊደረግ ስለሚገባው ቅድመ እና ድህረ ጥንቃቄ እንዲደረግ ሊያደርግ እና ሰልጣኞች ወቅታዊ ምዘና እንዲያገኙ በማድረግ የቴ/ሙ/ት/ስ/ ሰልጣኞች በደረጃ ሂደት ውስጥ ስለማለፋቸው ሊከታተል እና ሊቆጣጠር ይገባል፡፡

- ኤጀንሲው ጊዜያዊ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት በብቃት ማዕከላት ተዘጋጅቶ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ስለመሰጠቱ ሊያረጋግጥ እና ዋናውን በሶስት ወር ውስጥ ሊያዘጋጅ እና በማዕከላት በኩል ለተመዛኞች የደረሰ ስለመሆኑ ሊከታተል ይገባል፡፡
- የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ለሦስት አመታት ብቻ ስለማገልገሉ እና ከ 3 ዓመት በኋላ የሙያ ደረጃው ከተቀየረ ባለሙያዎች ምዘናውን እንደገና እንዲወስዱ፣ ከ 3 ዓመት በኋላ የሙያ ደረጃ ካልተቀየረ የአገልግሎት ክፍያ በማስከፈል በየ ሦስት ዓመቱ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱ እንዲታደስ የማድረግ ስራ እንዲሰራ የሙያ ብቃት ምዘና ማረጋገጫ ሥርዓትን አስመልክቶ በየደረጃው ለሚገኙ አመራርና ፈፃሚ አካላት በቂ የአቅም ግንባታ ስልጠና በመስጠት አፈፀፀሙን ሊቆጣጠር ይገባል፡
- ኤጀንሲው የሙያ ብቃት ምዘና ማዕከላት ተደራሽ ባለመሆናቸው ሰልጣኞችን ወቅታዊ ምዘና እንዳያገኙ ከማድረጉም በተጨማሪ ላልተገባ የገንዘብ፣ የጉልበት እንዲሁም የጊዜ ብክነት ስለሚዳርግ  የብቃት ምዘና ማዕከላት ተደራሽ እንዲሆኑ ወቅቱን የጠበቀ እና ጥራት ያለው ምዘና ለመስጠት ያስችል ዘንድ በሙያ ብቃት ምዘና ሂደት አሠራርና ክትትል ከኢንዳስትሪው ጋር የአሰራር ስርዓት በመዘርጋትና በመደገፍ የብቃት ማዕከላትን ሊያበቃና ሊከታተል ይገባል፡፡
- ፌ/ቴ/ክ/ሙ/ት/ስ/ ኤጀንሲው የሚያስፈልጉ መመዘኛ መስፈርቶች (በሙያው ላይ በስራ የሚገኝ፣ ምዘና በሚሰጥበት ሙያ ቢያንስ ሶስት ዓመት የሰራ፣ ደረጃ አምስትን የሚመዝን ካልሆነ በቀር ምዘና ከሚሰጥበት የሙያ ደረጃ ቢያንስ በአንድ ደረጃ ከፍ ብሎ የተመዘነ፣ የሙያ ምዘና ስነዘዴ የሰለጠነበት መረጃ ያለው፣ የመዛኝነት ሙያ ፍቃድ ያለውና መልካም የሙያ ስነ ምግባር ያላቸው)  እንዲመረጡ ግንዘቤ በመፍጠር እንዲሁም ጥራት ያለው ምዘና በማካሄድ ብቃቱ የተረጋገጠ ባለሙያ ለማፍራት ያስችል ዘንድ  የመዛኞች ሚና ከፍ ያለ በመሆኑ ምዘና መስፈርቱን

በሚያሟሉ የኢንዳስትሪ ውስጥ ባለሙያወች ስለመሰጠቱ በየሙያ ዘርፉ አፈፃፀሙን ሊከታተል ይገባል፡፡

- ኤጀንሲው ዜጎች በስራ ገበያ ጥናት የተደገፈ ተግባር ተኮር ስልጠና እንዲያገኙ፣ ስልጠናው በስራ ገበያ ፍላጎት ያተኮረ፣ ተገቢው ጥራት ያለው ሆኖ ዕድሉን ላላገኙ ዜጎች የቴ/ሙ/ት/ስ አቅርቦት እንዲኖር የማሰልጠኛ ተቋማት ተደራሽ እንዲሆኑ እና እውቅና የሚያገኙበትን መመዘኛ መመርያ ሊያወጣ እና አፈጻጸሙን ሊከታተል ይገባል፡፡
- ኤጀንሲው በፌዴራል ደረጃ በመንግስት፣ በግልና በውጪ ዜጎች ለሚቋቋሙና በሌላ ሀገር ህግ በተቋቋሙ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ስር ለሚተዳደሩ ማሰልጠኛ ተቋሞች  እንዲሁም ተቋሙን ለማስፋፋት ለሚፈልጉ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ማሰልጠኛ ተቋሞች የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት የእውቅና ፈቃድ ሊሰጥ እና ሊከታተል ይገባል፡፡
- ኤጀንሲው የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠናን ከህገ-ወጥ አሰራር ለመከላከልና በዘርፉ ጥራት ያለው ስልጠና ለመስጠት የማሰልጠኛ ተቋማት የማሰልጠኛ መርሃ ግብሮቻቸው ዕውቅና በተሰጠበት መመዘኛ መሰረት ስለማከናወናቸው እና በዘርፉ የሚስተዋለውን ህገ-ወጥ አሰራር ለመቅረፍና ጥራት ያለው ገበያ ተኮር ስልጠና ይሰጥ ዘንድ የማሰልጠኛ ተቋማት ዕውቅና ፈቃድ ያላቸው ስለመሆኑና ወቅቱን ጠብቀው  ያደሱ ስለመሆናቸው ክትትል ሊያደርግና ሊቆጣጠር ይገባል፡
- ኤጀንሲው የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ሰልጣኞች ከድህረ ስልጠና በኋላ የስራ አጥነትና ተያያዥ ችግሮች እንዳያጋጥማቸው ከየዘርፉ ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ጥራት ያለው የገበያ ፍላገቶት ጥናት በማካሄድ እና በተቋማት የሚሰጠው ስልጠና በስራ ገበያ ፍላጎት ላይ የተመሰረተ መሆኑን ሊከታተል ይገባል፡፡
- ኤጀንሲው በቴ/ሙ/ት/ስ/ የሚስተዋለውን የስልጠና ጥራት ችግር ለመቅረፍ ያስችል ዘንድ በየትኛውም ደረጃ ለሚገኙ የቴ/ሙ/ት/ስ አመራሮችና አሰልጣኞች የቅድመ እና የስራ ላይ ስልጠና ሊሰጥ እንዲሁም በቴ/ሙ/ት/ስ አሰልጣኞች ስልጠና ወቅት የሚስተዋሉ ክፍተቶችን ለይቶ ለመሙላት እንዲቻል የአሰልጣኞችን ስልጠናና ቀጣይ የስልጠና አፈጻጸም ሊከታተል ይገባል፡፡
- ኤጀንሲው የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ስርዓት ውጤታማነቱን ለማረጋገጥና ክፍተቶችን ለይቶ መሙላት ያስችለው ዘንድ በሙያ በዓይነትና

በደረጃ በመለየት በየጊዜው እየተገመገመ ማሻሻያ ማድረግ እና የድህረ ስልጠና ክትትል ጥናት (Impact Assessment) ሊያካሂድ ይገባል፡፡

- ኤጀንሲው በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ዙሪያ ሴቶች፣ አካል ጉዳተኞች እና ልዩ ድጋፍ ለሚሹ ክልሎች በአንጻሩ የተሻሉ ከሚባሉ ክልሎች ጋር መራመድ እንዲችሉ በተዘረጋው ስርዓት መሰረት ተግባራዊ መደረጉን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡
- ኤጀንሲው ሰልጣኞች ትክክለኛውን የስራ አለም እንዲረዱትና በቂ ተግባር ተኮር ክህሎት እንዲጨብጡ በየኮሌጆቹ የሚሰጠው ስልጠና ሙያተኞችን 70 በመቶ በተግባር እና 30 በመቶ በንድፈ ሃሳብ በሚሸፍን ስርዓተ ትምህርት/curriculum/ ትምህርትና ስልጠና በመስጠት ከደረጃ አንድ እስከ ደረጃ አምስት እየሰጡ መሆኑን፣ ሊከታተል ይገባል፡፡
- ኤጀንሲው አላማውን ለማሳካት የባለድርሻ አካላት ሚና የጎላ በመሆኑ ስርዓት በመዘርጋት እንዲሁም በየኮሌጆች ያለው አሰራር ቀልጣፋና ውጤታማ ለማድረግ ሰልጣኞችን ኢንዳስትሪዎች በሚፈልጉት እውቀትና ክህሎት ደረጃ ብቁ አድርጎ ለማፍራት እና ያለባቸውን የክህሎት ክፍተት በየትምህረት ደረጃው በወቅቱ እንዲሞሉ ለማስቻል በቴ/ሙ/ት/ስልጠና ዘርፍ ምርጥ ተሞክሮዎችን የማሰባሰብና የማስፋት ስራዎች እንዲሁም የትብብር ስልጠና እንዲያከናውኑ ለማድረግ በቅንጅት ሊሰራ ይገባል፡፡
- ኤጀንሲው ሃሰተኛ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀትን ለመከላከል፣ መረጃ ለጥናትና ምርምር ሲፈለግ በቀላሉ ማቅረብ እንዲቻልና በየደረጃው ካሉ ባለድርሻ አካላት ጋር መረጃን በቀላሉ መለዋወጥ በማስቻል አላግባብ የጊዜንና የገንዘብ ብክነትን ለመከላከል ያስችል ዘንድ በሀገር አቀፍ ደረጃ ያሉ የቴክኒክና ሙያ ትምህርት እና ስልጠና የማሰልጠኛ ተቋሞች ያሉበትን ደረጃ የሚያሳይ፣ የሰልጣኞቻቸውን ቁጥር፣ የሙያ ብቃት ምዘና ውጤት (የሙያ ምዘናን ወስደው ብቁ የሆኑ) እና ከስራ ጋር የተሳሰሩትን (ወደ ስራ የተሰማሩ ምሩቃን) ሰልጣኞችን መጠን መረጃዎችን አቀናጅቶ ለመያዝ፣ መረጃ በማጠናከር እና በየጊዜው በማሻሻል በሲስተም የተደገፈ የመረጃ ቋት (ዳታ ቤዝ) ሊያለማ ይገባል፡፡
- ኤጀንሲው ከክልል አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር እውቅና የተሰጣቸውን መርሃ ግብሮችና የሚሰጡባቸውን ማሰልጠኛ ተቋሞች የተጠቃለለ ዝርዝር መረጃ አደራጅቶ በመያዝ በየወቅቱ በመገናኛ ዘዴ ለህዝብ ይፋ ሊደርግ ይገባል፡፡

“የኦዲት መመዘኛ መስፈርት (Evaluative Criteria)

የኦዲት አካባቢ:- የሙያ ደረጃ ምደባና ብቃት ምዘና እና የተቋማት ልማት አቅም ግንባታ አፈፃፀምን በተመለከተ፣

ኦዲት ተደራጊው መ/ቤት:- የፌዴራል ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኤጀንሲ

| የኦዲት ጭብጥ (Issues) | የመገምገሚያ መስፈርት (Evaluative criteria) |
|---|---|
| 1. ኤጀንሲው በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ብቁና ጥራቱን የጠበቀ የሰው ኃይል ለማፍራት ሀገራዊ የስራ ገበያውን የባለሙያ ፍላጎት መሰረት ያደረጉ ሙያዎችን በመለየት ደረጃውን /እስታንዳርዱን/ የጠበቀ የሙያ ደረጃ ምደባና የሙያ ብቃት ምዘና ስርዓት የዘረጋ እና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን መገምገም | ኤጀንሲው ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የስራ ገበያውን ፍላጎት መሰረት ያደረጉ የሙያ ደረጃዎችን ሊያዘጋጅ፣ ሊከልስ እና በአግባቡ በስራ ላይ መዋላቸውን ሊከታተል ይገባል፡፡ምንጭ:- በደንብ ቁጥር 199/2003 አንቀፅ 6 ንዑስ አንቀጽ 4፣ እና የሙያ አዘጋጃጀት ማኑዋል |
| | ኤጀንሲው የሙያ አዘጋጃጀት ማኑዋል፣ ስርዓተ - ትምህርቶች እና የስልጠና መሳሪያዎች (Teaching and Training learning material/Competency biased learning material) መዘጋጀታቸውን እና ተግባራዊ መደረጋቸውን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡ ምንጭ:- በደንብ ቁጥር 199/2003 አንቀፅ 6 ንዑስ አንቀጽ 5 |
| | ኤጀንሲው በፀደቁና በተከለሱ የሙያ ደረጃዎች ላይ ተመስርቶ የምዘና መሳሪያዎች ሊያዘጋጅ፣ ሊያሰራጭ እና ለአተገባበሩም አስፈላጊ ድጋፍና ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡ ምንጭ:- ደንብ ቁጥር 199/2003 አንቀፅ 6 ንዑስ አንቀጽ 5 የሙያ ብቃት ምዘና ማዕከላት ዕውቅና አሰጣጥ መመሪያ ገጽ 8 |
| | ኤጀንሲው የሙያ ብቃት ምዘና ስርዓት በመዘርጋት የቴ/ሙ/ት/ስ ሰልጣኞች በምዘና ሂደት ውስጥ ያለፉ ስለመሆኑ ሊከታተል እና አፈፃፀሙን ሊቆጣጠር ይገባል፡፡ ምኝጭ:- ደንብ ቁጥር 199/2003አንቀፅ 6 ንዑስ አንቀጽ6 |
| | ኤጀንሲው ለሙያ ብቃት ምዘና ሀገር አቀፍ የብቃት ምስክር ወረቀት አሰጣጥ ስርዓትን በመዘርጋት አፈፃፀሙን ሊቆጣጠር |

| | |
|---|---|
| | ይገባል፡፡ምንጭ፡-ደንብ ቁጥር 199/2003አንቀፅ 6 ንዑስ አንቀጽ6፣የቴ/ሙ/ት/ስ/ስ .0.6 ገፅ 52 |
| | ኤጀንሲው የሙያ ብቃት ምዘና ማዕከላትን በማብቃት ተደራሽነት ለመከታተል እና ለመደገፍ የሚያስችል የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋና አፈጻጸሙን ሊከታተል ይገባል፡፡ ምንጭ፡- ሙያ ብቃት ምዘና ማዕከላት ዕውቅና አሰጣጥ መመሪያ፣ገጽ 8 |
| | ኤጀንሲው መዛኞች ለመዛኝነት ሲመረጡ የሚያስፈልጉ መመዘኛ መስፈርቶችን ያሟሉ ስለመሆኑ ሊከታተል ይገባል፡፡ ምንጭ፡- የሙያ ብቃት ምዘና ማዕከላት ዕውቅና አሰጣጥ መመሪያ፣ ገጽ 6 |
| 2. ኤጀንሲው በሃገር አቀፍ ደረጃ የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና አሰልጣኞችን፣ ተቋማትን እና ሰልጣኞችን አቅም ለመገንባት ፣ ድጋፍ እና ክትትል ለማድረግ እና እውቅና መስጠት የሚያስችል ፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ የአሰራር ስርአት የዘረጋ እና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን መገምገም፡፡ | ኤጀንሲው የማሰልጠኛ ተቋማት ተደራሽ እንዲሆኑ እና እውቅና የሚያገኙበትን መመዘኛ መመርያ ሊያወጣ እና አፈጻጸሙን ሊቆጣጠር ይገባል፡፡ ምንጭ፡- የቴክኒክ እና ሙያ ትምህርት እና ስልጠና ኢጀንሲ ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 199/2003አንቀፅ 6 ንኡስ አንቀፅ 7 እና ትራንፎርሜሽን ዕቅድ (2008-2012) ነሀሴ 2007 ዓ.ም. የታተመ ገፅ 28 |
| | ኤጀንሲው በፌዴራል ደረጃ በመንግስት ፣ በግልና በውጪ ዜጎች ለሚቋቋሙና በሌላ ሀገር ህግ በተቋቋሙ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ስር ለሚተዳደሩ ማሰልጠኛ ተቋሞች እንዲሁም ተቋሙን ለማስፋፋት ለሚፈልጉ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ማሰልጠኛ ተቋሞች የእውቅና ፈቃድ ሊሰጥ እና ሊከታተል ይገባል፡፡ (ምንጭ፡-አዋጅ ቁጥር 954/2008 አንቀፅ 29 ንዑስ አንቀጽ2) ገፅ 25 |
| | ኤጀንሲው የማሰልጠኛ ተቋማት የስልጠና መርሃ ግብሮችን ዕውቅና ፍቃድ በተሰጠበት መመዘኛ መሰረት ስራወችን የማያከናውኑ ተቋማትን የዕውቅና ፈቃዳቸውን መሰረዙ/መታገዱ እንዲሁም የዕውቅና ፍቃዳቸው የማያሳድሱ ተቋማት ክትትል ሊያደርግ እና ሊቆጣጠር ይገባል፡፡ምንጭ፡- የቴክኒክ እና ሙያ ትምህርት እና ስልጠና ኢጀንሲ አዋጅ ቁጥር 954/2008 አንቀፅ 31 ንዑስ አንቀጽ1) ገፅ27 ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 199/2003 አንቀፅ 6 ንኡስ አንቀፅ 7 እና ዕውቅና አሰጣጥ መመሪያ ገፅ 23 እና 25 |

| | |
|---|---|
| | ኤጀንሲው በማታ ፕሮግራም ስልጠና የሚሰጡ ተቋማት የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ፈቃድ ያላቸው መሆኑን ሊከታተል እና ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡ (ምንጭ፡- የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት የፕሮግራም ምዝገባና የእውቅና ፈቃድ አሰጣጥ መመሪያ ሰኔ/2003ዓ.ም ገጽ27) |
| | ኤጀንሲው ለቴ/ሙ/ት/ስ የስራ ገበያ ክትትል የሚደረግበት ስርዓት ሊዘረጋ እና በተቋማት የሚሰጠው ስልጠና በስራ ገበያ ፍላጎት መሰረት መሆኑንና ጥራት ያለው መሆኑን ሊከታተል ይገባል፡፡ (ምንጭ፤-የቴ/ሙ/ት/ስ አስትራቴጂ 7.1 ገፅ 36 እና 52 |
| | ኤጀንሲው የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና የሥራ ኃላፊዎችና አሰልጣኞችን የብቃት መስፈርት ሊያዘጋጅና ተግባራዊነቱን ሊከታተል ይገባል፡፡ (ምንጭ፡-የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኤጀንሲ ማቋቋሚያ የሚኒስቴሮች ምክር ቤት ደንብ 199/2003 ገፅ 5773 |
| | ኤጀንሲው በየትኛውም ደረጃ ለሚገኙ የቴ/ሙ/ት/ስ አመራሮች እና አሰልጣኞች የቅድመ ስራ እና የስራ ላይ ስልጠና ሊሰጥ እንዲሁም ቀጣይ የስልጠና አፈፃፀም ሊቆጣጠር ይገባል፡፡ ምንጭ፡- አዋጅ ቁጥር 954/2008 አንቀጽ 18 ንኡስ አንቀጽ 1 ገጽ19 እና የቴ/ሙ/ት/ስ አስትራቴጂ 12.0.6 ገፅ 53 መሠረት |
| | ኤጀንሲው የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ስርዓት ውጤታማነቱን ለማረጋገጥ የድህረ ስልጠና ክትትል ጥናቶችን /Impact assessment / ሊያካሂድ ይገባል፡፡ ምንጭ፡- ደንብ ቁጥር 199/2003 አንቀፅ 6 ንዑስ አንቀጽ 15 መሠረት |
| | ኤጀንሲው በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ዙሪያ ሴቶች ፣ አካል ጉዳተኞች እና ልዩ ድጋፍ ለሚሹ ክልሎች ትኩረት እንዲያገኙ የሚያስችል ስርዓት ሊዘረጋ እና ተግባራዊነቱን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡ ምንጭ፡-ደንብ ቁጥር 199/2003 አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀፅ 13 |
| | ኤጀንሲው በየተቋማቱ የሚሠጡ የቴ/ሙ/ት/ስልጠና 70 በመቶ የተግባርና 30 በመቶ የንድፈ ሃሳብ ቀመርን የሚሸፍን ስለመሆኑ |

| | |
|---|---|
| | ሊከታተል እና ሊቆጣጠር ይገባል፡፡ ምንጭ፡-አዋጅ ቁጥር 954/2008 አንቀፅ 26 ንዑስ አንቀጽ1) ገፅ23 |
| 3. ኤጀንሲው ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት መስራቱን እና ቀልጣፋና ውጤታማ የሆነ የመረጃ ልውውጥ ስርአት የዘረጋ እና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን መገምገም፡፡ | ኤጀንሲው ከባለድርሻ አካላት (ከቴ/ሙ/ት/ስ ቢሮዎች ኤጀንሲዎች)፣ ከሙያ ምዘና ብቃት ማዕከላት ፣ ተቋማትን በበላይነት ከሚመሩ ሴክተር መ/ቤቶች እና አሰልጣኞች ) ጋር በቅንጅት ሊሰራ ይገባል፡፡ ( ምንጭ ፡-መልካም ተሞክሮ) |
| | ኤጀንሲው ከክልል አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር እውቅና የተሰጣቸውን መርሃ ግብሮችና የሚሰጡባቸውን ማሰልጠኛ ተቋሞች የተጠቃለለ ዝርዝር መረጃ አደራጅቶ በመያዝ በየወቅቱ በመገናኛ ዘዴ ለህዝብ ይፋ ማድረግ አለበት፡፡ (ምንጭ፡-አዋጅ ቁጥር 954/2008 አንቀፅ 30 ንዑስ አንቀጽ2) |
| | ኤጀንሲው በሀገር አቀፍ ደረጃ ያሉ የቴክኒክና ሙያ ትምህርት እና ስልጠና የማሰልጠኛ ተቋሞች ያሉበትን ደረጃ የሚያሳይ ፣ የሰልጣኞቻቸውን ቁጥር፣ የሰልጣኞቻቸውን የሙያ ብቃት ምዘና ውጤት (የሙያ ምዘናን ወስደው ብቁ የሆኑ) እና ከስራ ጋር የተሳሰሩትን (ወደ ስራ የተሰማሩ ምሩቃን) ሰልጣኞችን መጠን መረጃ በመረጃ ቋት( በዳታ ቤዝ) አጠናክሮ ሊይዝና በየጊዜው ሊያሻሽል ይገባል፡<br>(ምንጭ፡-አዋጅ ቁጥር 954/2008 አንቀፅ 40 ንዑስ አንቀጽ 2ና 3 እንዲሁም ደንብ ቁጥር 199/2003 አንቀፅ ፣) |